# የማስረጃ ህግ

# መግቢያ

በፍ/ቤት ክርክር የሚደረገባቸው ጉዳዮች ሁሉ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ማስረጃን የሚመለከቱ ጥያቄዎች የሚያስነሱ ናቸው ለማለት ይቻላል ። ውሳኔ ሊሰጥባቸው የተፈለጉ ጭብጦች ህጉን የሚመለከቱ ቢሆን እንኳ ወደ ህግ ጭብጥ ነት ደረጃ ከመድረሳቸው በፊት ፍሬ ነገሮቸን የሚመለከቱ ጭብጦች ደረጃ ከመድረሳቸው በፊት ፍሬ ነገሮችን የሚመለከቱ ጭብጦች እደሚያስተናግዱ የሚታወቅ ነው ። ፍሬ ነገሮቹን የሚመለከቱት ጭብጦች የሚያረጋግጡት ወይም የሚያስተባብሉት ደግሞ በማስረጃ አማካኝነት ነው ።

በሌላ በኩል ደግሞ የፍሬ ነገሮች መኖር ወይም የመደምደሚያን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ወይም ለማስተባበል ያስችላል ተብሎ የቀረበ ማስረጃ ሁሉ እንደተባለው ያረጋግጣል ወይ ያስተባብላል ለማለት አይቻልም ። ማስረጃው እውነተኛ ወይም ትክክለኛ ላይሆን ይችላል ።ወይም እውነተኛ ወይም ትክክለኛ ቢሆን እንኳን ያስረዳዋል ወይም ያስተባብለዋል የተባለው ፍሬ ነገር ወይም የተደረሰው መደምደሚያ በተፈለገው ደረጃ ላያስረዳ ይችላል ።

ስለዚህም ማስረጃውን የሚቀበለው ፍ/ቤት የቀረበለትን ማስረጃ የመመዘን ኃላፊነት ይወድቅበታል ፡፡ የሚመዘነው ደግሞ በአንድ በኩል በማስረጃነት የተገለፀው ፍሬ ነገር እውተኛ ወይም ትክክለኛ መሆን አለመሆን ለማጣራት ነው ፡፡ ማለትም ውሳኔ ለመስጠት ተገቢው የሆነውን ፍሬ ነገር መኖር ለማረጋገጥ ወይም ለማስተባበል በማስረጃነት የቀረበው ፍሬ  ነገር እውነት ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጥያቄ መሰረት በማድረግ ያጣራል ፡፡ በሌላ በኩልም የተባለው ማስረጃ እውነተኛ ነው ወይስ አይደለም  የሚለውን ጥያቄ መሰረት በማድረግ ያጣራል ፡፡ በሌላ በኩልም የተባለው ማስረጃ እውነተኛ ወይም ትክክለኛ ነው ቢባል ውሳኔ ለመሰጠት ተፈላጊ የሆነው ፍሬ ነገር ወይም ጭብጥ በሚፈለገው ደረጃ ማስረዳቱን ወይም ማስተባበሉን ያጣራል ፡፡ ስለዚህ  የቀረበው ማስረጃ

በሚፈለገው ደረጃ አስረድቷል ወይስ አላስረዳም "ለሚለው ጥያቄ መልስ ለመስጠት ፍርድ ቤቱ የማስረጃ ምዘና ተግባራት ማከናወን ይጠበቅበታል ፡፡ የዚህ ዝግጅት ዋንኛ ትኩረትም በወንጀልና በፍ/ሔር ጉዳዮች የማስረጃ ምዘና ሲከናወን ግምት ውስጥ ሊገቡ የሚገባቸው መሰረታዊ ነጥቦች በመጥቀስ ለውይይት በር መክፈት ነው ፡፡ በዚህ መሰረት ማስረጃ ሲመዘን ከቀረበው ማስረጃ እና ከጉዳዩ ዓይነትና አንፃር የማስረጃውን እውነተኛነት ወይም ትክክለኛት ለማረጋገጥ ምንም ነገሮችን ግምት ውስጥ ማስገባት እንደሚገባ፣ እንዲሁም ለጉዳዩ አግባብነት ካለው የአስረጅነት ደረጃ አንፃር የቀረበው ማስረጃ ተፈላጊው ፍሬ ነገር አስረድቷል ለማለት የሚበቃው ምን ዓይነት መመዘኛዎችን ሲያሟላ የፍርድ ቤት መዛግብትን እና ተሞክሮዎችን መሰረት በማድረግ ይገልፃል ፡፡

የቀጠለ

ዝግጅቱ በሶስት ክፍሎች በዘጠኝ ምዕራፎች የተከፋፈለ ነው ። በክፍል አንድ ስር የተካተቱት ሁለት ምዕራፎች (ምዕራፍ 1 እና 2) ማስረጃን በሚመለከት አጠቃላይ ግንዛቤ የሚሰጡ ናቸው ። ማስረጃ ምን ማለት እንደሆነ ለምን እንደሚያስፈልግ፣ ዓይነቶቹን ፣በልዩ ሁኔታ ማስረጃ ማቅረብ የሚያስፈልጋቸውን ፍሬ ነገሮች በአጭሩ ይገልፃሉ ። በክፍል ሁለት ስር የተካተቱት ሶስት ምዕራፎች(ከምዕራፍ 3-5)የማስረጃ አቀራረብን የሚመለከቱ ሲሆን ለፍርድ ቤት መቅረብ የሚችሉት ምን ዓይነት ማስረጃዎች እንደሆኑ ማን እና እንዴት እንደሚያቀርባቸው እንዲሁም ችሎት የቀረቡት ማስረጃዎች የገለፀት ፍሬ ነገር እንዴት እንደሚሰበሰብ መሰረታዊ ነጥቦች ይገልፃሉ ። ሶስተኛውን የዝግጅቱ አብይ ጉዳይ ማስረጃ መመዘንን የሚመለከት ሆኖ በዚህ ስር ከተጠቃለሉ አራት ምዕራፎች በመጀመሪያ (ምዕራፍ 6 ሥር በወንጀልና በፍ/ሐር ጉዳዮች ላይ ያስረዳሉ ተብሎ የሚቀርብ ማስረጃ አስረድቷል ለማለት

# የቀጠለ

ማሟላት የሚጠበቅበት ተፈላጊው የአስረጂነት ደረጃ ምን እንደሆነ የሚገለጽ ሲሆን በተከታዮቹ ሶስት ምዕራፍ ደግሞ በምዕራፍ 6 ላይ የተገለፀውን የአስረጂነት ደረጃ ማሟላት አለማሟላታቸውን ለማረጋገጥ የተለያዩ ዓይነት ማስረጃዎች እንዴት ሊመዘኑ እንደሚገባ እና ማስረጃዎቹ ሲመዘኑ ግምት ውስጥ መግባት የሚኖርባቸው ጉዳዮች ይገልፃሉ ፡፡

በየክፍሉ ከተለያዩ የህግ ድንጋጌዎች እና የፍርድ ጉዳዮች የተወሰዱ ጠያቂዎች የተካተቱ ሲሆን ዓላማቸውም የሰልጠናው ተከፋዮች እነዚህን ጥያቄዎች መሰረት በማድረግ የቡድን ውይይት እንዲያደርጉና ልምድ እዲለዋወጡ ማስቻል ነው ፡፡

# ክፍል አንድ

## ስለማስረጃ አጠቃላይ ግንዛቤ

## ምዕራፍ 1

## የማስረጃ ጽንሰ ሐሳብ አስፈላጊነትና ዓይነቶች

1. ማስረጃ ምንድ ነው ? ለሚለው ጥያቄ የአገራችን ህጎች ግልጽ መልስ አይሰጡም በህጎቻቸው ውስጥ የማስረጃ ጉዳይን የሚመለከቱ በርካታ ድንጋጌዎች ቢኖሩም ማስረጃ ግን አይተረጉሙትም ። ስለዚህም ማስረጃ ለሚለው ቃል ትርጉም ለመፈለግ ሌሎች ምንጮችን መመርመር ግዴታ ይሆናል ።

## የቀጠለ...

2 ከመዝገቡ ቃላት አንፃር "ፍሬ ነገርን ወይም በጭብጠነተ የተያዘን ጉዳይ መኖር ወይም አለመኖር አስመልክቶ ውሳኔ ሰጭውን ክፍል የማሳመን ውጤት ለመፍጠር ታቅዶ የሚቀርብ ማናቸውም ፍሬ ነገር ነው "የሚል ፍቺ ይሰጠዋል ። በአገራችን ማስረጃን አስመልክቶ ከተፃፈ ጹሑፎች ዓለማየሁ ሐይሌ "የኤክስፐርት ማስረጃ በኢትዮጵያ ህግ በማነፃፀር የቀረበ "በሚል ጹሑፋቸው (ገጽ 56)ላይ ማስረጃን "ለፍርድ ቤት ግምት መሰረት በመሆን ውሳኔ ሊያሰጡ ከሚችሉት ከነዚህ ፍሬ ነገሮች በመነሳትግምት የሚወሰድበት ነጥብ ላይ የሚደረስበት ሥረዓት ነው " ብለውታል። ከውጭ ሀገር ፀሐፊዎች ደግሞ (Richard may ) ማስረጃ ማንኛውም ፍሬ ነገርን ወይም መደምደሚያን ለማረጋገጥ ወይም ለማስተባባል የሚጠቅም ነገር ነው የክስ መስማት ሂደትን በተመለከተም ማስረጃ ማለት በጭብጥ የተያዙትን ፍሬ ነገሮች ለማረጋገጥ ወይም ለማስተባባል ተብሎ የሚቀርብ መረጃ ነው" ይሉታል ።

## የቀጠለ ..

3 ስለዚህ ከነዚህ ለማስረጃ ከተሰጡ ፍቺዎች የምንረዳቸው ቁም ነገሮች፡-

- ማስረጃ ለፍርድ ቤት የሚቀርቡ መረጃ ሲሆን ይህ መረጃም ፍሬ ነገርን የሚለከት ነው ፡፡
- ይህንን ፍሬ ነገርን የሚለከተው መረጃ ማስረጃ የሚያሰኘው በፍርድ ቤት በጭብጥ የተያዘን ፍሬ ነገር ወይም መደምደሚያ እውነተኛነት ወይም ትክክለኛነት ማረጋገጥ (proving any fact in issue or conclusion ) የሚረዳ በመሆኑ ነው ፡፡

4. በዚህም መሰረት ከማስረጃ ምንነት ጋር በተያያዘ የሚከተሉትን ማስተዋል ተገቢ ነው በመጀመሪያ ደረጃ ፍሬ ነገርን ወይም መደምደሚያን ለማረጋገጥ ወይም ለማስተባበል የሚቀርብ ይሁን እንጂ ማስረጃ ራሱ ፍሬ ነገር መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል ፡፡

## የቀጠለ ...

ማስረጃ ማለት ማስረጃ የፍሬ ነገርን መኖር ወይም መደምደሚያን ለማረጋገጥ ወይም ለማስተባባል የሚቀርብ እንጂ የህግ ጉዳይን ለማረጋገጥ ወይም ለማስተባበል የሚቀርብ አይደለም ። ህግን የሚመለከት ክርክር የተነሳ እንደሆነ ውሳኔ የሚያገኘው ህጉን በመመርመር ነው እንጂ ማስረጃ በማቅረብ አይደለም ። ማስረጃ የህግ ክርክርን ለማስረዳት የሚቀርብ አይደለም ።

## 1.2. የማስረጃ አስፈላጊነት

ማስረጃን በሚመለከት ጉዳይ ቀዳሚ የማስረጃ ህግ መርህ ተደርጎ የሚወሰደው የፍሬ ነገርን መኖር ወይም አለመኖር በመግለጽ ወይም አንድ ዓይነት መደምደሚያ እንዲወስድ ወይም እንዳይወስድ በሚል የሚጠየቅ ወይም የሚከራከር ማንኛውም ሰው ማስረጃ በማቅረብ ይህንን አቋሙን ማስረዳትና ፍርድ ቤቱን ማሳመን አለበት የሚለው ነው ስለዚህ የማስረጃ አስፈላጊነት ስለ አንድ ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖር ወይም ስለተወሰደ መደምደሚያ ትክክለኛ መሆን ወይም አለመሆን በፍርድ ቤት ግምት መሰረት በመሆን ውሳኔ መሰጠት ማስቻል ነው ።"

## **1.3. የማስረጃ ዓይነት**

1. የአንድን ፍሬ ነገር መኖር ወይም የመደምደሚያን ትክክለኛነት ለማረጋጠ ወይም ለማስተባባል ከሚቻልባቸው ዘዴዎች እና ማስረዳት ከሚፈለገው ፍሬ ነገር ወይም መደምደሚያ ጋር ማስረጃው የሚኖረውን ግንኙነት መሰረት በማድረግ ማስረጃን በተለያዩ መንገዶች ከፋፍሎ መረዳት ይቻላል ፡፡ **ፍሬ ነገርን ለማስረዳት ከምንጠቀምበት ዘዴ አንፃር** ማስረጃን

የምስክርነት ማስረጃ (Testimonial Evidence )

የሰነድ ማስረጃ (Document Evidence ) እና

ገላጭ ማስረጃ (Real or Demonstrative Evidence )በሚል ከፋፍሎ መመልከት ይችላል ፡፡

2. እንዲሁም በማስረጃነት የሚገለፀው ፍሬ ነገር ሊያስረዳው **ከተፈለገው ፍሬ** ነገር ወይም **መደምደሚያ ጋር ካለው ግንኙነት** አንፃር ማስረጃን ቀጥተኛ ማስረጃ (Dircet Evidence) ቀጥተኛ ያልሆነ ማስረጃ (Indirect Evidence )በሚል ይከፋፈላል ፡፡

## ሀ) ምስክርነት

- ምስክርነት ሰዎች በአካል ፍርድ ቤት ቀርበው ለችሎት መረጃ የሚሰጡበት መንገድ ሲሆን ፍሬ ነገሩን ለፍርድ ቤቱ የሚገልፁት በመሰረቱ በንግግር ነው ፡፡ (እንደ ሁኔታው ግን ምስክሮች በምልክት ቋንቋ እየገለፁ ለፍ/ቤቱ ሊተርጉም ይችላል ፡፡) በምስክርነት የቀረቡ ሰዎች በባለሙያ ምስክርነት ቀርቡም ወይም በሌላ ሁኔታ ዋነኛ መገለጫው ችሎት በግንባር ቀርበው ከፍርድ ቤቱ ጋር ቀጥታ ግንኙነት በማድረግ በአብዛኛው በንግግር በልዩ ሁኔታ በምልክት (መናገር የማይችሉ ሲሆኑ )ወይም በዳኞች ፊት ድርጊት በማሳየት ስለሚያወቁት ነገር መግለፃቸው ነው ፡፡ እነዚህ ሰዎች የሚገልፁት ፍሬ ነገር በዚሁ ጽሑፍ ውስጥ " የምስክር ቃል " በሚል የሚገለጽ ሲሆን ከንግግር በተጨማሪ በምልክት ወይም በድርጊት የተሰጠ የፍሬ ነገር መግለጫን እንደነገሩ አግባብነት ያጠቃልላል ፡፡

## ለ .ሰነዶች

1. የሰነድ ማስረጃ የሚባለው በላዩ ላይ የተፃፈበት፣የተሰለበት፣ወይም ማናቸውም ዓይነት ምልክት የተደረገበት፣ወይም ድምጽ የተቃደበት ወይም ድምጽና ምስል የተቀረፀበት ይዘቱ ማለትም የተፃፉው ጹሑፍ፣የተባለው ስዕል፣ወይም የተደረገው ምልክት ወይም የተቃደው ወይም የተቀረፀው ድምጽ ወይም ምስል ለአስረጂነት የሚቀርብ ማናቸውም ነገር ነው ። በዚህም መሰረት በጹሑፍ የተገለፁ ነገሮች (ለምሳሌ ውሎች፣ቼኮች፣ለፓሊስ ወይም ለፍርድ ቤት የተሰጠው የእምነት ቃል የተመዘገበት በጹሑፍ የተገለፀ የላብራቶሪ ወይም የህክምና ምርመራ ውጤት የሰነድ ማስረጃ ነው ። እንዲሁም ስዕሎች፣ቻርቶች፣በድንጋይ ላይ የተቀረፁ ነገሮች በቴፕና የቪድዮ ካሳቶች ዴስኮች የተፈለገው ይዘታቸው እስከሆነ ድረስ የሰነድ ማስረጃ ናቸው ።

# የቀጠለ

## ሐ) ገላጭ ማስረጃዎች

- እነዚህ ፍርድ ቤት እንዲያያቸውና ግንዛቤ እንዲወስድባቸው የሚቀርቡ ነገሮች ናቸው ለምሳሌ በወንጀል ድርጊት ንብረት ወይም ወንጀል ለመፈፀም አገልግሎት ላይ የዋለ መሳሪያ በማስረጃነት ሲቀርብ ገላጭ ማስረጃ ይባላል ፡፡ አገልግሎቱም ፍርድ ቤቱ ተመልክቶ አንድ ዓይነት ግንዛቤ እንዲወስድ ማስቻሉ ነው ፡፡ ተከሳሹ ግድያ ፈፀመበት የተባለው ቢላዋ በማስረጃነት ቢቀርብ ፍርድ ቤቱ ይህንን ተመልክቶ መሳሪያው የተባለውን ጉዳት ለማድረስ ብቃት እንዳለውና የተከሳሹን ቁርጠኝነት ----ወዘተ በሚመለከት ግምት ይወስድበታል ፡፡ የተሰረቀ እቃ ፍርድ ቤቱ እንዲመለከተው ቢቀርብም የከሳሽ ዐ/ህግ ክስና ምስክሮች እንደሚገልፁት ዕቃው በአንድ ሰው ሸክም ከቦታ ቦታ ሊንቀሳቀስ መቻል አለመቻሉን በተመለከተ ግንዛቤ ለመውሰድ ይጠቅማል ፡፡

## 1.3.2.ለማስረዳት ከተፈለገው ፍሬ ነገር ግንኙነት አንፃር የማስረጃ ዓይነቶች

### ሀ) ቀጥተኛ ማስረጃ

1. ማስረጃ ቀጥተኛ ነው የሚባለው አንድን በጭብጥ የተያዘ ፍሬ ነገር ወይም የተወሰደን መደምደሚያ ትክክለኛነት በቀጥታ ለማረጋገጥ ወይም ለማስተባባል የሚቀርቡ ሲሆን ነው ፡፡ከዚህ አንፃር ምስክር ቀርቦ በጭብጥ የተያዘው ፍሬ ነገር መኖሩን ወይም አለኖሩን ራሱ በስሜት ህዋሳቱ አማካኝነት በማየት፣በማሽተት፣በመቅመስ፣ በመስማት ወይም በመዳበስ ያወቀ መሆኑን የሚመሰክር ሲሆን ቀጥተኛ ማስረጃ ይባላል ፡፡

## የቀጠለ ...

2. በሰነድ ማስረጃ በኩልም በማስረጃነት የቀረበው ሰነድ በጭብጥ የተያዘው ፍሬ ነገር መኖሩን ወይም የተደረሰበት መደምደሚያ ትክክለኛ መሆኑን ሰነዱ ራሱ በቀጥታ ያረጋግጣል።ወይም ያስተባብላል በሚል የቀረበ ከሆነ ቀጥተኛ ማስረጃ ይባላል ። ለምሳሌ በቂ ስንቅ ሳይኖረው ቼክ ፈርሞ ሰጥቷል በሚል ገንዘብ እንዲከፍል በተከሳሽ ላይ ለቀረበ ክስ ከሳሽ ቼኩን በማስረጃነት ያቀረበ ቢሆን ተከሳሹ ስለመፈረም አለመፈረሙ እና ስለገንዘቡ ልክ ቼኩ በቀጥታ የሚናገር ስለሆነ ቀጥተኛ ማስረጃ ይባላል ። ቼኩ ሳይሆን "ተከሳሹ ቼክ መፈረሙን እናረጋግጣለን የሚል ሌላ ሰነድ ቢቀርብ ግን ቀጥተኛ ማስረጃ አይደለም "

የቀጠለ ....

ለ) ቀጥተኛ ያልሆነ ማስረጃ

1. ማስረጃ ቀጥተኛ ያልሆነ ነው የሚባለው ከሁለት ሁኔታዎች አንፃር ነው ፡፡ አንደኛው ማስረጃ ያስረዳል የተባለውን ፍሬ ነገር ምንጩ ማስረጃው ራሱ በቀጥታ ያወቀው ሳይሆን ከሌላ ያገኘው ወይም የተረዳው ሲሆን ነው ፡፡ ምስክር ይመሰክረዋል የተባለውን ፍሬ ነገር ራሱ በቀጥታ በስሜት ህዋሳቱ የተረዳው ሳይሆን ሌላ ሰው የገለፀለት መሆኑን ጠቅሶ የሚመሰክር ሲሆን ቀጥተኛ ሳይሆን የሰሚ ሰሚ ማስረጃ (Hearsay Evidence ) ይባላል ፡፡ከላይ በቂ ስንቅ ሳይኖረው ቼክ ሰጠ በሚል በቀረበው ምሳሌ ላይ እንደተመለከተው ተከሳሹ ቼክ መፈረሙን እና የገንዘቡን መጠን የሚናገረው ቼኩ ራሱ ሳይሆን ስለዚህ ይገልፃል ፡፡ በሚል የቀረበ ሌላ ጹሑፍ ቢሆን ሰነዱ ማስረጃም በኩል የሰሚ ሰሚ የሚያሳኘው ማስረጃ ሆኖ የቀረበው ሰነድ ላይ የተገለፀው ፍሬ ነገር ስለዚህ ፍሬ ነገር አውቃለሁ በሚል ሌላ ሰው የተዘጋጀ መሆኑ ነው ፡፡

# የቀጠለ ...

2.ሁለተኛው ቀጥተኛ ያልሆነ ማስረጃ ነው የሚባልበት ሁኔታ የሚያጋጥመው አካባቢያዊ ማስረጃ (circumstantial Evidence ) የቀረበ እንደሆነ ነው ። አካባቢያዊ ማስረጃ በጭብጥ ስለተያዘው ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖር በማረጋገጥ ከዚሁ ተነስተን በጭብጥ የተያዘውን ፍሬ ነገር በተመለከተ አንድ ዓይነት መደምደሚያ ላይ እንድንደርስ የሚያደርግ ነው ።

## የቀጠለ...

አካባቢያዊ ማስረጃን ቀጥተኛ ያልሆነ የሚያሰኘው በማስረጃነት የተገለፀው ፍሬ ነገር በጭብጥ ስለተያዘው ፍሬ ነገር በቀጥታ የሚናገር ወይም የሚገልጽ ሳይሆን ሌሎች ፍሬ ነገሮችን በመግለጽ በጭብጥ ስለተያዘው ፍሬ ነገር ግምት እንዲወሰድ የሚያደርግ መሆኑ ነው ፡፡

3. ማስረጃን ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ በሚል ከፋፍሎ ማየት ለምን አስፈለገ? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል ፡፡ የአንግሎ አሜሪካ የህግ ስርዓት ተከታይ በሆኑ አገሮች በልዩ ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የሰሚ ሰሚ ማስረጃ (ምስክርም ይሁን ሰነድ ) ተቀባይነት የለውም ፡፡ ከኢትዮጵያ ህግ አንፃር ሲታይ ግን በማስረጃነት ሊቀርብ ይችላል ፡፡

## የቀጠለ ....

የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ-ሥረዓት ቁጥር 137(1) እና የፍ/ሐ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 263(1) እንደሚያመለክቱት የሰሚ ሰሚ ማስረጃ በማስረጃነት ሊቀርብ ይችላል። ነገር ግን የማስረጃ ምዘና በሚከናወንበት ጊዜ የማሰረጃው ዓይነት ተጽህኖ ሊያሳድር እንደሚችል መረዳት ያስፈልጋል ። ማስረጃ ሲመዘን "ትክክለኛነቱ አጠራጣሪነቱ ፣እውነትነቱ"(የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 263(3) የሚፈተሸ በመሆኑ ይህ የመመዘን ተግባር ሲከናወን የማስረጃው ቀጥተኛ ወይም የሰሚ ሰሚ መሆን ግምት ውስጥ መግባት አለበት ። እንዲሁም ማስረጃ ሲመዘን ትክክለኛነቱ፣ አጠራጣሪነቱ እና አውነተኛነቱ ብቻ ሳይሆን ማስረጃው እውነተኛ ፣ትክክለኛ፣እርግጠኛ ቢሆን እንኳን በጭብጥ የተያዘውን ፍሬ ነገር መኖር ለማረጋገጥ ወይም ለማስተባበል ያለው ብቃት (ማለትም እውነት ቢሆንስ ለማስረዳት ይበቃልን የሚለው ) የሚመረምር በመሆኑ የማስረጃው ቀጥተኛ ወይም አካባቢያዊ መሆን አለመሆኑን መለየት በማስረጃ ምዘና ጊዜ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው ።

## የቀጠለ...

3.1 . ባለፈው ምዕራፍ ውስጥ ማንኛው የአንድን ፍሬ ነገር መኖር ወይም የአንድን መደምደሚያ ትክክለኛነት በመግለጽ ወይም በማስተባባል የሚከራከር ሰው ማስረጃ በማቅረብ ማስረዳት እንደሚገባው ተመልክቷል። ነገር ግን ይህ መሰረታዊ መርህ የማይመለከታቸው ልዩ ሁኔታዎች አሉ ።

ማለት ከፍሬ ነገሮቹ የተለየ ባህሪይ ወይም የሚያከራክር ነገር ባለመኖሩ ምክንያት ማስረጃ ማቅረብ አስፈላጊ የማይሆንባቸው ሁኔታዎች አሉ ። እነዚህም

## የቀጠለ....

→ፍ/ቤት ግንዛቤ ሊወስድባቸው የሚችሉ ወይም የሚገቡ ፍሬ ነገሮች እንደሁም፣

→በፍ/ቤት በሚደረግ የክርክር ሂደት በተከራካሪ ወገን የታመኑ ፍሬ ነገሮች ናቸው ፡፡

3.2 እነዚህን ሁኔታዎች በቅድሚያ መረዳት የተያዘውን ጉዳይ በአግባቡ ለመወሰን አስፈላጊ ነው ፡፡ አንድ ፍ/ቤት ማስረጃ መቀበል ሳያስፈልገው ለጉዳዩ አወሳሰን ተገቢ የሆነውን ፍሬ መኖር ወይም አለመኖር ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚገባ ነው ፡፡ ወይም የታመነ ነው የሚል አቋም መውሰድ እንዲችል ማድረግ ያስፈለገውም በተለያዩ ምክንያቶች ነው፡፡

## የቀጠለ....

ደረጃ በታወቀ ፍሬ ነገር ወይም አከራካሪ ያልሆነ ማረጋገጫዎች በመመልከት መወሰን በሚቻል ፍሬ ነገር ላይ ማስረጃ መቀበሉ ትርጉም ስለማይኖረው ነው ፡፡ በይፋ የታወቀ ወይም አከራካሪ ያልሆነ ማረጋገጫን መሰረት በማድረግ በቀላሉ ሊረጋገጥ የሚችል ሆኖ እያለ ተከራካሪዎች ግን ሊካካዱበት ይችላሉ ፡፡ ይህንን መከልከል አይቻልም ፡፡ ነገር ግን ፍ/ቤቱ ራሱ ግንዛቤ ሊወስድበት የሚችል ወይም የታመኑ ምንጮችን መሰረት በማድረግ መደምደሚያ ላይ መድረስ እየቻለ ተከራካሪ ወገኖችን ማስረጃ አቅርቡ ማለት ጊዜን ገንዘብ ከማባከን ሌላ የሚጨምረው ነገር የለም ፡፡

## የቀጠለ ...

3.3 በዚህ ምዕራፍ የሚገለፁትም እነዚህ ልዩ ሁኔታዎች ናቸው ። ነገር ግን ወደ ዝርዝር ውስጥ ከመግባት አስቀድሞ በአብዛኛው የቀድሞ የማስረጃ ህግ ጹሑፎች ላይ 3ኛው ማስረጃ ማቅረብ የማያስፈልገው ፍሬ ነገር ነው ስለሚባለውና በህግ ግምት (presumption) ላይ መጠነኛ መግለጫ መስጠት ያስፈልጋል ። አንድ ፍሬ ነገር በህግ ግምት እንዲረጋገጥ ህግ በደነገገ ጊዜ ይህ ፍሬ ነገር ህግ በሚወስነው ግምት መሰረት እንደሚረጋገጥ ይታወቃል ።

በዚሁ መሰረት ፦

## የቀጠለ …

❖ከአንድ ከተረጋገጠ ፍሬ ነገር (Basic Fact) በመነሳት ሌላ ፍሬ ነገርን ወይም መደምደሚያን (presumed fact ) ትክክለኛነት መገመት እንደሚገባ ነገር ግን ይህ ግምት መውሰዱ የሚጎዳው ሰው ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ ማስተባባል እንደሚችል ህግ ሊደነግግ ይችላል ። ይህም ሊስተባበል የሚችል ግምት (Rebutable presumption) ይባላል።

የቀጠለ ....

❖እንዲሁም ከአንድ ከተረጋገጠ ፍሬ ነገር (Basic Fact) በመነሳት ሌላ ፍሬ ነገርን ወይም መደምደሚያን (presumed fact) ትክክለኛነት መገመት እንደሚገባና ይህንን ህግ የወሰደውን ግምት ግን ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ ማስተባበል እንደማይቻል ህግ ሊደነግግ ይችላል። ይህም ሊስተባባል የማይችል የህግ ግምት (irrebutable conclusive presumption ) ይባላል ።

3.4. በሌላ በኩል ግን ግምት የሚወሰድበት ፍሬ ነገር በጥልቀት ከታየ ማስረጃ ማቅረብ አስፈላጊ ያልሆነበት ሁኔታ አለ ለማለት አይቻልም ። በርግጥ ማስረጃው የሚቀርበው ግምት የሚወሰደበትን ፍሬ ነገር መኖር ወይም መደምደሚያ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አይደለም ።

## የቀጠለ...

ይህ ህግ ግምት የማረጋገጥ ነው ። ነገር ግን ህግ ግምት መሰረት የሚሆነውን ፍሬ ገነር (Basic Fact) ለማስረዳት ማስረጃ ሊቀርብበት የሚገባ ነው ። ለምሳሌ የፍ/ሔር ቁጥር 3(1) "የልጅ መፀነስ ጊዜ የሚቆጠረው ልጅ ከተወለደበት በፊት ካለው ከሶስት መቶኛው ቀን ወዲህ ነው "ይላል ። በዚህም መሰረት ልጁ የተፀነሰበት ቀን ለመወሰን የሚቻለው ልጁ የተወለደበትን ቀን ለማስረዳት ማስረጃ ማቅረብ አስፈላጊ ነው ። ይህ ልጁ የተፀነሰበትን ጊዜ ለመገመት መሰረት ነው ። ከዚህ አንፃር ምንም እንኳን ልጅ የተፀነሰበትን ቀን ለማስረዳት ማስረጃ ባይቀርብም የተወሰደበትን ቀን ለማስረዳት ግን ማስረጃ መቅረቡ አይቀሪም ። ስለዚህ ግምት የሚወሰድበት ፍሬ ነገር መኖርን ለመገመት መንደርደሪያ የሆነውን ፍሬ ነገር ለማስረዳት ማስረጃ የሚቀርብ በመሆኑ ይህ ግምት የሚወሰድበት ፍሬ ነገር በሚል በተጠቀሰው በዚህ ምዕራፍ ጉልህ ስፍራ የሚሰጠው አይደለም ።

## የቀጠለ ...

በዚህም መሰረት ቀጥሎ በፍርድ ቤት ግንዛቤ ስለሚወሰድባቸው እና ስለታመኑ ፍሬ ነገሮች ይገልፃል ።

አንድ ፍሬ ነገር በፍ/ቤት ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚችለውና ማስረጃ ማቅረብ ሲፈለግ አይደለም የሚባለው ፍሬ ነገሩ በስፋት የታወቀ (Common knowledge)

በመሆኑ ወይም ተቀባይነት ያላቸው ምጮችን (Referance form authoratve sources ) ሊረጋገጥ የሚችል ሲሆን ነው ። የአንዳንድ ፍሬ ነገሮች መኖር ወይም አለመኖር ክርክር የሚያስነሳ በስፋት የሚታወቁ በመሆናቸውም የተነሳ ዳኞች ግንዝቤ የሚወስዱባቸው ሊሆኑ ይችላሉ ። "አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ነው " "አንበሳ የዱር አራዊት ነው "----- የሚሉትን በኢትዮጵያ ውስጥ ክርክር የማያስነሱ ፍሬ ነገሮች ናቸው እንደዚህ ያሉ ፍሬ ነገሮች ማረጋገጥ ውሳኔ ለመሰጠት በሚገባ የሚታወቅ ነው በማለት የአንድን ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖር ለማስረዳት ወይም ለማስተባባል ማስረጃ ማቅረብ አያስፈልግም የሚል አቋም ሊወስዱ የሚችሉት የራሳቸውን ዕውቀት መሰረት በማድረግ ሳይሆን በአካባቢው ህብረተሰብ ዘንድ በሚገባ መታወቅን መሰረት በማድረግ ነው ።

3.5. በተጨማሪም አንዳንድ ፍሬ ነገሮች በስፋት የሚታወቁ ባይሆኑም እንኳን የነዚህን ፍሬ ነገሮች መኖር ለማረጋገጥ ወይም ለማስተባባል ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልግ ተቀባይነት ያላቸውን አስገዳጅ ምንጮች (Authoritative Sources ) በመመልከት ውሳኔ ላይ መድረስ ይቻላል ፡፡ ለምሳሌ በቂ ስንቅ ሳይኖር ቼክ ፈርሞ ስለሰጠ በቼኩ ላይ የተጠቀሰውን ገንዘብ ሊከፍል ይገባል የሚል ከሳሽ በተከሳሽ ላይ የቀረበው ክስ ተከሳሹ " ክሱ የቀረበው ለክስ ማቅረቢያ በህግ የተወሰነው ጊዜ አንድ ቀን ካለፈው በኋላ በመሆኑ በይርጋ የታገደ ነው" በሚል መቃወሚያ በያቀርብና ከሳሹ በበኩሉ ክሱን ፍ/ቤት ከቀረበበት ቀን በፊት ያለው ቀን የህዝብ በዓል ቀን በመሆኑ ሊቆጠርበት እንዳማይገባ ቢገለጽ "ክስ ከቀረበበት ቀን በፊት ያለው ቀን " የህዝብ በዓል ቀን ነው ወይስ አይደለም ሚለው ጭብጥ ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባ ሲሆን ይህንን ለማረጋገጥ ግን ፍ/ቤቱ ከሳሹን ማስረጃ እንዲያቀርብ ሊያስገድድው አይገባም ፡፡ ይሄንን

## የቀጠለ ….

- ተቀባይነት ያለው የቀን መቆጣጠሪያ በመመልከት ወይም
- ስለህዝብ በዓላት ቀናት የወጡትን አዋጆች

በመመልከት መወሰን አለበት ።

3.6. ማስረጃ መቀበል ሳያስፈልግ ግንዛቤ ሊወሰድባቸው ስለሚገቡ ፍሬ ነገሮች በህግ በግልጽ የተደነገገባቸው ሁኔታዎችም አሉ ። ለምሳሌ በ1934 ዓ/ም በቁጥር 1 የወጣው የነጋሪት ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ ላይ ማናቸውም አዋጅ ድንጋጌ ፣ህግ ፣ደንብ፣ውሳኔ፣ትዕዛዝ፣ማስታወቂያ በማናቸውም የመንግስት ስራ ላይ የተሾመ ሹም ስም፣ስራና ፊርማ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ የወጣ እንደሆነ ማናቸውም ፍ/ቤት ሊቀበለው እንደሚገባ ተደንግጓል ።በ1987ዓ/ም የወጣው የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 3/1987 እንደዚሁ በተመሳሳይ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ላይ የወጡ ነገሮችን ፍ/ቤቶች ሊቀበሉዋቸው እንደሚገባ ተደንግጓል።

## የቀጠለ ....

ስለዚህ የክርክር መነሻ የሆነው ፍሬ ነገር በነጋሪት ጋዜጣ ላይ መውጣት አለመውጣቱን ነጋሪት ጋዜጣውን በመመልከት ማረጋገጥ እንደሚገባ ሁሉ በነጋሪት ጋዜጣ ላይ የተገለፀ ፍሬ ነገር ትክክለኛነቱ ለማረጋገጥ ሌላ ማስረጃ መቀበል አያስፈልግም ። ጋዜጣውን በመመልከት ብቻ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል ።

3.7. አንድ ፍሬ ነገር መኖሩ ወይም አለመኖሩ ታምኗል የሚባለው በተከራካሪ ወገኖች በአንደኛው ስለዚህ ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖር የተገለፀውን ሌላኛው ወገን አምኖ ሲቀበለው ወይም ስምምነቱን ስገልጽ ነው ። በዚህም መሰረት የታመነውን ፍሬ ነገር በተመለከተ የታመነለት ሰው ማስረጃው አድርጎ እንዲጠቀምበት፣ወይም ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልገው በፍርድ ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ተደርጎ እንዲወሰድ የማድረግ ውጤት አለው ።

## የቀጠለ ....

3.8. የእምነት ቃል አሰጣጡን በተመለከተም ክርክሩ ከመጀመሩ በፊት ማለትም ከፍ/ቤት ውጪ የተሰጠና የማስረጃነት ዋጋ ያለው ( Evidentiary Admissino ) ወይም ከፍ/ቤት ከተጀመረው ክርከር ሂደት ማለትም ፍ/ቤት ውስጥ የተሰጡ የእምነት ቃል (Judicial Admssino ) ሊሆን ይችላል ።

3.9. ከፍርድ ቤት ውጪ የተሰጡ የእምነት ቃሎች ፍሬ ነገርን ለማስረዳት በማስረጃነት ሊቀርቡ የሚችሉ ናቸው ። (የማስረጃ ተቀባይነት የሚመለከቱ ደንቦችን እስከ አሟሉ ድረስ ማለት ነው ። )ከነዚህም መካከል

- በወንጀል ጉዳይ የወንጀሉ ድርጊት መፈፀሙን በማመን በተከሳሹ ለመርማሪ ፓሊስ ወይም ለምርመራ ቃል ተቀባይነት ፍርድ ቤት የሚሰጡ የዕምነት ቃሎች ፣
- በፍ/ሔር ጉዳይ ዕዳን በማመን ከፍ/ቤት ውጭ የተሰጡ መተማመኛዎች ተጠቃሽ ሲሆኑ እነዚህም በማስረጃነት ሊቀርቡ ይችላሉ ። ነገር ግን አምኖአል የተባለው ሰው ማስረጃ በማቅረብ ማስተባባል ይችላል ።

3.10. በፍርድ ቤት ውስጥ የተሰጡ የዕምነት ቃሎች የተለያዩ ዓይነት አላቸው ፡፡ ለምሳሌ ያህልም ፡-

- በወንጀል ጉዳይ ተከሶ ፍ/ቤት የቀረበ ተከሳሽ ክሱ ተነብቦለት ከተረዳው በኋላ የዕምነት ክህደት ቃሉን እንዲሰጥ ሲጠይቅ ወንጀሉን በማመን የሚሰጠው የዕምነት ቃል ፣
- በፍ/ሔር ጉዳይ የተከሰሰው ሰው ለፍ/ቤት በሰጠው መልስ ፣ወይም በክርክሩ ሂደቱ በቃል ፣በጹሑፍ የሰጠው የእምነት ቃል ተጠቃሽ ናቸው ፡፡

በፍ/ቤት ውስጥ የተደረገ የማመን ቃል እንደ ሁኔታው የማስረጃነት ወይንም ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልግ እንደተረጋገጠ ፍሬ ነገር የመወሰድ ውጤት ያስከትላል ፡፡

3.11. ከላይ ከተመለከተው መረዳት የሚቻለው ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልግ ፍሬ ነገሩ የተረጋገጠ ተደርጎ እንዲወሰድ የማስደረግ ውጤት ሊኖረው የሚችለው ፍ/ቤት ውስጥ የተደረገ ማመን ነው ፡፡

የቀጠለ ....

በዚህ ምዕራፍ የሚታየው በፍ/ቤት የተደረገ የእምነት ቃል ሲሆን በፍ/ሔር እና በወንጀል ጉዳዮች የተለያየ አፈፃፀም ስለአለው ለያይቶ መመርመሩ አስፈላጊ ነው ፡፡

## 2.3.2. በወንጀል ጉዳይ በችሎት የታመኑ ፍሬ ነገሮች

1. በወንጀል ጉዳይ በፍ/ቤት የታመኑ ፍሬ ነገሮች ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልግ የተረጋገጡ ተደረገው የሚወሰዱበት ዕድል በጣም ጠባብ ነው ፡፡ በወንጀል መቅጫ ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 134 ላይ እንደተመለከተው እንደተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ተደርገው የሚወሰዱት "ተከሳሹ በክሱ ማመልከቻ ላይ የተዘረዘረውን ወንጀል ለመስራቱ በሙሉ ያመነ " እንደሆነ ነው ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በወንጀል ጉዳይ፡-

•የዕምነት ቃል ሰጠ የሚባለው ተከሳሹ ራሱ ነው ፡፡ እንደ ፍ/ሔር ጉዳይ ከሳሹ (ተከሳሹ በመልስ ላይ የገለፀውን ከሳሽ ሊያምን ይችላል )

## የቀጠለ ....

ተከሰሹም ቢሆን በመሰረቱ አመነ ለመባል "በክሱ ማመልከቻ ላይ የተዘረዘረውን ወንጀል ለመስራቱ በሙሉ ያመነ"መሆኑ መረጋገጥ አለበት አንደ ፍ/ሔር ጉዳይ በዝምታ፣ወይም በግልጽ እና በዝርዝር ባለማስተባበል መነሻ አምኖአል አይባልም (የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/ 133-134 ድንጋጌ ከፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/73(1)፣83፣234፣235.241 ጋር አገናዝብ )

- ተከሳሹ ራሱ "በክሱ ላይ የተዘረዘረውን ወንጀል ለመስራቱ በሙሉ ያመነ "ሆኖ እያለ ፍ/ቤቱ " አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ዐ/ህጉ ለክሱ የሚደግፈውን ማስረጃ እንዲያቀርብ ለማዘዝና ተከሳሹም የመከላከያ ማስረጃውን እንዲያቀርብ ለመፍቀድ ይችላል ፡"የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 134(2)

2. ሆኖም ቃሉ የዕምነት ቃል የሚለውን የሟላ ሆኖ ከተገኘና ፍ/ቤቱም የዐ/ህግንና የመከላከያ ማሰረጃን መቀበል አስፈላጊ ሆኖ ባላገኘው ጊዜ የታመነው ፍሬ ነገር እንደተረጋገጠ ተቆጥሮ የጥፋተኝነት ውሳኔ ይሰጣል ይህም ማለት ፡፡

## የቀጠለ …

•ፍሬ ነገሩን ለማስረዳት ማስረጃ ማቅረብን አላስፈላጊ ያደርገዋል ። ስለዚህም ዐ/ህጉም ሆነ ተከሳሹ ማስረጃ አያቀርቡም ፣

•በቅጣቱ ላይ ካልሆነ በስተቀር ጥፋተኛነትን ባቋቋሙት ፍሬ ነገሮች ላይ ይግባኝ መጠየቅ አይፈቀድም (በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/185(1)።

### 2.3.3. በፍ/ሔር ጉዳይ በችሎት የታመኑ ፍሬ ነገሮች

1. በፍ/ቤት ውስጥ በችሎት የታመኑ ፍሬ ነገሮች ማስረጃ ሳያስፈልጋቸው ውሳኔ ለማሰጠት የሚችሉት በዋነኛነት በፍ/ሔር ጉዳይ በችሎት የተሰጡ ናቸው የሚባሉት የዕምነት ቃሎች፣

•ተከራካሪ ወገኖች የሚያቀርቡአቸው የአቤቱታ ጹሑፎች ፣እንዲሁም፣

•እነዚህ ወገኖች በፍ/ቤት ለሚደረግ የቃል ክርክር በሚሰጧቸው መልሶች ሊገለፁ ይችላሉ ። በዚህ መንገድ የተሰጡትን ቃሎች የእምነት ቃል የሚያደርጋቸው።

•ተከራካሪ ወገኖች ወይም ወኪሎቻቸው በግልጽ ማመናቸው፣

## የቀጠለ ...

• በዝምት ማለፋቸው ፣ወይም

• በአነጋገር ወይም በአገላለጽ ዘይቤ ማመናቸው ተደርጎ እዲወሰድ ማድረጋቸው ሊሆን ይችላል (የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/73(1)83፣234፣235፣241--)።

2. በተጨማሪም የፍ/ሔር ጉዳይ እንደ ወንጀል ጉዳይ በሙሉ የታመነ በመሆኑ የታመነው ፍሬ ነገር በሙሉ ማስረጃ ማቅረብ የማያስፈልገው ወይም ፣

• በገልጽም በዝምታ ወይም በአነጋገር ዘይቤ በከፊል የታመነ ሆኖ የታመነው ክፍል ብቻ ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልግ ውሳኔ ሊያሰጥ የማያስችል ሊሆን ይችላል ።

# ክፍል ሁለት

## ማስረጃን ለፍርድ ቤት ስለማቅረብ

## ምዕራፍ 3

## ስለማስረጃ ተቀባይነት

### 3.1. ጠቅላላ

1 ባላፉት ምዕራፎች ውስጥ እንደተገለፀው በተወሰኑ ልዩ ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር የአንድን ፍሬ ነገር መኖር በመጥቀስ በፍ/ቤት የሚከራከር ሰው ወይም አንድ ዓይነት መደምደሚያ ላይ ሊደርስ ይገባል በሚል የሚከራከር ሰው ማስረጃ በማቅረብ የፍሬ ነገሩን መኖር ወይም የመደምደሚያውን ትክክለኛነት ማስረዳት ይገባዋል ። የተባለው ፍሬ ነገር አለመኖሩን ወይም የተጠቀሰው መደምደሚያ ትክክለኛ አይደለም የሚል ሰውም ማስረጃ በማቅረብ ይህንኑ የማስተባበያ አቋሙን ማስረዳት አለበት።

የቀጠለ ...

2. በሌላ በኩል ደግሞ የፍሬ ነገርን መኖር ወይም የመደምደሚያን ትክክለኛነት ለማስረዳት ወይም ለማስተባበል የተፈለገው ማስረጃ በዘፈቀደ ወይም ማስረጃ አቅራቢው ስለፈለገው ብቻ ይቀርባል ማለት አይደለም ፡፡ ማስረጃው ሊቀርብ የሚችለው ተቀባይነት ስኖረው ብቻ ነው ፡፡ ተቀባይነት የሌለው ማስረጃ ሊቀርብ አይችልም ፡፡

3. የማስረጃው ተቀባይነት የሚወሰነው ደግሞ በሁለት መንገዶች ነው ፡፡ የመጀመሪያውን የማስረጃ ተቀባይነት ቀዳሚ ደንብ የማስረጃን አግባቢነት የሚመለከተው ነው ፡፡ ማለትም እንዲቀርብ የተጠየቀው ማስረጃ ያስረዳዋል ለተባለው ፍሬ ነገር አግባብነት ሊኖረው ይገባል ፡፡ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/137(1) ላይ" በዋናው ጥያቄ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ውሳኔ ስለሚሰጥበት ፍሬ ነገር ተገቢ የሆኑትና ምስክሩ በቀጥታም ሆነ ቀጥታ ባልሆነ መንገድ መንገድ የሚያውቀውን ፍሬ ነገር ብቻ "ነው በሚል ሲደነግግ "ተገቢ የሆኑትና የሚለው ምስክሮች የሚያስረዱት ፍሬ ነገር ውሳኔ ለሚሰጥበት

ፍሬ ነገር አግባብነት ያለው መሆን እንዳለበት የሚያመለክት ነው ፡፡ ብቻ" የሚለው ቃል ደግሞ ህጉ አግባብነት ያላቸውን ብቻ ለመቀበል መቁረጡና አግባብነት የሌላቸውን ደግሞ ላለመቀበል መወሰኑን ያመለክታል ፡፡" በፍ/ሥ/ሥ/ህጉም በቁጥር 263(1) ላይ የደነገገውም ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ ድንጋጌ ጋር ተመሳሳይ ነው ፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች ምስክሮችን የሚመለከቱ ይሁን እንጂ የማስረጃው ዓይነት ሰነድም ይሁን ሌላ አግባብነት የሌላቸው ማስረጃዎች ለፍ/ቤት አይቀርቡም ፡፡ ለዚህም የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/33 (3) እና የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 138 እና 146 ድንጋጌዎች መመልከት ይቻላል ፡፡

የቀጠለ ...

4.  በሁለተኛ ደረጃም ማስረጃው ውሳኔ ለመስጠት ተገቢነት ቢኖረው እንኳ እንዳይቀርብ የሚያግድ በህግ የተደነገገ ክልከላ ካለ አይቀርብም ።ማስረጃ ሊቀርብ የሚችለው ውሳኔ ሊሰጥበት ለተፈለገው ፍሬ ነገር አግባብነት ስላለው ብቻ ሰይሆን ህግ እንዳይቀርብ ያልከለከለው በመሆኑ ጭምር ነው ። ስለዚህ ህግ እንዳይቀርብ የከለከለው ማስረጃ አግባብነት ቢኖረው እንኳን ሊቀርብ አይችልም ። በዚህም መሰረት የማስረጃ ተቀባይነት በተመለከተ ከላይ ከተገለፁት ሐሳቦች መረዳት የሚቻለው ።

•ማንኛውም ማስረጃ ሊቀርብ የሚችለው ያስረዳዋል ለተባለው ፍሬ ነገር አግባብነት ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ ነው ።

•በተጨማሪም ማስረጃው ሊቀርብ የሚችለው በህግ እንዳይቀርብ ያልተከለከለ እንደሆነ ነው ።

## የቀጠለ ...

5. የማስረጃ ተቀባይነት ጉዳይ ብቸኛ ባይሆንም መሰረታዊ የማስረጃ ህግ ደንብ ነው ለማለት ይቻላል ፡፡ ይህም በተከበሩ ምክንያቶች ነው አግባብነት የሌለው ማስረጃ ሊቀርብ አይገባም የሚባለው የተያዘውን ክርክር ወይም ጭብጥ ለመወሰን ስለማይጠቅም ነው ፡፡ ስለዚህም አግባብነት የሌለውን ማስረጃ እንዳይቀርብ ማገድ የፍ/ቤቱ እና የተከራካሪ ወገኖችን ጊዜና ወጪ ከመቆጠበም በላይ የፍርድ ሂደቱ ሥርዓት ይዞ እንዲጓዝ ያደርጋል ፤ለተያዘው ጭብጥ በማይጠቅሙ ማስረጃዎች ከምችት ምክንያት የውሳኔ አሰጣጥ እንዳይወሳሰብም ያደርጋል፡፡

6. በአገራችን የማስረጃ ተቀባይነትን የሚመለከቱ ደንቦች በተለያዩ ሕጎች ውስጥ ተሰበጣጥረው ይገኛሉ ፡፡ በተግባር እንደሚታየውም በበርካታ ፍ/ሔር እና የወንጀል ጉዳዮች የማስረጃ ተቀባይነት የሚመለከቱ ክርክሮች የሚቀርቡ ሲሆን ፍ/ቤቶች ደግሞ ህጎችን በመመርመር ተገቢውን ብይን መሰጠት ይገባቸዋል ፡፡ መታለፍ የሌለበት መሰረታዊ ነጥብ ግን አግባብነት የሌላቸው ማስረጃዎች ሊቀርቡ አይገባም ህግ አይቀርቡም ሲል የከለከላቸው ማስረጃዎችም ተቀባይነት ሊያገኙ አይገባም ፡፡

## የቀጠለ ......

የዚህ ዝግጅት ማዕከላዊ ነጥብ ማስረጃን መመዘን የሚመለከት መሆኑ ይታወቃል ፡፡ ያም ሆነ ግን የማስረጃ ተቀባይነት ጉዳይ ማስረጃን በመመዘን ጥያቄ ላይ ተጽህኖ የሚያሳድር በመሆኑ መታወቅ ይገባዋል ፡፡ የሚመዘነው ተቀባይነት አለው ተብሎ እንዲቀርብ የተፈቀደ ማስረጃ ብቻ ነው ፡፡ ማስረጃው አግባብነት የሌለው ከሆነ የተያዘውን ጭብጥ በመወሰን ረገድ ፋይዳ ስለሌለው በማስረጃ ምዘና ሂደት ግምት ውስጥ የሚገባ አይደለም ፡፡ህግ ተቀባይነት የለውም በሚል እንዳይቀርብ የከለከለው ማስረጃ ደግሞ ውሳኔ ሊሰጥበት ለተፈለገው ፍሬ ነገር አግባብነት ቢኖረው እንኳን ህግ ሊቀርብ አይገባም በሚል የከለከለው በመሆኑ አይመዘንም ፡፡ ስለዚህ የማስረጃ ምዘና በሚገባ ለማከናወን ተቀባይነት የሌላቸውን (አግባብ ባለመሆናቸው ወይም በመከልከሉ ምክንያት ) ማስረጃዎች አስቀድሞ እንዳይቀርቡ ማስወገድ የማስረጃ ምዘና ሂደትን የሚያቀላጥፍና ከስህተትም የሚጠብቅ በመሆኑ በዚህ ምዕራፍ ቦታ ሊሰጠው በቅቷል በዚህም መሰረት የማስረጃ ተቀባይነት ጥያቄን በሁለት በመክፈል ማለትም

## የቀጠለ ...

- የማስረጃ አግባብነትን እና
- ሌሎች ማስረጃ ተቀባይነት የለውም የሚያሰኙ ደንቦችን በአጭሩ እንመለከታለን

## 3.2. ስለማስረጃ አግባብነት

### 3.2.1. ጽንሰ -ሀሳቡ

ከላይ እንደተገለፀው  የማስረጃ አግባብነት የሚወሰነው በሁለት ፍሬ ነገሮች መካከል በሚኖረው ግንኙነት መነሻ ነው ። እነዚህ ፍሬ ነገሮችም ማስረጃው ይገልፀዋል  የሚባለውና ማስረጃው ያስረዳዋል ወይም ያስተባብለዋል የተበላው ፍሬ ነገር ናቸው ። ከዚህ አንፃር ትኩርት ሊሰጥባቸው የሚገቡ ነጥቦች ፡-

❖የማስረጃው አግባብነት የሚወሰነው  ይህ ማስረጃው ይገለፀዋል የተባለው ፍሬ ነገር ማስረጃው ሊያስረዳው ወይም ሊያስተባብለው ከሚፈልገው ፍሬ ነገር ጋር ያለው ትስስር በነገሮች ኢኮኖማአዊ ግንኙት (Lopical Connection ) ወይም ህግ በፈጠረው  ትስስር ለምሳሌ ህፃኑ የተፀነሰበት ቀን ከዚህ በኋላ ነው ብሎ ለመገመት የተወለደበትን ቀን የሚመለከተው ፍሬ ነገር መነሻ ሊሆን ይችላል ።

❖ማስረጃው ያስረዳዋል ወይም ግምቱ እንዲወስድ ያስችለዋል ወይም ያስተባብለዋል የተባለው ፍሬ ነገር በፍ/ቤት ክርከር ረገድ በጭብጥ የተያዘ ፍሬ ነገር (Fact in issue )ወይም ለዚህ በጭብጥ ለተያዘው ፍሬ ነገር አግባብነት ያለው ሌላ ፍሬ ነገር (another fact relevant top the fact in issue )ሊሆን ይችላል ። (retanlal and dhirajlalp....................)

- የቀጠለ ...

- በማስረጃነት የቀረበው ወይም እንዲቀርብ የሚፈለገው ፍሬ ነገር የሚሰጠው አገልግሎት በጭብጥ የተያዘውን ፍሬ ነገር መኖር ማረጋገጥ ወይም ማስተባበል (Proving or disproving existence or non – existence of fact ) ወይም ይኸው ፍሬ ነገር ስለመኖሩ ወይም ስለአመኖሩ ግምት እንዲወስድ ማስቻል (rendring probable the existence or non existence ) ነው ፡፡

## 3.2.2 የማስረጃ አግባብነት በወንጀል ጉዳዮች

1. በወንጀል ጉዳዮች የሚቀርቡ ማስረጃዎች ውሳኔ ለሚሰጥበት ፍሬ ነገር አግባብነት ሊኖራቸው እንደሚገባ ይህም በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/እንደተደነገገ ቀደም ሲል ተገልጾአል፡፡ የአግባብነት ድንጋጌው ተፈፃሚ የሚሆነውም በዐ/ህግ በኩል ለሚቀርቡ ማስረጃዎች ብቻ ሳይሆን በተከሳሽ በኩል ለሚቀርቡ የመከላከያ ማስረጃዎች ጭምር ነው ፡፡ ሊቀርብ የተፈለገው ማስረጃ ውሳኔ ሊሰጥበት ለተፈለገው ፍሬ ነገር አግባብነት ያለው መሆኑ ወይም አለመሆኑን በሁለት ፍሬ ነገሮች መካከል ባለው ግንኙነት ወይም ትስስር የሚወሰን ሆኖ የዚህን ግንኙነት መኖር ለማረጋገጥ ደግሞ

## የቀጠለ

•በክስ ማመልከቻው ላይ የተገለፀውና ተላላፊ የተባለው የወንጀል ህግ ድንጋጌ ወንጀሉን ያቋቁማሉ በሚል የደነገጋቸው ፍሬ ነገሮች ሊመረመሩ ይገባል ፡፡ በጭብጥ የሚያዘውን ፍሬ ነገር ለማወቅ ይረዱናል ፡፡

•ማስረጃው ይገልፀዋል የተባለውን ፍሬ ነገር ደግሞ ግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች (ዐ/ህጉና ተከሳሹ ) ማስረጃውን ከመስማታቸው በፊት ስለማስረጃው ዓይነትና ይገልፀዋል ስለተባለው ፍሬ ነገር ከሚሰጡት መግለጫ ለመረዳት ይቻላል ፡፡ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/136 እና 142 (2) ፍ/ቤቱ ይህንን መግለጫ ካደመጠ በኋላ ማስረጃውን ከመቀበሉ በፊት በአግባቡ ላይ ሊወሰን ይገባል ፡፡

2. በወንጀል ጉዳይ የማስረጃ አግባብነት ሲወሰን ከጭብጥ ወይም በወንጀል ህጉ ላይ ከተጠቀሰው እና ተከሳሹ ተላለፈ የተባለውን ወንጀል ያቋቁማሉ ተብለው ከተገለፁት ፍሬ ነገሮች እና በክስ ማመልከቻው ላይ ከተጠቀሱት ፍሬ ነገሮች አንፃር የሚታዩ መሆኑ ግልጽ ነው ፡፡ ነገር ግን ሊቀርብ የተፈለገው ማስረጃ የግዴታ ከእነዚህ ፍሬ ነገሮች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ሊኖረው ይገባል ብሎ መደምደም ስህተት ነው ፡፡

## የቀጠለ

የተፈለገው ማስረጃ ከጭብጡ ጋር በቀጥታ ባይገናኝም እንኳን የወንጀሉን አፈፃፀም አካባቢያዊ ሁኔታ የሚያስረዳ ከሆነ አግባብነት ሊኖር ይችላል ። እንደነዚህ ያሉ ቀጥተኛ ሳይሆን ቀጥተኛ ያልሆኑ ማስረጃዎች በተናጠል ሲታዩ ጭብጡን የሚያስረዱ ባይሆኑም ተጠረቃቅመው ሲገናዘቡ ግን ሊያስረዱ ይችላሉ ። ከላይ እንደተመለከተው የማስረጃ አግባብነት የሚለካው በጭብጥነት ከተያዘው ፍሬ ነገር ወይም ለዚህ ፍሬ ነገር አግባብነት አለው ከተባለው ፍሬ ነገር ጋር ካለው አግባብነት ነው የሚባለው ለዚህ ነው ።እንግሊዝና ህንድን በመሳሰሉ ሀገሮችም በወንጀል ጉዳይ ማስረጃ አግባብነት አለው ከሚባልባቸው ምክንያቶች መካከል በጭብጥ ለተያዘው ፍሬ ነገር ወይም ለዚህ ፍሬ ነገር አግባብነት ላለው ፍሬ ነገር ፡-

- አንድ አባል አንድ ክፍል የሆኑ ፍሬ ነገሮች፣
- አጋጣሚ፣መንስኤ ወይም ውጤት የሆኑ ፍሬ ነገሮች፣
- አመቺ ሁኔታዎችን የፈጠሩ ፍሬ ነገሮች፣
- ያነሳሱ፣ ዝግጅነትን ፣የሚያሳዩ እንዲሁም ከድርጊቱ በፊትና በኋላ የታዩ ባህርያት ይገኙበታል ። በእኛ አገርም ተፈፃሚነት ሊኖራቸው ይችላል ።

## 3.2.3. የማስረጃ አግባብነት በፍ/ሐር ጉዳዮች

1. በፍ/ሐር ጉዳዮች የማስረጃ አግባብነትን ለመወሰን ዋነኛው መመዘኛ ማስረጃው ይገልፀዋል በተባለው ፍሬ ነገር እና በጭብጥ በተያዘው ፍሬ ነገር መካከል ያለው ትስስር ወይም ግንኙነት ነው፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በህግ የሚወሰንበት ሁኔታም አለ ህጉ የማስረጃውን አግባብነት የሚወስነውም ፡-

- ሕጉ በፍሬ ነገሮች መካከል ያለውን ትስስር ሊወስን ይችላል ፡፡ የህፃኑ መፀነስ ከመቼ ጀምሮ ነው? የሚለውን ለማስረዳት የተወለደበትን ቀን ማስረዳት ይገባል በሚል በተፀነሰበት እና በተወለደበት ቀን መካከል ትስስር እንዲፈጠር ማለት ነው ፡፡ እንዲሁ ዓይነት ትስስር የሚታይባቸው በርካታ ድንጋጌዎች አሉ ፡፡
- ህጉ የአንድን ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖር ለማስረዳት አግባብነት ያላቸውን የተወሰኑ ፍሬ ነገሮች ብቻ ናቸው በሚል የሚደነግግበት ሁኔታ አለ፡፡ በፍ/ሕ/ቁ 1996 ላይ እንደተመለከተው ማለት ነው ፡፡

• የቀጠለ. . .

• እንዲሁም ህጉ የአንድን ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖር ለማስረዳት አግባብነት የላቸውም በሚል የተወሰኑ ፍሬ ነገሮች ከማስረጃነት ያስወገደበት ሁኔታም ይኖራል ። በፍ/ሕ/ቁ 826፣837፣1163(2)፣1701 ላይ እንደተገለፀው ያለው ማለት ነው ።

2. ማስረጃው ሊገልፀው የፈለገው እና ያስረዳዋል የተባለው ፍሬ ነገር ሊገኝ የሚችለውም የተከራካሪዎቹ  አቤቱታ ጹሑፍን፣ግራ ቀኙ በክርክር ሂደት ከገለፁዋቸው ነገሮችን እና ማስረጃ ሊያቀርቡ ማስረጃው ስለሚገለፀው ፍሬ ነገር የሚሰጡት መግለጫን በመመርመር ነው ።

## 3.3 ማስረጃ ተቀባይነት እንዳይኖረው በህግ ስለሚደነገግበት ሁኔታ

1. የማስረጃ ተቀባይነት መሰረታዊ መርህ የሚከተለው ነው ። ማንኛውም አግባብነት ያለው ማስረጃ በተለይ እንዳይቀርብ በህግ ካልተከለከለ በቀር ተቀባይነት ሊኖረው ይገባል ። በዚህም መሰረት

# የቀጠለ

አግባብነት ያለው ሆኖ ተቀባይነት የሚያጣው ህጉ የከለከለው እንደሆነ ነው ፡፡ በሕንድ እና በእንግሊዝ የማስረጃ ህግ መሰረት ማስረጃ ተቀባይነት ከሚያጣባቸው ሁኔታዎች መካከል ፡-

- የሰሚ ሰሚ ማስረጃ፣
- በግዴታ የተሰጠ የዕምነት ቃል፣
- የምስክር አስተያየት የሚሰጥበት ማስረጃ፣
- ፀባይን የሚመለከት ማስረጃ፣
- የትዳር የስራ ሚስጢርን የሚመለከቱ ማስረጃዎች ይገኙበታል

2. በአገራችን ግን የሰሚ ሰሚ ማስረጃ እና በትዳር ጓደኛ ላይ የሚሰጥ ምስክርነት በማስረጃነት እንዳይቀርብ የሚከላከል ህግ የለም የምስክር አስተያየት የሚሰጥበት ማስረጃን በተመለከተም ምንም እንኳን አይቀርብም በሚል የተደነገገ ነገር ባይኖርም ምስክር የሚቀርበው ፍሬ ነገሮችን ብቻ ለመግለጽ በመሆኑ በተላይ የባለሙያ ማስረጃ ሆኖ እንዲቀርብ ፍ/ቤት የሚያዝዝ ካልሆነ በቀር አይቀርብም ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የህጎቻችን ድንጋጌዎች ሲፈተሸ ፡-

# የቀጠለ

•2003 ላይ ውል በጹሑፍ እንደሆነ ህግ ባዘዘ ጊዜ ውሉን የተሰረቀ ፣የጠፋ፣መሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር ውሉን በምስክር ወይም በህሊና ግምት ማስረዳት አይቻልም በሚል ተደንግጎአል ። ስለዚህ አንድ ውል በጹሑፍ እንዲሆን ህግ ባዘዘ ጊዜ ውሉን ማስረዳት የሚቻለው የጹሑፍ ሰነድን በማቅረብ ነው ጹሑፍ ከሌለ በምስክር ማስረዳት አይቻልም ። በጹሑፍ ውል የተደረገ ከሆነም ውሉ የተሰረቀ ወይም የጠፋ መሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር ምስክር ማቅረብ አይቻልም ። በማስረጃነት የቀረበ የውል ሰነድ ላይ የተገለፀ ፍሬ ነገሮችን ማስረዳት የሚቻለው በሰነዱ ብቻ ነው ።

•ኑዛዜን በተመለከተም በግልጽ ወይም በተናዛዡ ጹሑፍ የተደረገ ኑዛዜ መኖሩንና በኑዛዜው ላይ የሰፈረውን ቃል ማስረዳት የሚቻለው በኑዛዜው ሰነድ ብቻ ነው ቁጥር 896-897

## 2.3.2 ፍሬ ነገሩ (ማስረጃው) እንዳይቀርብ የሚደረግ ክልከላ

1. በኢትዮጵያ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 138 ላይ በህግ በተለይ ካልተፈቀደ በቀር የጥፋተኛነት ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ተከሳሹ በወንጀል ተከስሶ የተቀጣ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ ሊቀርብ እንደማይገባ ተደንግጎአል ፡፡ የቀድሞ የጥፋተኛነት ሪከርድን በሚመለከት የኢትዮጵያ ህግ የወሰደው አቋም ከአንግሎ አሜሪካን የህግ ሥረዓት የማስረጃ ህግ ጋር የሚቀራረብ ስለመሆኑ ይህ ድንጋጌ ማረጋገጫ ነው ፡፡ በዚህም መሰረት የቀድሞው የጥፋተኛነት ሪከርድ ከፍርድ በፊት እንዳይቀርብ የሚከላከለው አንድም አግባብነት ስለሌለው ሲሆን አግባብነት አለው የሚባል ቢሆን እንኳ ከፍርድ በፊት ጥፋተኛ ሆኖ ያለመቆጠርን ህገ መንግስታዊ ድንጋጌ በማፈለስ ዳኞች አሁን የተከሰሰበትንም ወንጀል ፈጽሟል የሚል አቋም እንዳይዙና ማስረጃውን ፍታሐዊ በሆነ ሁኔታ የማመዛዘን አቅማቸው እንዳይደክም ለማድረግ ነው ፡፡

የቀጠለ.

2. ከፍርድ ቤት የቀድሞ ጥፋተኛነትን የሚገልጽ ውሳኔ ሊገልጽ አይገባም የሚለው ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነው ተከሳሹ አሁን የተከሰሰበት ወንጀል ቀደም ሲል ተከስሶ ጥፋተኛ ከተባለበት ወንጀል ጋር ሊኖረው የሚችለውን ተሳሳይነት ወይም ልዩነት ግምት ውስጥ ሳያስገባ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል ። በዚህ መሰረት ቀደም ሲል ጥፋተኛ የተባለበት ወንጀል አሁን ክስ ከቀረበበት ወንጀል ጋር ተመሳሳይም ሆነ የተለያየ ግምት ውስጥ ሳይገባ እንዳይቀርብ መደረግ ይኖርበታል ።

3.የፍ/ሔር ጉዳይ በሚመለከት ግን እንዲህ ዓይነት ክልከላ የለም ። ዋናው ነገር የማስረጃው አግባብነት ነው።በፍ/ሕ/ቁ/ 2149 ላይ በወንጀል መቀጣት ወይም ነፃ መውጣት በፍ/ሔር ረገድ ጥፋት መፈፀሙን ወይም አለመፈፀሙን ለመወሰን ፍ/ቤቱን አያስገድደውም በሚል ተደንግጓል ።

የቀጠለ.

ሊወሰን በዚሁ ጉዳይ በወንጀል በተሰጠው ውሳኔ ሳይገደድ መወሰን እንደሚችል ለመግለጽ ነው ፡፡ ለማጠቃለል በወንጀል ጉዳይ የተሰጠ ውሳኔ አግባብነት ካለው በፍ/ሔር ጉዳይም ሊቀርብ ይችላል ፡፡ ይህ ማለት ግን በወንጀል ተከስሶ ጥፋተኛ መባሉ በፍ/ሔር አጥፍቷል ፣ነፃ ነው መባሉም በፍ/ሔር አላጠፋም የሚል መደምደሚያ ላይ የግዴታ አያደርስም ማስረጃው ግን ይመዝናል ፡፡

**3.3.3. ማስረጃው ከተገኘበት መንገድ አንፃር የሚደረግ ክልከላ**

4. ማስረጃው ከተገኘበት መንገድ አንፃር የተቀባይነት ጥያቄ የሚያስነሳው ከፍ/ቤት ውጪ የተሠጠ የዕምነት ቃልና በዚህ መሰረት የተሰበሰቡ ሌሎች ማስረጃዎች ህጋዊነት አጠያያቂ ሲሆን ነው ፡፡ ከፍ/ቤት ውጪ የተሰጠ የእምነት ቃል አግባብነት እስካለው ድረስ በማስረጃነት ሊቀርብ እንደሚችል ቀደም ሲል ተገልጾአል፡፡ ይህንን ዓይነት ማስረጃ ሲቀርብ ግን በነፃ ፍቃድ የተሰጠ መሆን ይኖርበታል ፡፡ የእምነት ቃሉ በነፃ ፍቃድ የተሰጠ መሆኑ እንደሚጋበው በአስገዳጅነት መቀመጡ ተገቢነቱ ለፍ/ሔር ለወንጀል ጉዳዮች ተፈፃሚነት ቢኖረውም ጉልህ ስፍራ የሚሰጠው ግን በወንጀል ጉዳይ በመሆኑ በዚህ ላይ ትኩረት ተሰጥቶበታል ፡፡

የቀጠለ.

5.የወንጀል ድረጊት መፈፀሙን በማመን ተከሳሹ ለመርማሪ ፖሊስ ወይም በምርመራ ቃሉን ለተቀበለ ፍ/ቤት የሰጠው ቃል በማስረጃነት ሊቀርብ እንደሚችል በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/27(2) ላይ በግልጽ፣በቁጥር 35 ላይ ደግሞ በአነጋገር ተመልክቶአል ። ነገር ግን ለመርማሪው ፖሊስ የተሰጠው የእምነት ቃል በነፃ ፍቃድ የሰጠ መሆን ይኖርበታል ።በዚህም መሰረት የዕምነት ቃሉ ተቀባይነት እንዲኖረው፤-

- ተከሳሹ የዕምነት ቃሉን ለመሰጠት ሊገደድ አይገባም ። ተጽህኖ ወይም ግዴታ እንዳለ የሚያመለክቱት ደግሞ በድብደባ በዛቻ በማስፈራራት፣በመደለል የተስፋ ቃል በመሰጠት በመጠጥ ወይም በአደንዛዥ እጽ አዕዕኖ ቃል እንዲሰጥ በማድረግ የተገኘ ሲሆን ነው ። በእንደዚህ ዓይነት ወይም ኃይል ወይም ዛቻ ወይም መደለል መነሻ የተገኘ የዕምነት ቃል ደግሞ ተቀባይነት የለውም ።

## • የቀጠለ

• ተከሳሹ ቃሉን የሰጠው በነፃ ፍቃድ መሆኑ በቀረበው የዕምነት ቃል ማስረጃ ላይ መጠቀስ አለበት ። ስለዚህ ተከሳሹ ቃል መስጠት ያለመስጠት መብቱ መሆኑ አምኖ በነፃ ፍቃዱ የሚሰጠው ቃል ግን ወደፊት በፍ/ቤቱ በማስረጃነት ሊቀርብበት እንደሚችል የተነጋሪው መሆኑ በእምነት ቃሉ ላይ ተመዝግቦ መገኘት አለበት ። (መዝገቡ ምትኬ ገጽ 48)

6.ከዚህ በተጨማሪ የእምነት ቃሉ በወንጀል ምርመራ ቃል ለመቀበል ሥልጣን ለተሰጠው አካል የተሰጠ መሆን እንዳለበት የሚገልጽ አቋም አለ ። (መዝገቡ ምትኬ ገጽ48-49)። በአንዳንድ የፍ/ቤት ጉዳዮች ውስጥ እንደሚታየው የእምነት ቃል የተሰጠው ምርመራ ለማድረግ በህግ ስልጣን ለተሰጠው አካል ሳይሆን ለቀበሌ ገበሬ ማህበር በሆነ ጊዜ በማስረጃነት እንዲቀርብ ሊደረግ አይገባም ። (የጠ/ፍ/ቤት ወ.ይ.መ.ቁ 3281 ተመልከት) በሌላ በኩል ግን የእምነት ቃሉ የተሰጠው በህግ ቃል ለመቀበል ሥልጣን ላለው አካል እስከሆነ ድረስ (ፖሊስ ፍ/ቤት )የዕምነት ቃሉ ተቀባይነት ለማግኘት በነፃ ፍቃድ ሊሰጥ የሚገባ ሲሆን በነፃ ፍቃድ ሳይገደድ መብቱ ተናግሮት አውቆ ተረድቶ የሰጠ መሆኑ በእምነት ቃሉ በራሱ ላይ መግለጽ ይገባል ።

የቀጠለ . . .

7. ተከሳሽ የዕምነት ቃሉን የሰጠው በነፃ ፍቃዱ አለመሆኑን የማስረዳት መብት እንዳለውም መታወቅ አለበት ከዚህ አንፃር በበርካታ የፍ/ቤት ውሳኔዎች ላይ እንደሚታየው ፡-

- ተከሳሹ ቃሉን ሰጥቶ ወደ ምርመራ ክፍል ሲመለስ በአካሉ ላይ የታየበትን ጉዳት የሚያስረዱ ምስክሮችን በማቅረብ
- በቁጥጥር ስር በዋለበት እና የተከሳሽነት ቃሉን በሚሰጥበት ጊዜ መካከል ያለው ልዩነት
- የተከሳሽነት ቃሉን በተደጋጋሚ የሰጠበትና እየተለዋወጠ የተመዘገበበት ሁኔታ (በአንዳንድ መዝገቦች ላይ እንደሚታየው ተከሳሹ በመጀመሪያ ክዶ ቃሉን ከሰጠ በኋላ መጀመሪያ የሰጠውን ለውጦ የዕምነት ቃል ሰጥቷል በሚል የሚመዘገብበት ሁኔታ አለ ፡፡)

## የቀጠለ . . .

• በፍ/ቤት የዕምነት ቃል ከሰጠ በኋላ ወደ ጣቢያ የተመለሰ ከሆነ በዕምነት ቃሉ በነፃ ፍቃድ ያልተሰጠ ለመሆኑ ጠንካራ ግምት ሊያስድሩ የሚችሉ ፍሬ ነገሮች በመሆናቸው እነዚህን በማስረጃነት በማቅረብ ቃሉ በነፃ ፍቃድ የተሠጠ ነው የሚለውን የከሳሽ ክርክር መስተባበል ይችላል።

8. በወንጀል ጉዳይ ተከሳሹ የዕምነት ቃሉን በነፃ ፍቃዱ መስጠቱ መረጋገጥ አለበት የሚለውን አቋም ህገ መንግስታዊ ድጋፍ ያገኘ ሲሆን በኤ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 19(5)ላይ እንደተገለፀው በማስገደድ የተገኘ የዕምነት ቃል በማስረጃነት ቢቀርብ ተቀባይነት እንደሌለው ተደርጎአል ።

## የቀጠለ

9. ስለዚህ ተቀባይነት የማይኖረው በግዴታ በተፅዕኖ ወይም በማባበል፣ወይም በማታለል የተገኘው የዕምነት ቃል ብቻ ሳይሆን በዚህ የዕምነት ቃል መነሻ የተገኘው ሌላ ማስረጃም ጭምር ነው ።የዕምነት ቃሉን ውድቅ አድርጎ በዚህ የዕምነት ቃል መነሻ የተገኘውን ማስረጃ መቀበል ማለት ዞሮ ዞሮ "የተገኘው ውጤት የተጠቀምንበትን መንገድ ትክክለኛነት ያረጋግጣል ::

# ምዕራፍ 4
## ስለማስረጃ አቀራረብ

### ጠቅለላ

- ፍሬ ነገርን
- ለማስረዳት ወይም ለማስተባበል የሚቀርብ ማስረጃ የተቀባይነትን መስፈርቶች ማሟላት እንደሚገባው ባለፈው ምዕራፍ ውስጥ ተገልጾአል ፡፡ ነገር ግን እንዲቀርብ የተፈለገው ማስረጃ ተቀባይነት አለው መባሉ ብቻውን ማስረጃን የሚመለከቱ ጥያቄዎችን ሁሉ አሟልቶ አይመልስም፡፡ የማስረጃ ተቀባይነት ጥያቄ ምን ዓይነት ማስረጃዎች ሊቀርቡ እንደሚገባና እንደማይገባ ይነግረናል ፡፡ ከዚህ አልፎ ግን ተቀባይነት ያለውን ማስረጃ ማን ሊያቀርብ እንደሚገባ እና እንዴትና መቼ ማቅረብ እንዳለበት አይነግረንም ፡፡ የዚህ ምዕራፍ ዓለማ እነዚህን ጥያቄዎች መመለስ ይሆናል ፡፡

# የቀጠለ . . .

•እነዚህን ጥያቄዎች የሚመለከት ደንቦች በተለያዩ ህጎች ውስጥ ተሰግስገው እናገኛለን ። አንዳንዶቹ በ1952 ዓ/ም በወጣው የፍ/ሔር ህግ ውስጥ (ማን ያቀርበዋል የሚለውን ጥያቄ በተመለከተ )ሌሎች ደግሞ 1954 እና በ1958 ዓ/ም እንደቅደም ተከተላቸው በወጡት የወንጀልና የፍትሐብሔር ሥነ-ሥረዓት ህጎች ውስጥ (ማን ? እንዴትና ? መቼ? የሚሉትን ጥያቄዎች በተመለከተ ) ተሰበጣጥረው እናገኛቸዋለን ።ሌሎች ህጎች ውስጥም ይኖራሉ ።

•በአገራችንም ሆነ በሌሎች አገሮች ህጎች የሚገኙትን የማስረጃ አቀራረብን የሚያመለክቱ ደንቦች ሲቀኙ፣

•እንደ ጉዳዩ ዓይነት ( ወንጀል ወይስ ፍ/ሔር)፣

•እንደ ማስረጃው መንገድ (ምስክር ፣ሰነድ፣ወይስ ሌላ ማስረጃ ) እንዲሁም እንደ ሥነ-ሥረዓት ህጎቻቸው የአወቃቀር ፍልስፍና የአገልግሎ አሜሪካን የህግ ስረዓት ወይስ የአህጉራዊው አውሮፓ የህግ ሥርዓት ) ልዩነት ያሳያሉ።

## የቀጠለ . . .

- የጉዳዩን ዓይነት በተመለከተ በወንጀል ጉዳይ የማስረጃ አቀራረብ ከፍ/ሔር ጉዳይ የማስረጃ አቀራረብ የሚስማማቸው ነጥብ ቢኖርም በበርካታ ሁኔታዎች ልዩነት ያሳያሉ ፡፡ ለምሳሌ ወረድ ብለን እንደምናየው (ተከሳሹ በሰጠው የዕምነት ቃል መሰረት ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልግ የጥፋተኝነት ውሳኔ ካልተሰጠ በቀር ) ማስረጃ የማቅረብና የማስረዳት ሸክሙ ምን ጊዜም ቢሆን የዐቃቤ ህጉ ነው ፡፡ የማስረዳት ሸክም ወደ ተከሳሹ የዞረበት ሁኔታ በመሰረቱ (በፀረ ሙስና እና የማስረጃ ስነ- ሥረዓት አዋጅ ቁጥር 236/93 እንደተሻሻለ ላይ ከሚታዩ በስተቀር )ከከሳሹ ወደ ተከሳሹ የሚዞርበት ሁኔታ የለም፡፡ በፍ/ሔር ግን የማስረዳት ሸክሙ በመሰረቱ የከሳሽ ቢሆንም ወደ ተከሳሹ ሊዞር ይችላል ፡፡

## የቀጠለ . . .

- የማስረጃውን መንገድ ወይም ዓይነት በተመለከተ የማስረጃ አቀራረብና ተያያዥ ጥያቄዎች ከማስረጃው ዓይነት አንፃር የተለዩ ደንቦችን የሚከተሉ ሊሆኑ ይችላሉ ፡፡ ሊቀርቡ የታሰቡት ማስረጃዎች ምስክሮች ፣ሰነዶች ወይም ሌላ ዓይነት መሆናቸው በማስረጃው አቀራረብ ላይ ልዩነት ሊፈጥር ይችላል ፡፡ ምስክር በሆነ ጊዜ ምስክሩ ፍሬ ነገሩን ለማስረዳት ያለው የመገንዘብና የመረዳት ችሎታ ግምት ውስጥ ይገባል ፡፡ ሰነዶችና ኤግዚቢቶች ግን እንዲህ ዓይነት (የአዕምሮ ሁኔታን ፣የአካል ሁኔታን) ተፈላጊውን ፍሬ ነገር ለመረዳትና ለማስረዳት ተፈላጊ የሆነ መመዘኛ አግባብነት ላይኖራቸው ይችላል ፡፡

የቀጠለ

• በሶስተኛ ደረጃም የማስረጃ አቀራረብና የቀረበውን ማስረጃ የመመርመር ጥያቄ (በተከተዩ ምዕራፍ በዝርዝር የሚታይ ይሆናል ) እንደየ ህግ ሥረዓቱ የሚለያይ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። ከማስረጃ አቀራረብ አንፃር የህግ ስረዓቶቹ የአገልግሎ አሜሪካ የህግ ሥረዓት ተከታይ ይሆኑ እንደ እንግሊዝ ፣አሜርካን፣ህንድ ......ወዘተ የመሳሰሉት አገሮች የወንጀል ሥነ-ሥረዓት (Adversarial Procedure ) ከአህጉራዊው አውሮፓ የወንጀል ሥነ-ሥረዓት (Inquisitorial Procedure ) በበርካታ ጉዳዮች የተለያየ ነው ። የፍ/ሔር ሥነ-ሥረዓት አካሄድ አጠቃላይ ባህሪያት በሁለቱም ሥረዓቶች በአብዛኛው ተመሳሳይ ሲሆን በወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ ማስረጃን በተመለከተ መሰረታዊ ልዩነቶች ይንፀባረቃል ።በዚሁ መሰረት

## የቀጠለ

- የመንግስት ሚናን በተመለከተ በአግልግሎ አሜሪካ የወንጀል ሥነ ሥረዓት (Adversarial Procedure )መንግስት የራሱን ክስ ይመረምራል ማስረጃ ያጠናቅራል በችሎት የራሱን ክስ ያቀርበል ማስረጃውን ራሱ አቅርቦ የምረምራል ተከሳሹም እንዲሁ የራሱን ማስረጃ ያቀርባል ማስረጃውንም ራሱ አቅርቦ ይመረምራል ተከሳሹም እንዲሁ የራሱን ማስረጃ ያቀርባል ፣ይመረምራል ፡፡ በአሁጉራዊው አውሮፓ የወንጀል ሥነ ሥረዓት (Inquisitorial Procedure ) መንግስት የራሱንም ሆነ የተከሳሽ ማስረጃዎችን ይመረምራል ፡፡ ክስ ያቀርባል የራሱንም ሆነ የተከሳሹን ማስረጃ ፍ/ቤት ያቀርባል ፣ይመረምራል ውሳኔም ይሰጣል፡፡

## የቀጠለ

- በአንግሎ አሜሪካን የወንጀል ሥነ-ሥረዓት አስተሳሰብ ስለ ወንጀል ጉዳይ ትክክለኛው እውነት ሊገለጥ የሚችለው ሁለቱም ተፎካካሪ ወገኖች እኩል ዕድል አግኝተው ችሎት ባቀረቡአቸው ማስረጃዎች አማካኝነት በሚደረግ ክርክርና ጥያቄ ሲሆን በአህጉራዊው አውሮፓ የወንጀል ሥነ-ሥረዓት አስተሳሰብ ደግሞ እውነት የሚወጣው በችሎት በሚደረግ ክርክር ሳይሆን በወንጀል ምርመራ ሂደት ነው ።ልዩ በሆነ ሁኔታ ሲታይ ደግሞ በአግልግሎ አሜሪካ የወንጀል ሥነ ሥረዓት ደንብ መሰረት ማስረጃ ለችሎት የማቅረብ ግዴታ ፤የቀረቡትን ምስክሮች በችሎት የመጠየቅ ግዴታ የእያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን ሲሆን የምስክሮችን ተራ የመወሰን መብቱም የእያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን ነው ። የተከላካዩ ጠበቃም ሚናው ከፍተኛ ነው ።

የቀጠለ . . .

• በአህጉራዊው አውሮፓ የወንጀል ሥነ ሥረዓት ደንብ መሰረት ደግሞ ማስረጃዎችን የመጥራት ፣የማስቀረብ እና የመጠየቅ እንዲሁም የከሳሽንም ሆነ የተከሳሽን ምስክሮች አቀራረብ ተራ የመወሰን ስራ የዳኛው ነው ፣የጠበቃ ሚናም ውስን ነው ። በዚህም መሰረት የሁለቱም ሥነ-ሥረዓቶች መሰረታዊ ግብ ተመሳሳይ ቢሆንም (ማለትም እውነቱን አንጥሮ በማውጣት አጥፊን ብቻ መቅጣትና ያለጠፋውን በነፃ ማሰናበት ) ወደዚህ ግብ በመድረስ ረገድ የተለያዩ መንገዶችን ይከተላሉ ።

<u>ጥያቄ 4.1</u>

ከላይ ከተገለፀት ሁለት የወንጀል ሥነ ሥረዓት ዓይነቶች አንፃር የኢትዮጰያ የወንጀል ሥነ ሥረዓት ወደ የትኛው ሊመደብ ይችላል ?

ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ፡-

## የቀጠለ . . .

- የማቅረብ ግዴታ “የማስረዳት ሸክም "(Burden of proof) የሚለው ጽንስ ሀሰብ አንዱ ክፍል ነው ።“የማስረዳት ሸክም "በመሰረቱ ሁለት ጽንሰ ሀሳቦችን ያዘለ ሲሆን እነርሱም
- ማስረጃው ለፍ/ቤት የማቅረብ ግዴታ (Burden of Procedure ) እና
- የማሰመን ሸክም (Burden of Persuasion )ናቸው ።

በዚህ ምዕራፍ የምንመለከተው ማስረጃ ለማቅረብ ግዴታን (Burden of Production) ሁለተኛውና የማሳመን ሸክምን (Burden of Persuasion ) ደግሞ ስለማስረጃ ምዘና በሚመለከተው በምዕራፍ 6 ላይ ይገልፃል ።

ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ ማስረጃ ማቅረቢ የሚገባው ማን ነው ? የሚለውን ጥያቄ የሚመለከት ነው ።ይህም በሚከተለው አጠቃላይ መርህ የሚመራ ነው ። ይኸውም ማስረጃ ሊቀርብበት በሚያስፈልገው አንድ ፍሬ ነገር ላይ ማስረጃ ማቅረብ የሚገባውና አስቀድሞም ማስረጃ ማቅረብ የሚገባው ምንም ማስረጃ ሳያቀርብ ቢቀር በክርክሩ ተሸናፊ የሚሆነው ወገን ነው ።

## የቀጠለ . . .

•በወንጀል ጉዳይ ሲሆን የማቅረብ ግዴታ የሚወድቀው ( በእምነት መሰረት ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልግ ውሳኔ የሚሰጥበት ሁኔታ ከሌለ ማለት ነው ) በከሳሽ ዐ/ህግ ላይ ነው ።

ተከሳሹ ማስረጃ ሊያቀርብ የሚገደደው ዐ/ሕጉ ማስረጃ አቅርቦ ካሳመነ ፍርድ ቤቱም በበቂ ሁኔታ አስረድቷል የሚል መደምደሚያ ላይ ከደረ በኋላ ነው ። ወንጀል መቅጫ ሥነ-ሥረዓት ህግ ቁጥር 136(1) ላይ "ዐቃቤ ህግ ክሱን ሲከፍት"የሚለው አገላለጽ፣በቁጥር 141 ላይ " ዐቃቤ ህጉ ማስረጃውን አሰምቶ ከጨረሰ በኋላ "የሚለው ይህንን ያረጋግጣል ። ስለዚህ

*በወንጀል ጉዳይ ማስረጃ በቅድሚያ የማቅረብ ግዴታ ምን ጊዜም በዐቃቤ ህጉ ነው ።

*በወንጀል ጉዳይ የማስረዳት ሸክም ወደ ተከሳሹ የሚዞርበት ሁኔታ የለም በተለይ የማስረዳት ሸክም ወደ ተከሳሹ የሚዞርበት ሁኔታ (በወንጀል ጉዳይ ማለት ነው ) የተደነገገው በፌደራል የፀረ ሙስና ሥነ ሥርዓት የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁጥር 236/93 ላይ ነው ።

## የቀጠለ . . .

- በፍ/ሔር ጉዳይ ማስረጃ በመጀመሪያ በማቅረብ ማስረዳት የሚገባው ምንም ማስረጃ ባያቀርብ ተሸናፊ የሚሆነው ወገን ነው ፡፡ ማስረጃ ማቅረብ የሚገባው ማን ነው የሚለውን በተመለከተም በፍ/ሔር ላይ በየቦታው ተሰበጣጥረው የተቀመጡ ድንጋጌዎች እናገኛለን ለማሰየት ያህል በቁጥር 5፣ 196(2)896 ፣እና 2001 ላይ የተደነገገውን መመልከት ይቻላል ፡፡ በዚህም መሰረት ኑዛዜ አለኝ የሚል ወገን ይህ ኑዛዜ መኖሩና ይዘቱንም በተመለከተ የማስረዳት ሸክም አለበት ፡፡ በተጨማሪም በፍ/ሔር ጉዳይ ማስረጃ የማቅረብ ሸክም ሁል ግዜ ተሸካሚ የሚሆነው ከሳሽ ነው ማለት አይቻልም ፡፡ በዚህም መሰረት

- ከሳሹ ክሱ ለአቀረበው ክስ ተከሳሹ ክሱን አምኖ የማቻቻያ ጥያቄ የአቀረበ እንደሆነ የማቻቻያ ጥያቄውን በሚመለከት (ከሳሹም የማቻቻያ ጥያቄውን የተቀበለው ካልሆነ በቀር) የማስረዳት ሸክሙ የተከሳሹ ይሆናል ።
- ከሳሹ ክሱን ሲያቀርብ ያስረዱልኛል በሚል የተዘረዘራቸው ሰነዶች በተከሳሹ እጅ የሚገኙ መሆናቸውን ጠቅሶ እያለ ተከሳሹ ማስረጃው በእጁ መኖሩን ሳይክድ ነገር ግን ለማቅረብ ፍቃደኛ ካልሆነ የማስረዳት ሸክሙ ወደርሱ ይዞራል ።

## ማስረጃ ስለሚቀርብበት ጊዜና ሁኔታ

## የምስክሮች አቀራረብ

አጠቃላይ በሆነ አገላለጽ በማስረጃነት የሚቀርቡ ምስክሮች የሚሰጡት የምስክርነት ቃል በጭብጥ ለተያዘው ፍሬ ነገር ወይም ለዚህ ፍሬ ነገር አግባብነት ላለው ሌላ ፍሬ ነገር አግባብነት እስከ አለው ድረስ የመመስከር ብቃት አላቸው።

## የቀጠለ . . .

•እንግሊዞ አሜሪካ የህግ ሥረዓት በሚከተሉ አገሮች ውስጥ የተደነገጉት ማስረጃን ብቃት የለውም የሚያሰኙ የተለያዩ ምክንያቶች በአገራችን በቀጥታ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል ማለት አይቻልም ። ዋናው ነገር ምስክሩ ሊመሰክር ስለመጣበት ጉዳይና ስለሚጠየቀው ጥያቄ የመረዳት ችሎታው ነው ። በአዕምሮ መናወጥ፣በአካል በደረሰ ጉዳት የተነሳ ለመረዳት አለመቻል ወይም ተፈላጊውን ፍሬ ነገር ለመግለጽ ባለመቻል (በንግግርም ሆነ በምልክት መግለጽ የማይቻል) ካልሆነ በቀር መመስከር ይችላል። ስለዚህም አዘውትረው በመቀወሚያነት የሚቀርቡት

• ህፃናት ስለሆኑ ሊመሰክሩ አይገባም ፣

•ከተከራካሪ ወገኖች ጋር ፀብ ወይም ዝምድና አላቸው አብረን በግብረ አበርነት የተካሰሰን በመሆኑ ለመመስከር ብቁ አይደሉም የሚሉ መቃወሚያዎች ተቀባይነት የላቸውም ። እነዚህ የመቃወሚያ ነጥቦች ማስረጃን በመመዘን ረገድ የራሳቸው ድርሻ የሚኖራቸው ሲሆን (ይህም በምዕራፍ 7 ላይ ይገለፃሉ) ማስረጃዎች ብቃት የላቸውም ለማስባል ግን አይችሉም ።

## የቀጠለ . . .

• ይህ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ግን በህጋችን የተደነገጉት የሚከተሉት ነጥቦች ትኩረት ሊሰጥባቸው ይገባል ፡፡

• በወንጀል ህግ ላይ እንደተደነገገው አንድ ሰው በፈፀመው ወንጀል ምክንያት የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተላለፈበት ፣ፍርድ ቤቱ ከሚወስነው መደበኛ ቅጣት በተጨማሪ የምስክርነት መብቱን ሊያግደው የሚችል ሲሆን ፍ/ቤቱ እንዲሁ ዓይነት ቅጣትን ሲወሰነ ምስክሩ የመመስከር ብቃቱን ያጣል ፡፡

• በምስክርነት የተቆጠሩት ሰዎች ልዩ እውቀት ያላቸው (ኤክስፐርቶች) ከሆኑ ለምስክርነት ሊቆሙ የሚችሉት ተፈላጊው እውቀት እንዳላቸው ማረጋገጫ ሲገኝ ነው ማረጋገጫው የእውቀት ደረጃቸውን እስከምን ደረጃ ድረስ ሊያረጋግጥ ይገባል ? የሚለው እንደተያዘው ጉዳይ የሚለያይ ሲሆን ነገር ግን ባለሞያው ያስረዳዋል በተባለው ፍሬ ነገሩ ወይም ይገልፀዋል ከተባለው አስተያየት አኳያ የባለሞያነት ማረጋገጫ ከሌለው ምስክር ለመሆን ብቃት የለውም ለማለት ይችላል ፡፡

የቀጠለ . . .

•በወንጀልም ሆነ በፍ/ሔር ምስክሮች መቼ ይቀርባሉ ለሚለው ጥያቄ መልሱ ተመሳሳይ ነው ለማለት ይችላል ። በወንጀል ጉዳይ ዐ/ሕጉ ክስ ሲያቀርብ ያስረዱልኛል የሚላቸውን ምስክሮች ስም ዝርዝር አያይዞ ማቅረብ የሚጠበቅበት ሲሆን በፍ/ሔር ጉዳይም ከሳሽ ክሱን ሲያቀርብ የምስክሮቹን ስም ዝርዝር ከክሱ ጋር አባሪ በሆነ ጹሑፍ ገልፃ ማቅረብ ይገባዋል ። ተከሳሹም እንዲሁ መልሱን ሲያቀርብ ከመልሱ ጋር አባሪ በሆነ ጹሑፍ ያስረዱልኛል የሚላቸውን ምስክሮች ስም ዝርዝር ገለፃ ማቅረብ አለበት ። (የወንጀል መቅጫ ህግ ሥነ ሥረዓት ቁጥር 124፣የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 222፣223፣234፣) በዚህም መሰረት በህግ ተፈቀደ ልዩ ሁኔታ ካልሆነ በቀር የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 256(1)እና የወ/መ/ሥ/ሕ/ቁ 143)በመጀመሪያ ዝርዝራቸው ለፍ/ቤቱ ገቢ ያልተደረ ምስክሮች ሊቀርቡ አይገባም ለማጠቃለል ጉዳዩ ወንጀልም ሆነ ፍ/ሔር፣

•ዝርዝሩ ማስረጃ ከመሰማቱ በፊት ለፍርድ ቤቱ ሊቀርብ ይገባል ፤

•ነገሩ ሲሰማ (ማለትም ማስረጃ ሊሰማ በተቀጠረበት ቀን ) ግራ ቀኙ ለቆጠሯቻ ምስክሮች መጥሪያ አውጥተው አድርሰው አቅርበው ማሰማት ይገባቸዋል ።

## የቀጠለ . . .

•መጥሪያ ደርሶአቸው ያልቀረቡ ምስክሮች ፍርድ ቤቱ በሚሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ተገድደው ቀርበው የምስክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡ ይደረጋል፣

•በዝርዝር ያልተጠቀሱ ምስክሮች እንዲቀርቡ እንደመብት መጠየቅ የማይቻል ሲሆን ሊፈቀድ የሚቻለው መቅረቡ ለትክክለኛ ፍርድ አስፈላጊ መሆኑን ፍርድ ቤቱ አምኖ የፈቀደ እንደሆነ ነው ፡፡

## የሰነዶች አግዚቢቶች አቀራረብ

7.1.በተለመደው የአገራችን የፍርድ ቤቶች አሰራር ሰነዶችና ማስረጃ የሚሆኑ ሌሎች ነገሮች ለፍ/ቤት የሚቀርቡት ምስክሮች ከተሰሙ በኋላ መሆኑ ይታወቃል፡፡ (የወንጀልን ጉዳይ በሚመለከት ማለት ነው ) ዐ/ሕግ ስለሰነድ ማስረጃ ሲጠየቅ ምስክሮች ከተሰሙ በኋላ እንደሚያቀርብ የሚገልጽ ሲሆን ስለኢግዚቢት ማስረጃ ሲጠየቅ ደግሞ "ፖሊስ ጋ ስለሚገኙ እንዳያቀርባቸው ለፖሊስ ትዕዛዝ ይሰጥልኝ "በሚል እያሳሰበ ፖሊስ በታዘዘው መሰረት ኢግዚቢቶችን አላቀረበም እየተባለ ተደጋጋሚ ትዕዛዝ የሚሰጥበት ሁኔታ ይሰተዋላል፡፡ ይህ ትክክለኛ የማስረጃ አቀራረብ ነውን ? የሚለውን ደግሞ ከህጉ ጋር በማገናዘብ መመርመር ያስፈልጋል ፡፡

## የቀጠለ . . .

7.2. በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥረዓት ቁጥር 124 ላይ እንደተደነገገው ነገሩ በሚሰማበት ቀን መረጃዎች (ኤግዚቪቶች)ሁሉ ፍ/ቤት መቅረብ ይገባቸዋል ፡፡ ከየት ነው የሚቀርቡት ?ለሚለው ደግሞ ቁጥር 97 መልስ ይሰጣል ፡፡ ቁጥር 97 መረጃዎች (ኤግዚቪቶች )እና የተከሳሽነት እና የምስክር ቃሎች ፍርድ ቤት መዝገብ ቤት ቀርበው መዝገብ ቤቱ ተርክቦ ቁጥርና ምልክት እንዲሚያደርግባቸው ከዚያም በፍ/ቤት መዝገብ ቤት በተጠበቀ ስፍራ እንደሚጠበቁ የሚወጡትም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ብቻ እንደሆነ ይገልፃል ፡፡ እነዚህ መረጃዎች የተሰጣቸውን ቁጥርም በወንጀል መዝገቡ ውስጥ እንደሚመዘገብ ቁጥር 97(1)(ሀ) ይመለከታል ፡፡ በዚሁ መሰረት

- ሰነዶች እጅግ ቢዘገይ የክስ ማመልከቻው ፍ/ቤት ሲቀርብ አብረው መቅረብና መዝገብ ቤት መቀመጥ የሚገባቸው ሲሆን ለማስረጃነት ሲፈለጉም በዳኞች ትዕዛዝ ወጪ ያደርጋሉ ፡፡
- ኢግዚቪቶችም አስቀድመው ፍ/ቤት ቀርበው በተጠበቀ ስፍራ መቀመጥ የሚገባቸው ሲሆን ለማስረጃነት ሲፈልጉም የሚቀርቡት

ከዚሁ ነው ፡፡

## የቀጠለ . . .

7.3. በፍ/ሔር ጉዳይም ተከራካሪ ወገኖች ይጠቅሙኛል ወይም ያስረዱልኛል የሚሉትን ሰነድ ከአቤቱታዎቻቸው ጋር አያይዘው ማቅረብ ይገባቸዋል ። የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 137(1)፣223(1)(ለ)፣234(1)። በልዩ ሁኔታ ፍ/ቤት እንዲቀርቡ ካልፈቀደ በስተቀር ቁጥር 256(1)፣145(1)፣115፣119፣264 ዘግይተው ሊቀርቡ አይችሉም ማስረጃው በእጅ የማይገኝ ከሆነ በትዕዛዝ እንዲቀርብ ፍ/ቤቱን መጠየቅ የሚቻል ሲሆን(ቁጥር 145) ነገር ግን ፍ/ቤቱ ተከሳሹ መጥሪያ ከመስጠቱ በፊት ይህ ማስረጃ እንዲቀርብ ትዕዛዝ መስጠት ይገባዋል ። በትዕዛዝ እንዲቀርብለት የጠየቀው ተከሳሹ ከሆነም መልሱን ከመስጠቱ በፊት ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ሰጥቶ ማስረጃውን እንዲያስቀርብለት መጠየቅ ይኖርበታል ።ፍ/ቤቱም በዚሁ መሰረት ማስረጃው እንዲቀርብ ትዕዛዝ እንደሚሰጥ ይጠበቃል ።

# ምዕራፍ 5
# ምስክሮችን ስለመመርመር

## 5.1 ጠቅላላ

• ባለፈው ምዕራፍ ውስጥ ውሳኔ ለመስጠት አስፈላጊ በሆነው ፍሬ ነገር ላይ ሊያስረዱ የሚችሉ ማስረጃዎች ፍ/ቤት የሚቀርቡበት ሁኔታ ተገልጾአል። ማስረጃን ማን እንዴትና መቼ ማቅረብ እንደሚገባውም ተጠቅሶአል ። በዚህ ምዕራፍ ደግሞ የቀረቡት ማስረጃዎች እንዴት እንደሚመረመሩ ማለትም ተፈላጊውን ፍሬ ነገር ለፍ/ቤቱ እንዴት እንደሚያስረዱ ይገልፃል ። በመሰረቱ ፍሬ ነገርን ለማስረዳት የሚቀርቡት ምስክሮች ብቻ ሳይሆኑ ሰነዶች እና ሌሎች ገላጭ ማስረጃዎች ጭምር ቢሆኑም ነገር ግን ምስክሮች የሚመረምሩበት ሥረዓት ለየት ያለ በመሆኑ በምስክሮች ቃል አቀባበል ሁኔታ ላይ ይህ ምዕራፍ እንዲያተኮር ተደርጓአል ። ምስክሮች በማስረጃነት ፍ/ቤት ሲቀርቡ ማስረጃ ተብሎ የሚቆጠረው በችሎት የሰጡት ቃል በመሆኑና በውሳኔ ጊዜም የሚመረመረው ይኸው ምስክሮች የሰጡት ቃል በመሆኑ የምስክሮች ቃል አቀባባል መሰረታዊ በመሆኑ ትኩረት ሊሰጠው ችሎአል ።

## የቀጠለ . . .

- ወደ ዋናው ጉዳይ ከመግባቱ በፊት ግን የሚከተሉት ሁለት ነጥቦች ትኩረት ሊሰጥባቸው ይገባል ፡፡
- በወንጀልም ሆነ በፍ/ሔር ጉዳይ ምስክሮች የሚመረምሩበት ሁኔታ የተወሰነ ልዩነት ቢኖረውም በአብዛኛው ተመሳሳይ ነው ለማለት ይችላሉ፡፡
- በኢትዮጵያ የወንጀልም ሆነ የፍትብሔር ሥነ ሥረዓት ህጎች መሰረት ምስክሮችን ችሎት የማቅረብ፣የቀረበ ምስክሮች የሚያስረዱትን ፍሬ ነገር የማስመዘገብ እና የመመርመር ወይም የመጠየቅ መብቱም ግዴታዊም የተከራካሪ ወገኖች ነው ፡፡ ፍ/ቤቱ አስፈላጊ በሆነ ግዜ በራሱ አነሳሽነት ማስረጃ የማስቀረብና ራሱም ሆነ ተከራካሪ ወገኖች ያቀርቡአቸውን ምስክሮች የመጠየቅ ሥልጣን ቢኖረውም ዋነኛው ግዴታ የሚወደቀው ግን በተከራካሪ ወገኖች ላይ ነው ፡፡ ስለዚህ የኢትዮጵያ የወንጀል ሥነ ሥረዓት ህግ የአንግሎ አሜሪካን የወንጀል ሥነ ሥረዓት አካሄድ (Adversarial Procedure )የሚከተል ነው ማለት ይችላል ፡፡

## 5.2. ምስክሮች በተከራካሪ ወገኖች ፊት ቀርበው መመስከር የሚገባቸው ስለመሆኑ

• ምስክሮች ቃላቸውን የሚሰጡበትና የሚመረመሩት ተከራካሪ ወገኖች ባሉበት መሆኑ የታወቀ ነው ።ጉዳዩ ወንጀልም ሆነ ፍ/ሔር በመሰረቱ ልዩነት የለውም ። ተከሳሹ በሌለበት ጉዳዩ እንዲሰማ የታዘዘ በሆነ ጊዜ (የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 70(ሀ) እና የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/161 ይመለከታል)ምስክሮች ተከሳሽ በሌለበት ሊቀርቡ የሚችሉ ቢሆንም ነገር ግን ችሎት ቀርበው ቃላቸውን መሰጠት ይኖርባቸዋል ። ይህ የሆነበት ምክንያቱም አንድ ምስክር የሰጠው የምስክርነት ቃል እውነተኛነት ወይም ሐሰተኛነቱ እርግጠኛነቱ ወይም አጠራጣሪነቱ የሚፈተነው በሚቀርብለት መስቀለኛ ጥያቄ በመሆኑ ነው (የኤ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 19(4) ። ስለዚህ ምስክር ተከራካሪ ወገን ባለበት ቀርቦ ማነነቱን አረጋግጦ የምስክርነት ቃሉን ሊሰጥ ይገባዋል።

## የቀጠለ. . .

- በሌላ በኩል ደግሞ በወንጀል ጉዳይ በዐ/ሕግ በኩል የተቆጠረ ምስክር በተከሳሹ ፊት ቀርቦ የምስክርነት ቃሉን መስጠቱ ወይም የቀረበ ቢሆን እንኳ ማንነቱንና አድራሻውን በተከሳሹ ፊት መግለጹ ለደህንነቱ አስፈላጊ ሁኔታ የሚፈጠርበት ቢሆንስ? ተከሳሹ ሳያየውና ማንነቱንና አድራሻውን ሳይገልጽ የምስክርነት ቃሉን እንዲሰጥ ሊደረግ ይችላልን ? የሚለው ጥያቄ ሲነሳ ይችላል ፡፡በዚህ ጭብጥ ላይ ሌሎች አገሮች አዲስ አሰራር እየተከተሉ ይገኛሉ ፡፡ በዚህም መሰረት በእንግሊዝ ህግ የዐ/ሕግ ምስክር ማንነቱን በግልጽ ሳይናገር ወይም በአካል ችሎት ቀርቦ ሳይታይ የምስክርነት ቃሉን የሚሰጥበት ሁኔታ ያለ ሲሆን ይህም ፡-

*ችሎት ቀርቦ ማንነቱንና አድራሻውን ተከሳሹ እየሰማ ከመናገር ይልቅ በጹሑፍ ለፍ/ቤቱ ለመግለጽ ፣ወይም

•

• የቀጠለ. . .

•የተለየ ሁኔታ ደግሞ በችሎት ሳይገኝ የምስክርነት ቃሉን ሊሰጥ ይችላል

•እንዲህ ዓይነት ምስክርነት እንዲሰጥ የመወሰን ስልጣኑ የፍ/ቤቱ ሆኖ ነገር ግን ትዕዛዝ ከመስጠቱ በፊት

•ምስክሩ ተጫባጭ የሆነ ስጋት ያለበት መሆኑ

•ምስክሩ የሚሰጠው ቃል ለጉዳዩ አወሳሰን አግባብነት ያለውና የምስክርነት ቃሉን ሳይሰጥ ቢቀር ፍትህን የሚያዛባ መሆኑን፣እና

•ምስክሩ ችሎት ሳይቀርብ ምስክርነቱን ቢሰጥ በተከሳሹ ላይ ከባድ ተጽህኖ የሚያሳድር አለመሆኑን ማረጋገጥ አለበት

## 5.3 ምስክሮች ስለሚመረምሩበት ሥነ ሥረዓት

### 5.3.1. ጭብጥን ስለመያዝ

በወንጀልም ሆነ በፍ/ሔር ጉዳይ በማስረጃነት የሚቀርቡ ማናቸውም ማስረጃ ውሳኔ ስለሚሰጥበት ጉዳይ አግባብነት ሊኖረው እንደሚገባ በምዕራፍ 3 ላይ ተገልጾአል።

• የቀጠለ. . .

• ማስረጃው አግባብነት እንዳለው ለመወሰን ደግሞ አስቀድሞ ውሳኔ የሚሰጥበት ተፈላጊውና አከራካሪው ፍሬ ነገር ተለይቶ ሊታወቅ ይገባል ፡፡ ይህ ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባው አከራካሪውና ይቀርባል የተባለው ማስረጃ ጭብጥ በመባል የሚታወቅ ሲሆን ማስረጃው ከመቅረቡና ከመሰማቱ በፊት አስቀድሞ መታወቅ አለበት ፡፡ ይህ በወንጀልም ሆነ በፍ/ሔር ጉዳይ መፈፀም ያለበት ሲሆን የጭብጥ አያያዝ መሰረቶችም በዚያው በምዕራፍ 3 ላይ ተመልተዋል ፡፡

ሀ )ዋና ጥያቄ

1. ዋና ጥያቄ የሚባለው ምስክሩን የአቀረበው ወገን በመጀመሪያ የሚያቀርበው ጥያቄ ነው ፡፡ ዓለማውም ምስክሩ የጠራው ወገን በክርክሩ ያለውን አቋም እንዲደግፍላት ማድረግ ሲሆን ምስከሩም በጭብጥ ስለተያዘው ፍሬ ነገር በቀጥታ ሆነ ቀጥታ ባልሆነ መንገድ የሚያውቀውን ያስረዳል ፡፡

## የቀጠለ. . .

## ከዚህ እንፃር

- በምስክር ምርመራ ሂደት ዋና ጥያቄ ወይም መሰረታዊ ነው ዋና ጥያቄ ከሌለ መስቀልኛ ሆነ ድጋሚ ጥያቄ አይኖርም ፡፡
- በዋና ጥያቄ ላይ የመምራት ጥያቄ መጠየቅ አይቻልም
- እንዲሁም ምስክር አቅራቢው በመሰረቱ የራሱን ምስክር ዋና ጥያቄ ሲጠይቅ የማስተባባል ጥያቄ ሊጠይቀው አይገባም ፡፡

## 2.የመምራት ጥያቄ

- ጥያቄ አቅራቢው እንዲመለስለት የሚፈልገውን መልስ የሚጠቁም ወይም አስቀድሞ ምስክሩ መልስ ሰጥቶበት ያላረጋገጠውን ፍሬ ነገር እንደተረጋገጠ በመቁጠር በዚህ በመመስረት የሚቀርብ ጥያቄ ለማመልከት ነው ፡፡

## የቀጠለ....

## በዋና ጥያቄ ላይ የመምራት ጥያቄ እንዳይጠየቅ የተከለከለውም

- ምስክር አቅራቢው ወገን ምስክሩ ደግፎት ይመሰክራል ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን እንዲመስለት የሚፈልገውን መልስ በጥያቄ መልኩ ለምስክሩ ማቀበል የለበትም፡፡
- ምስክሩ ያለረጋገጠውን ፍሬ ነገር እንደተረጋገጠ በመቁጠር ወይም በማስመሰል በማለፍ ወሳኝ የሆነ ፍሬ ነገር መኖር አለመኖሩ ሳይታወቅ መታለፍና ስህተት መፍጠር የለበትም
- (Hermann P-z)በሚባሉ ምክንያቶች ነው ፡፡

3.የማስተባበያ ጥያቄ መጠየቅ በመሰረቱ የተከለከለውም ምስክር አቅራቢው ወገን ምስክሩን ያቀረበው ያስረዳልኛል በሚል በመሆኑና ያቀረበው ምስከር ደግፎት እንዲመሰክር የሚጠበቅ ሲሆን ራሱ ያቀረበው ምስክር የሰጠው መልስ ትክክለኛ አለመሆኑን ወይም የሚያጠራጥር መሆኑን ወይም አስቀድሞ ከሰጠው ቃል ጋር የሚጋጭ መሆኑን ያሚያመለከት ጥያቄ መጠየቅ ምስከሩ ሲቀርብ ከተገመተው ግምት ጋር የሚጋጭ ነው እውነት ይናገራል ብሎ ያቀረበውን ምስክር ሐሰተኛ መሆኑን እንዲገልጽ ማድረግ እርስ በርሱ የሚጋጭ ነው ፡፡ ሆኖም የማስተባባል ጥያቄ በዋና ጥያቄ ላይ የሚቀርብበት ሁኔታ ይኖራል ፡፡ይኸውም

• **የቀጠለ. . .**

• ምስክሩ ለመመስከር ፍቃደኛ ያልሆነበት ሁኔታ ወይም

• አስጠቂ (hostile ) በሆነ ጊዜ ነው ፡፡

የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 145 ተፈፃሚነት የሚኖረውን በዚህ ሁኔታ ነው ፡፡ የፀረ ሙስና ሥነ ሥረዓትና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁጥር 236/1993 አንቀጽ 40 ላይም ይህ ተደንግጓል፡፡

እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሲፈጠር ምስክሩ መጀመሪያ ሲጠየቅ በሰጠው መልስና በማስተባባያ ጥያቄ ጊዜ በሰጠው መልስ መካከል ልዩነት ቢፈጠር የትኛው ተቀባይነት ይኖረዋል ?የሚለውን በማስረጃ ምዘና ወቅት የሚታይ ይሆናል (ምዕራፍ 7 ተመልከት )፡፡

## ለ) መስቀለኛ ጥያቄ

1. ምስክሩ የአቀረበው ወገን ዋና ጥያቄ ጠይቆት እንዳአበቃ ሌላኛው ወገን የሚያቀርበው ጥያቄ ነው ዓላማዎቹም

• ምስክሩ ለዋና ጥያቄ በሰጠው መልስ ውስጥ ሐሰተኛ ፣የማይታመን ወይም አጠራጣሪ ቃል መኖሩን መለየት፣

• እንዲሁም ከዚሁ ምስክር ላይ መስቀለኛ ጥያቄ ጠያቂው ሌሎች ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን ለማግኘት ማስቻል ናቸው ፡፡

## የቀጠለ . . .

2.መስቀለኛ ጥያቄን በተመለከተ የሚከተሉት ትኩረት ሊሰጥባቸው ይገባል ።

- መስቀለኛ ጥያቄ ዋነኛ ዓለማው በዋና ጥያቄ ላይ የተሰጠውን መልስ ሀሰተኛነት አጠራጣሪነት ወይም የማይታመን መሆኑን ማሳየት በመሆኑ የዋና ጥያቄ መኖርን ግድ ይላል ። ምስክር አቅራቢው የራሱን ምስክር አልጠየቀውም ፣አልፈለገውም ያለ እንደሆኑ መስቀለኛ ጥያቄ አይቀርብም፣
- በመስቀለኛ ጥያቄ ጊዜ የመምራት ጥያቄ መጠየቅ ይቻላል ።
- የመስቀለኛ ጥያቄ አግባብነት የሚለካው በዋና ጥያቄ ጊዜ ከተጠየቀ ጥያቄ ሳይሆን ለጥያቄው ከተሰጠው መልስ አንፃርና ።

## ሐ) ድጋሚ ጥያቄ

- ምስክሩን የአቀረበው ወገን ምስክሩ መስቀለኛ ጥያቄ ተጠይቆ ከአበቃ በኋላ የራሱን ምስክር ለሁለተኛ ጊዜ የሚጠይቀው ጥያቄ ነው ። ድጋሚ የተባለውም ምስክር አቅራቢው ለሁለተኛ ጊዜ ምስክሩን ስለሚጠይቀው ነው ። ዓላማውም በመስቀለኛ ጥያቄ የተነሳውን ነገር ለማጣራት ነው ። ድጋሚ ጥያቄ በተመለከተም
- መስቀለኛ ጥያቄ ያልተጠየቀ ከሆነ ድጋሚ ጥያቄ ሊቀርብ አይገባም
- ለመስቀለኛ ጥያቄ ምስክሩ የሰጠው መልስ ማጣራትን ብቻ የሚመለከት ነው ።

## ክፍል ሶስት

## ማስረጃን ስለመመዘን

## ምዕራፍ 6

## የማስረጃ አስረጅነት መመዘኛ (ደረጃ)

### 6.1 ጠቅላላ

1. የሚቀርበው ማስረጃ ሊያስረዳው ወይም ሊያስተባብለው ለተፈለገው ፍሬ ነገር አግባብነት ያለው መሆኑ፣እንዲሁም በህግ እንዳይቀርብ ክልከላ ያልተደረገበት መሆኑ ብቻውን ተፈላጊውን ፍሬ ነገር አስረድቷል ወይም አስተባብሏል ለማለት አያስችልም ። አግባብነት ያለው ማስረጃ ሊያስረዳ ከተፈለገ ፍሬ ነገር ጋር ግንኙነት ሊኖረው እንደሚችል የታወቀ ነው ምክንያቱም ምንም አግባብነት የሌለው ማስረጃ አስቀድሞም አይቀርብም ይህ ማለት ግን ማስረጃው የተፈለገውን ፍሬ ነገር መኖር አስረድቷል ወይም አስተባብሏል ማለት አይደለም ።ከተፈላጊው ፍሬ ነገር ጋር የደበዘዘ ግንኙነት ያለው ማስረጃ እንደሚቀርብ ሁሉ ግንኙነቱ ምን ቢወፍር ደግሞ መቶ በመቶ በርግጠኝነት ያስረዳዋል ወይም ያረጋግጠዋል ለማለት አይቻልም ።

## የቀጠለ . . .

ከዚህ አንፃር የቀረበው ማስረጃ ከተፈላጊው ፍሬ ነገር ጋር ያለው ግንኙነት እስከምን ድረስ ነው ?ሊያስረዳው የቀረበውን ፍሬ ነገር አስረድቷል ወይስ አላስረዳም? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ማስረጃን መመዘን አስፈላጊ ነው ።

2. የቀረበው ማስረጃ ተፈላጊውን ፍሬ ነገር አስረድቷል ወይስ አላስረዳም ? የሚለው ጥያቄ በማናቸውም በፍ/ቤት ለተያዘና ማስረጃም ለቀረበበት ጉዳይ አግባብነት አለው

፡ ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ማስረጃን ከመመርመር አልፎ ከተፈላጊው ፍሬ ነገር አንፃር ማገናዘብ ይጠይቃል ። በተጨማሪም ማስረጃው ሲመዘን የሚደርስበት መደምደሚያ አስረድቷል ወይም አላስረዳም የሚል ከመሆኑ አንፃር ማስረጃው አስረድቷል ለማለት የሚቻለው ምን ሁኔታዎችን ሲያሟላ ነው ? የሚለውም ወሳኝ ነጥብ ነው ። ይህ ማስረጃው ተፈላጊውን ፍሬ ነገር አስረደቷል የምንልበት መስመር ወይም ደረጃ የአስረጂነት መመዘኛ (Standard of proof) ይባላል ። ማስረጃው አስረድቷል ወይም አላስረዳም ለማለት የሆነ መመዘኛ አስቀድሞ መወሰን ያስፈልጋል ።

## የቀጠለ. . .

3..የአስረጅነት ደረጃ ወይም መመዘኛ የሚባለውም ይህንን ጽንሰ ሀሰብ የሚመለከተው ነው አስረጂነት መመዘኛ (Standard of proof) "ከዚህ አንፃር ሲታይ የሚኖረው ትክክለኛ ፍቺ " ከሳሽ (በወንጀል ጉዳይ ከሆነ ዐ/ህጉ )ረቺ ለመሆን እንዲያስችለው በክሱ መስማት ሂደት ሊያቀርብ የሚገባው የማስረጃ መጠን ነው በዚህም መሰረት

- የአስረጂነት መመዘኛ ከሳሽ አሸናፊ ለመሆን ወይም ፍ/ቤቱን ለማሰመን የሚያስቾለውን የማስረጃ መጠን የሚመለከት ነው ።
- የ"ማስረጃ" መጠን ሲባል ግን በቁጥር ደረጃን ለመግለጽ ሳይሆን (ማለትም ይህንን ያህል ምስከር ፤ይህንን ያህል ገጽ ሰነድ በሚል ሳይሆን የማስረጃውን ጥራት ወይም የማስረዳት ብቃት ደረጃ ለማለት ነው ።
- ይህንን"መጠን "የአሟላ ከሳሽ አሸናፊ ወይም አስረድቷል ሲባል ካላሟላ ግን አስረድቷል አይበልም።

4..የአስረጅነት መመዘኛ በሚመለከት በህግ የሚወሰደው አቋም እንደ ሀገሩ የህግ ሥረዓት እና እንደ ጉዳይ ዓይነት የሚለያይ ነው ። ማለትም የአንግሎ አሜሪካን የህግ ሥረዓት ተከታይ አገሮች ማስረጃን አስረድቷል የሚሉበት መመዘኛ ከአህጉራዊው አውሮፓ የህግ ሥረዓት ተከታይ አገሮች የአስረጅነት ደረጃ ወይም መመዘኛ

የሚለይ ሲሆን እንዲሁም ይኸው የአንግሎ አሜሪካ የህግ ሥረዓት የአስረጅነት መመዘኛ እንደ ጉዳይ ወንጀል ፍ/ሔር መሆን የተለየ ነው ። በዚህም መሰረት በዚህ ምዕራፍ ተከታይ ክፍሎች

- ማስረጃ አስረድቷል ለማለት ተፈላጊው የአስረጅነት ደረጃ ወይም መመዘኛ በሁለት የህግ ስረዓቶች ስላለው ገጽታ እና
- የማስረጃ አስረጇነት መመዘኛ በኢትዮጵያ ህግ ያለው ገጽታ ይገለፃል።

## የቀጠለ . . .

### 6.2. የማስረጃ አስረጂነት መመዘኛ በሚመለከት የሌሎች አገሮች አቀራረብ ፡፡

### 6.2.1. የእንግሎ አሜሪካ የህግ ሥረዓት (COMMON LAW)

በእንግሎ አሜሪካ የህግ ሥረዓት ተከታይ አገሮች የማስረጃ አስረጂነት መመዘኛ ለፍ/ሔር ለወንጀል ጉዳዮች ተመሳሳይ አይደለም ፡፡ የአሜሪካንን(ዩናይትድ ስቴትስ ) የማስረጃ ህግ ወስደን ጉዳዩን ብንመርምር ሶስት ዓይነት የአስረጂነት መመዘኛዎች እንዳሉ መረዳት ይችላል ፡፡ እነዚህም

- ከምክንያቲዊ ጥርጥሬ በላይ የማስረዳት መመዘኛ ለወንጀል ጉዳዮች የሚያገለግል (Beyond reasobable doubt standard )
- ግልጽና አሳማኝ በሆነ ሁኔታ የማስረጃ መመዘኛ (Clear andi Convincing evidence standard )ለተወሰኑ የፍ/ሔር ጉዳዮች የሚያገለግል ፡፡
- በተሻለ ሁኔታ ማሰመን የማስረዳት መመዘኛ (preponderance of evidence ) ለአብዛኛው የፍ/ሔር ጉዳዮች የሚያገለግል መመዘኛ ናቸው ፡፡

## የቀጠለ. . .

## ሀ) በወንጀል ጉዳይ የአስረጂነት ደረጃ (መመዘኛ )

1.በአንግሎ አሜሪካ የህግ ሥረዓት ተከታይ አገሮች በወንጀል ጉዳይ የአስረጅነት መመዘኛው "ከምክንያታዊ ጥርጥሬ በላይ " ማስረዳት ነው ፡፡

•በወንጀል ጉዳይ ከሳሽ ዐ/ሕግ ተከሳሽ የተከሰሰበትን ወንጀል ስለመፈፀሙ ምክንያታዊ ጥርጥሬ በማያስነሳ ሁኔታ የማስረዳትና ፍ/ቤቱን (በአብዛኛው ከህዝብ መካከል የተመረጡ ዳኞች ነው በዚህ ላይ የሚወሰኑት )ማሳመን ይጠበቅበታል ፡፡ ምክንያታዊ ጥርጥሬ ሲባል "ጉዳዩን የሚለከቱ ዳኞች" በዕለት ተዕለት የኑሮ ሂደት ውስጥ ወሳኝ በሆነ ጉዳዮች ላይ የሚከሰትና በውሳኔዎች ላይ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ተፅዕኖ ሊያስድር የሚችል ጥርጣሬ (Retanlal and Dhirajlal pp.31-31)ከዚህ አንፃር ዐ/ሕግ በወንጀል የተከሰሰ ሰው የተከሰሰበትን ድርጊት ስለመፈፀሙ ምክንያታዊ ጥርጣሬ በማያስነሳ ሁኔታ ማስረዳት አለበት ሲባል ለዐ/ሕጉን ማስረጃ መሰረት በማድረግ ተከሳሹ ድርጊቱን ፈጽሟል ወይም አልፈፀመም ብለው ጥርጣሬ እንዲያደርባቸው የሚያደርግ ሁኔታ ነው ፡፡

–

## የቀጠለ . . .

<u>ስለዚህም</u>

- ጥርጣሬው ምክንያታዊ ሊሆን ይገባል ፡፡
- የጥርጣሬው ምንጭም የዐ/ህጉ ማስረጃ ወይም የተከሳሽ የመከለከያ ማስረጃ የፈጠረው ሊሆን ይችላል ፡፡
- ምክንያታዊ ጥርጣሬ መኖር አለመኖሩ ላይ ውሳኔ ለመስጠት መነሻው ምክንያትን መሰረት ያደረገ ጥርጣሬ አለ የሚባለው ከመደበኛ ባለሞያ ዳኞች አመለካከት አንፃር ሳይሆን የሚላከው ተራ ሰው በኑሮ ልማድ ካለው አመለካከት በመነሳት ነው ፡፡ ከህዝብ መካከል የተመረጡ ዳኞች በዚህ ረገድ ውሳኔ እንዲሰጡ መደረጉ የዚህ ነፀብራቅ ነው ፡፡
- በማናቸውም ሁኔታ ማሰረጃው ምክንያታዊ ጥርጣሬን በማያስነሳ ሁኔታ ተከሳሹ ድርጊቱን ስለመፈፀሙ የማያስረዳ ከሆነ ማለትም የዐ/ህግ ማስረጃ ያስረዳው ፍሬ ነገር አጠራጣሪ ሁኔታዎች ካሉና ጥርጣሬውን ምክንያታዊ ከሆነ ተከሳሹ የጥርጣሬው ተጠቃሚ መሆን ይገባዋል

## የቀጠለ. . .

2. በወንጀል ጉዳይ ተፈላጊው የአስረጂነት መመዘኛ ከምክንያቲዊ ጥርጣሬ በላይ ማስረዳት እንዲሆን ያስፈለገው " በወንጀል የተከሰሰ ሰው ድርጊቱን መፈፀሙ በሚገባ እስኪረጋገጥ ድረስ ነፃ ሆኖ የመቆጠር መብት አለው " የሚል መርህ ለማስፈፀም ነው ። ስለዚህ ከሳሽ ዐ/ህግ ይህንን" ነፃ ሆኖ የመገመት /የመቆጠር መብት" ለማስቀረት ወይም ለማስተባበል ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል የሚያቋቀሙ ፍሬ ነገሮችን በሙሉ እርግጠኛ ለመሆን በሚጠጋ ሁኔታ ማስረዳትና ተከሳሹ ጥፋተኛ መሆኑን ማሰማን ይጠበቅበታል ። እንዲሁም በወንጀል ጉዳይ በማስረጃ ምዘና ወቅት በሚፈፀም ስህተት ምክንያት ወንጀሉን ያልፈፀመ ሰው በስህተት ወይም ባልተረጋገጠ ማስረጃ ምክንያት ጥፋተኛ እንዳይሆን መከላከል ነው።በአንግሎ አሜሪካ የህግ ስረዓት መሰረት ወንጀል ያልፈፀመና ነፃ ሊባል የሚገባውን ሰው በስህተት ጥፋተኛ ማድረግ የሚያስከትለው ኪሳራ ሲነፃፃር እጅግ የከፋ ተደርጎ ይወሰዳል ።

## የቀጠለ . . . .

"በስህተት ምክንያት አንድ ሰው ከሚቀጣ አስር ወንጀለኞች በነፃ ቢለቀቁ ይመረጣል " እንደሚባለው ማለት ነው ።(Clermomt p16)

ሌላው ምክንያት ተብሎ የሚገለፀው ደግሞ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ የአስረጂነት መመዘኛ ህብረተሰቡ ለወንጀል ህግ አክብሮትና መተማመን

እንዲኖረው ያደርጋል የሚል ነው ። ማለትም ወንጀል ያልፈፀሙ ሰዎች ጥፋተኛ ተደርገው ይቀጣሉ የሚል ስጋት እንዳይኖረው ያደረጋል የሚል ነው ።

አመለካከት አለ ።

**ለ. በፍትሐብሔር ጉዳይ የአስረጂነት ደረጃ (መመዘኛ )**

ከላይ እንደተገለፀው የፍ/ሔር ጉዳይ ለማስረዳት የሚቀርቡ ማስረጃ አስረድቷል ለማለት ተፈላጊ የሆነው የአስረጂነት ደረጃ ወይም መመዘኛ ከወንጀል ጉዳይ የተለየ ነው ። ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ማስረዳትን የሚፈልገው መመዘኛ ለፍ/ሔር ጉዳዮች ተፈፃሚ አይሆንም በአሜሪካን ህግ መሰረት በፍ/ሔር ጉዳይ የሚቀርብ ማስረጃ የአስረጂነት ደረጃ ወይም መመዘኛ ሁለት ሁለት መልክ አለው ። እነዚህም፦-

## የቀጠለ. . .

- በተሻለ ሁኔታ በማሳመን የማስረዳት መመዘኛ (preponderance )እና
- ግልጽና ወሳኝ በሆነ ሁኔታ የማስረዳት መመዘኛ (Clear and convincing evidence) ናቸው፡፡

ከነዚህ መካከል በስፋት የሚታወቀውና እጅግ በሚበዙት የፍ/ሔር ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት ያለው በተሻለ ሁኔታ በማሰመን የመስረዳት ደረጃ ወይም መመዘኛ ነው ፡፡

2. የተሻለ አስረጅ በማቅረብ የማስረዳት መመዘኛ (preponderance )ማለት በፍ/ሔር ጉዳይ የማሰመን ሸክም ያለበት ወገን (በአብዛኛው ከሳሹ ነው ) የአቀረበው ማስረጃ ያስረዳል ተብሎ የቀረበበትን ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖር በተመለከተ የማይመስል ከሚባል ይልቅ ይመስላል በሚል ደረጃ ማስረዳት መቻሉን የሚመለከት ነው (More likely than not )፡፡ በዚህም መሰረት ክስ የአቀረበ ከሳሽ አቋሙን ያስረዳልኛል በሚል የአቀረበው ማስረጃ አጠራጣሪ ሁኔታዎች ቢኖሩ እንኳን እነዚህ አጠራጣሪ

# የቀጠለ . . .

ሁኔታዎች ቢኖሩ እንኳን  እነዚህ አጠራጣሪ ሁኔታዎችም ምክንያታዊ ቢሆኑም እንኳን ከሳሹ የአቀረበው ማስረጃ ያስረዳዋል ከተባለው ጭብጥ አንፃር ፍሬ ነገሩ  የለም ከማለት ይልቅ አለ ያስብላል በሚል ደረጃ ከደረሰ አስረድቷል ይባላል ። ስለዚህ የዚህ የማስረዳት መመዘኛ ማዕከላዊ ነጥብ አከራካሪ ከሆነው ጭብጥ የትኛው የተሻለ (መኖሩን ወይም አለመኖሩን )ያስረዳል ? የሚል ነው ። ለምሳሌ ተወላጅነት ለማስረዳት የቀረቡት ምስክሮች ከፊሉ አመልካቹ በጋብቻ ውስጥ የተወለደ መሆኑን ሲመሰክሩ  ከፊል ደግሞ ሟች የተወለደበት ጊዜ ተከሳሹ ( አባት ነው በሚል ክስ የቀረበበት ሰው )ከከሳሹ (አመልካቹ ) አናት ጋር አብረው ይኖር እንደነበር ነገር ግን በጋብቻ ውስጥ አለመሆኑን የመሰከሩ ቢሆን ማስረጃዎች የሰጡት ቃል በአንድ ላይ ሲመዘን "አመልካቹ በጋብቻ ውስጥ አልተወለደም ከማለት ይልቅ በጋብቻ ውስጥ የተወለደ መሆኑን በተሻለ ያስረዳል " ማለት ይቻለል ከጥርጣሬ በላይ አስረድቷል? የሚል ጥያቄ ማቅረብ አያስፈልግም ።

3. በፍ/ሔር ጉዳይ ይህንን የመሰለ ቀለል ያለ የአስረጅነት መመዘኛ ተመራጭ የሆነው በወንጀል የተቀመጠው ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ የማስረዳት ግዴታ የተፈለገበት ምክንያት በፍ/ሔር ጉዳይ ቦታ ስለሌለው ነው ፡፡ በፍ/ሔር የተከሰሰ ሰው ኃላፊነቱ እስኪወሰን ድረስ ንፁህ ሆኖ ይገመታል የሚል መርህ የለም ፡፡ አንድ ሰው ያለአግባብ ጥፋተኛ ቢሆን የሚፈጥረው ኪሳራ አስር ጥፋት የፈፀሙ ሰዎች በነፃ ቢለቀቁ ከሚደርሰው ኪሳራ የከፋ ነው የሚል መርህ በፍ/ሔር ጉዳዮች ላይ አግባብነት የለውም ፡፡ በፍ/ሔር ጉዳይ በአንድ ሰው ላይ የሚደርሰው ኪሳራ በሌላ ሰው ላይ ከሚደርሰው ኪሳራ ጋር እኩል ክብደት አለው ፡፡ ስለዚህ ተገቢ የሚሆነው ማስረጃ የበለጠ ያስረዳው የትኛውን ፍሬ ነገር ነው ? የሚለው መመዘኛ ነው ፡፡

# የቀጠለ. . .

4. ግልጽና አሳማኝ ማስረጃ በማቅረብ የማስረዳት የአስረጅነት መመዘኛ (Clear and Convincing Evidence standard of proof ) ተቀባይነት (በአሜሪካ ህግ መሰረት ማለት ነው ) በተወሰኑ ጉዳዮች ነው ፡፡ ለምሳሌ የአስተዳዳሪነት ወይም ሞግዚቱ ይህንን ተግባር ለማከናወን ብቃት እንደሌለው በግልጽና ፍ/ቤቱን በሚያሳምን ማስረጃ ማስረዳት ይገባል እንደሚባለው ዓይነት ማለት ነው :: ይህ ማለት ማስረጃው ተከሳሹ ለሞግዚትነት ወይም ለአሳዳሪነት በቂ አለመሆኑን ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ እንዲያስረዳ አይጠበቅም ፡፡ ተፈላጊው ነገር ማስረጃው ተከሳሹ የሞግዚትነት ሥራውን ለመስራት አልቻለም ለማለት በቂና ፍ/ቤቱም እንዲያምን ማድረግ መቻሉ ነው ፡፡

## የቀጠለ ...

5. ይህ በቂና አሳማኝ ማስረጃ በማቅረብ የማስረዳት መመዘኛ መካከለኛ ደረጃ ወይም መመዘኛ (intermediate Standard ) ሊባልም ይችላል። ስለዚህም ምክንያቱ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ከማስረዳት ዝቅ ይላል፣ባይመስላል ወይም የትኛውን የበለጠ ያስረዳል (preponderance) ከሚለው ደግሞ ከፍ ማለቱ ነው ።

## 2.የሲቪል ህግ ሥረዓት አቀራረብ

1. ይህን የህግ ሥረዓት በሚከተሉ አገሮች የማስረጃው የአስጅነት ደረጃ ወይም መመዘኛ በወንጀልና በፍ/ሔር ጉዳዮች መካከል ልዩነት አይንፀባረቅም ። በሁለቱም ጉዳዮች ማስረጃው እንዲያስረዳ የሚጠበቀው የተፈለገው ፍሬ ነገር መኖሩን ወይም አለመኖሩን ከፍ ባለ ደረጃ ማስረዳቱ ነው ። ማስረጃው ምክንያታዊ ጥርጣሬ በሚያስነሳ ሁኔታ እንዲያስረዳ አይጠበቅበትም ( በወንጀልም ሆነ በፍ/ሔር ጉዳይ ማለት ነው )። እንዲሁም በተሻለ ደረጃ ያስረዳ በሚልም የወረደ መመዘኛ አይቀበልም። መመዘኛው የሚሆነው ማስረጃው በተቻለ መጠን ግልጽና አሰማኝ በሆነ ሁኔታ ተፈላጊው ፍሬ ነገር ስለመኖሩ ወይም አለመኖሩ ሊያስረዳ ይገባል የሚለው ነው ።

## የቀጠለ ...

2.በዚህም መሰረት የሲቪል ህግ ሥረዓት የማስረጃ አስረጂነት መመዘኛ ከአንግሎ አሜሪካ የህግ ስረዓት ጋር ሲነፃፃር ከላይ ከተጠቀሰው የአሜሪካ ህግ በተወሰኑ የፍ/ሔር ጉዳዮች ላይ የሚፈለገውን በቂና አሳማኝ ማስረጃ የማቅረብ የማስረዳት መመዘኛ (Clear and Convincing evidence standard of proof )ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ይህንን ለወንጀልም ሆነ ለፍ/ሔር ጉዳይ በተመሳሳይ ይጠቀማሉ ፡፡ ለዚህ የህግ ሥረዓት ጀርመን ፣ፈረንሳይ እና ጃፓንን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል ፡፡ (Ciermont, pp2-3-13-14)

## 6.2.3. ልዩነት ስለሚያስከትለው ውጤት

1. ሁለቱ የህግ ሥረዓቶች የተለየ መመዘኛ መከተላቸው የተለያዩ ውጤቶችን የሚያስከትል ሲሆን ፡- እነዚህም

- በወንጀል ክስ የጥፋተኛነት ውሳኔ ከማስገኘት (Conviction Rate )
- ወጪን ከቀነስ (Cost minimization ) እንዲሁም
- ጥንቃቄ እንዲደረግ ከማበረታት አንፃር (Providing incentives ) ሊገልጽ ይችላል ፡፡

የቀጠለ . . .

2.በወንጀል ክስ የጥፋተኛነት ውሳኔ ከማስገኘት አንፃር ሲታይ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ የማስረዳት የአስረጅነት መመዘኛ ከፍተኛ በመሆኑና በጥርጣሬ መነሻ ተከሳሾቹ በነፃ ሊለቀቁ የሚችሉበት ዕድልም የሰፋ በመሆኑ በቂና አሳማኝ መመዘኛን ከሚጠቀሙ አገሮች ጋር ሲነፃፀር ክስ ከቀረበባቸው ተከሳሾች መካከል ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው በነፃ እንዲሰናበቱ ያደርጋል ስለዚህ የጥፋተኛነት ውሳኔ የማስጠት መቶኛው የቀነሰ ነው ፡፡

3. ወጪን ከመቀነስ አንፃር በማነፃፀሪያነት የሚታየው የፍ/ሔር ጉዳይ ነው ፡፡ ማስረጃው አስረድቷል ለማለት ከፍ ያለ መመዘኛ የሚጠይቅ ስርዓት ተፈፃሚ የሚያደረግ ከሆነ ይህንን ደረጃ የሚያሟላ ማስረጃ ማቅረብ የሚያስፈልግ ሲሆን ለዚህ ተከራካሪ ወገን (በአብዛኛው ከሳሹ ) ማስረጃውን ለማሟላት ከፍተኛ ወጪ ያወጣል ፡፡ በአንፃሩ የተሻለ ወይም በይመስላል አስረጅነት ደረጃ ተፈፃሚ የሚደረግ ከሆነ ይህንን መመዘኛ የሚያሟላ ማስረጃ በቀላሉ ማግኘት ስለሚቻል ማስረጃን ለመሰብሰብ የሚወጣውን ወጪ ይቀነሳል ፡፡

## የቀጠለ . . .

4. ጥንቃቄ እንዲደረግ ከማበረታታት አንፃር ሊፃፀር የሚችለውም በፍ/ሔር ጉዳይ ሆኖ በተለይ በቸልተኛነት ላይ የተመሰረተ ኃላፊነት ከመወሰን ጋር ነው ። የአስረጅነት መመዘኛው ከፍተኛ ነው ማለት ( እንደ ሲቪል ህግ ስርዓት ማለት ነው ) ተከሳሹ በቸልተኛነት አጥፍቷል ለማስባልና ቸልተኛነት መኖሩን ለማስረዳት ከሰሽ ያለውን ዕድል ያጠብበታል ። ደካማ ማስረጃ በማቅረብ ቸልተኝነትን ማስረዳት አስቸጋሪ ይሆናል ። ስለዚህም በማስረጃው በቂ አለመሆን የተነሳ ጥፋት የፈፀሙ ሰዎች ከኃላፊነት የሚያመልጡበት ዕድል ስለሚያሰፋላቸው ቸልተኛ ላለመሆን እንዳይተጉ ያደርጋል ፣ወይም ትጋታቸውን ይቀንሳል ። በሌላ በኩል ደግሞ ቀላል ባለ መመዘኛ (ለምሳሌ ቸልተኛነት ያለ ይመስላል የሚል ) በመጠቀም ቸልተኛነትን ማስረዳት የሚቻል ከሆነ ከሳሽ ቸልተኛነቱን በቀላሉ እና ደከም ባለ ማስረጃ የማስረዳት ዕድሉን ስለሚያሰፋለት ሰዎች ቸልተኛ እንዳይሆኑ፣እንዲጠነቀቁ ይበረታታል ::

## 6.3 የአስረጂነት መመዘኛ ከኢትዮጲያ ህግ አንፃር

### 6.3.1 በወንጀል ጉዳይ

1. በወንጀል ጉዳይ የቀረበ የዐ/ህግ ማስረጃ ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል መፈፀሙን ያስረዳል ወይ? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/141 እና 142 ድንጋጌ አጣምሮ ማየት ያስፈልጋል ፡፡ ቁጥር 141 ርዕሱ "ዐቃቤ ህጉ ክስን ባለስረዳ ጊዜ ስለ ተከሳሹ መልቀቅ " የሚል ሆኖ ዝርዝሩ ደግሞ "ዐቃቤ ህጉ ማስረጃውን አሰምቶ ከጨረሰ በኋላ ማፍረሻ ማስረጃ ማቅረብ አስፈላጊ ሳይሆን ተከሳሹን ጥፋተኛ የሚያደርገው ሆኖ ባልተገኘ ጊዜ እና ማስረጃው በቂ ሆኖ ሳያገኘው የቀረ እንደሆነ ተከሳሹ በነፃ እንዲለቀቅ ፍ/ቤቱ ያዛል" ይላል ፡፡ ቁጥር 142/1/ ደግሞ ተከሳሹ ማስተባባያ (የመከላከያ ) ማስረጃ እንዲያቀርብ የሚታዘዘው "በቀረበበት ማስረጃ መሰረት የተመሰከረበት ከሆነ"ነው ፡፡ በዚህም መሰረት እነዚህ ሁለት ድንጋጌዎች ተጣምረው ሲታዩ፡-

• **የቀጠለ . . .**

•ተከሳሹ መከላከያ እንዲያቀርብ የሚታዘዘው ተከሳሹ “በቀረበበት ማስረጃ መሰረት የተመሰከረበት ከሆነ"ነው ።

•ተከሳሹ በቀረበበት ማስረጃ መሰረት ተመስክሮበታል የሚባለው ይህ የዐ/ህግ ማስረጃ "ተከሳሽን ጥፋተኛ የሚያደርገው ሆኖ " የተገኘ እንደሆነ ነው ።

•ማስረጃው ተከሳሹን ጥፋተኛ ሊያደርገው የሚችለው ደግሞ በፍ/ቤቱ አስተያየት ተከሳሹን ጥፋተኛ ለማድረግ በቂ ሆኖ ሲገኝ ነው ።

2. ከዚህ የምንረዳው ማስረጃው ተከሳሹን ጥፋተኛ ለማድረግ በቂ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን የሚወስነው ፍ/ቤት መሆኑን ነው ። ነገር ግን ይህ አባባል የተሟላ ስዕል አይሰጥም ።

ጥፋተኛ ሆኖ ለመገኘት በቂ ማስረጃ እንደሚያስፈልግ ከመግለጽ አልፎ "በቂ "ነው ሲባል ምን ማለት እንደሆነ አይነግረንም "በቂ ነው " ሲባል ምን ማለት ነው ? ምክንያታዊ ጥርጣሬ በማያስነሳ ሁኔታ ማስረዳት? ወይስ ግልጽና አስማኝ በሆነ ሁኔታ ማስረዳት ? ወይም በተሻለ አስረድቷል በሚል መመዘኛ ማስረዳት ?

የቀጠለ . . .

3. ድንጋጌ አተረጓጎም በተመለከተ የአገራችን ፍ/ቤቶች በአብዛኛው የሚቀበሉት ጥርጣሬ በማያስነሳ ሁኔታ ማስረዳት ነው ። በበርካታ የፍ/ቤት ውሳኔዎች ላይ እንደሚታየው ዐ/ሕግ በሚያቀርበው ማስረጃ ተከሳሹ ወንጀሉን ስለመፈፀሙ ጥርጣሬ በሚያስነሳ ሁኔታ ማስረዳት እንደሚገባው አቋም ይያዛል (ለምሳሌ የጠ/ፍ/ቤት የወ/ይ/መ/ቁ 1118/76 ተመልከት )

4. ሆኖም በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 141 ላይ የተደነገገው በቂ የሚለው ቃል ምንም ጥርጣሬ በማያስነሳ ሁኔታ ማስረዳትን የሚመለከት አይደለም በቂ የሚለው ቃል ፍፁም የተሟላ የሚለውን ይመለከታል ለማለት አስቸጋሪ ነው በዚሁ መሰረት፡-

* በቁጥር 141 መሰረት በቂ ነው የሚለው መመዘኛ በአንግሎ አሜሪካ የህግ ስረዓት በወንጀል ጉዳይ ተፈላጊው የሆነውን "ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ የማስረዳት "መመዘኛ ይመለከታል ለማለት አይቻልም ። ከላይ እንደተጠቀሰው "ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ " ሲባል የአስረጂነት ደረጃው ወደ መቶ በመቶ የተጠጋ እውነተኛነቱ የተረጋገጠን ማስረጃ የሚመለከት ሲሆን ይህ ደግሞ ከበቂ በላይ እንጂ "በቂ "ለማለት የማይቻል ነው ። ቁጥር 141 ግን የአስረጂነቱ "በቂ" በላይ " ይሁን በማለት አይናገርም ። ከውሳኔ በፊት ጥፋተኛ ሆኖ ያለመቆጠር መብት በኢትዮጲያ ህግ ውስጥም የተካተተ ቢሆንም ይህ ማለት ግን (ከኛ ህግ አኳያ ) ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ማስረዳትን አይመለከትም ።

## •የቀጠለ . . .

•እንዲሁም በቁጥር 141 መሰረት ማስረጃው "በቂ " ለመሆን በአንግሎ አሜሪካ የህግ ሥረዓት ተከታይ አገሮች ለአብዛኛው የፍ/ሔር ጉዳዮች አስረጅነት በመመዘኛነት የሚያገለግልውን በይመስላል ወይም በተሻለ አስረድቷል ።(Balance of probability or preponderance ) ይመለከታል ለማለት አይቻልም ። ለወንጀል ጉዳይ እንዲህ ዓይነት መመዘኛ የማይታወቅ ሲሆን ቁጥር 141 ላይ ይህን መመዘኛ ለማንፀባራቅ ተፈልጎ ቢሆን ኖሮ "ማፍረሻ ማስረጃ ሳያስፈልግ ተከሳሹን ጥፋተኛ የሚያደርገው ሆኖ ባልተገኘ ጊዜ....... ተከሳሽ በነፃ እንዲለቀቅ ፍ/ቤቱ ያዝዛል " ማለት ብቻ ይበቃ ነበር ። ይህም ይበዛል ። ህጉ ግን ከዚህ በተጫማሪ "እና ማስረጃወወ በቂ ሆኖ ሳያገኘው ሲቀር ----የሚል ጨምሮበታል። ስለዚህ ያስረዳ ይመስላል የሚል መመዘኛ መጠቀም አንችልም ።

•**የቀጠለ .**. .

•ይልቁንም ቁጥር 141 የሚቀርበው በአንግሎ አሜሪካን የህግ ሥረዓት ተከታይ አገሮች (ለምሳሌ በአሜሪካ )በጣም ለተወሰኑ የፍ/ሔር ጉዳይ ብቻ የሚውለው በሲቪል ህግ ሥረዓት ደግሞ ለፍ/ሔር ለወንጀል ጉዳዮችም ተመሳሳይ አገልግሎት ያለው ግልጽና አሳማኝ ማስረጃ በማቅረብ የማስረዳት መመዘኛ ነው ለማለት ይችላል ፡፡ ስለዚህ በኛ አገር የወንጀል ጉዳይ የአስረጂነት ደረጃው ዐ/ሕግ ተከሳሽ ወንጀሉን ስለመፈፀሙ ግልጽና ፍርድ ቤቱን የሚያሳምን ማስረጃ በማቅረብ ማስረዳት አለበት የሚለው ነው ፡፡

## 5. ይህ መመዘኛ በኛ ህግ ተፈፃሚነት ካለ

* ዐቃቤ ህግ የአቀረበው ማስረጃ ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል ለማቋቋም አስፈላጊ የሆኑን ነገሮች ሁሉንም በበቂ ሁኔታ (ከላይ የተጠቀሰው መመዘኛ ማለት ነው ) ማስረዳት የሚጠበቅበት ሲሆን ከነዚህ መካከል አንዱን እንኳን ግልጽና አሳማኝ በሆኑ ሁኔታ ማስረዳት ካልቻለ መመዘኛውን አላሟላም ማለት ነው ፡፡

• <u>የቀጠለ .</u> . .

•ዐ/ህግ ያቀረበው ምስክር በቀረበለት መስቀልኛ ጥያቄ ወይም በተከሳሽ መከላከያ ማስረጃ አማካኝነት ክብደት የእጣ ማስረጃ በሚያሳምን ሁኔታ ሊያስረዳ አይችልምና

•እንዲሁም ዐ/ህጉ የአቀረበው ማስረጃ በግልጽ በሚታይ ሁኔታ የማይታመን በመሆኑ የተነሳ የጥፋተኛነት ውሳኔ ለመሰጠት የሚያስችል ሲሆን (When the evidence adduced by the prosecution is so manifestly unreliable )በቂ ነው ለማለት አንችልም (fisher ,p310)

## 6.3.2 በፍትሐብሔር ጉዳይ

1.ኢትዮጵያ የፍ/ሔር ጉዳይ ለማስረዳት የቀረበ ማስረጃ አስረድቷል ለማለት መመዘኛው ምንድነው ? የሚለውን በተመለከተ የተቆጠረው መልስ ለማግኘት ያስቸግራል ፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉ የሚደነግገው የማስረዳት ሸክም ያለበት ሰው አስቀድሞ ማስረጃውን ካቀረበ በኋላ ሌላኛው ተከራካሪ ወገን ደግሞ በመቀጠል የሚያቀርብ መሆኑን እንጂ የማስረጃው አስረጅነት አስከ ምን ደረጃ መሆን እንዳለበት አይደነግግም ፤ዞሮ ዞሮ ግን በፍ/ሔር ጉዳይም ቢሆን የቀረበ ማስረጃ ሁሉ በደፈና አስረድቷል የማይባልና ይልቁንም የሚመዘን በመሆኑ ማስረጃው ተፈላጊውን ፍሬ ነገር አስረድቷል ለማለት የሚቻልበት መመዘኛ ማበጀት የማይቀር ነው ፡፡

የቀጠለ . . .

2.የማስረጃውን አስረጅነት ለመወሰን የሚረዱ መመዘኛዎች ከፍ/ሔር ህጉና ከሌሎችም ህጎች ማግኘት ይችላል ። ለምሳሌ በፍ/ሔር ህግ ውስጥ ይህንን መመዘኛ የሚያመለክቱ ድንጋጌዎችን ማግኘት ይቻላል ። እነዚህ መመዘኛዎ ሲታዩም አንድ ወጥ ሳይሆኑ እንደተፈላጊው ፍሬ ነገር ሊለያዩ የሚችሉ ናቸው ። በዚህም መሰረት የሚቀጥለውን ማጠቃላያ ለመሰጠት ይቻላል ።

* ከፍ ያለ የአስረጅነት ደረጃን የሚጠይቁ ድንጋጌዎች የሚገኙ ሲሆን እነዚህም በህጉ ተለይተው በተቀመጡ ጊዜ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል ። በነዚህ ድንጋጌዎች ላይ የማስረጃው የአስረጅነት ደረጃ "እርግጠኛ በሆነ ዓይነት በማስረዳት " (ቁጥር 756/2 ) ወዘተ በሚል ተቀምጠዋል ።

* በሚመስል ሁኔታ ማስረዳት ብቻ በቂ መሆኑ በግልጽ የተነገረባቸው ድንጋጌዎችም አሉ ።ለምሳሌ በቁጥር 157/1/ አነጋገር አንድ ሰው ጠፍቷል በሚል ውሳኔ ለመሰጠት የጠፋው ሰው የሞተ የሚመስል መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ማግኘቱ በቂ ነው (ቁጥር 157/1/)።

## • የቀጠለ . . .

- ህግ በዚህ ዓይነት ቋንቋ ማስረዳት ይችላል በሚል ሲያስቀምጥ በሚመስል ማስረዳት (preponderance) በቂ ነው ፡፡ ሌሎችም በቁጥር 62/1/፣2341/3/፣2342/3፣2344/2/ መመልከት ይችላል ፡፡
- ድንጋጌዎች በግልጽ ቋንቋ " መስሎ ሲታይ "በሚል የሚያስቀምጡ ቢሆን እንኳን ከፍ ያለ አስረጅነትን የሚገልፅ የተለየ ድንጋጌ እስከሌለ ድረስ ለፍ/ሔር ጉዳይ "በሚመስል ሁኔታ “ማስረዳት በቂ ነው ፡፡

## ምዕራፍ 7
## የምስክሮች ቃል አስረጂነት ስለመመዘን

### 7.1 ጠቅላላ

•የማስረጃ የመጨረሻ ግብ ሊያስረዳው የቀረበበትን ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖር ማስረዳት መቻል ነው ፡፡ ማስረጃው ሊያስረዳው የቀረበበት ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለኖር አስረድቷል የሚባለው መቼ ነው ?የሚባለው የማስረጃ አስረጅነት መመዘኛ (ወይም ደረጃን )የሚመለከት ሲሆን ባለፈው ምዕራፍ ተገልፆአል፡፡ ያም ሆኖ ግን ማስረጃው አስረድቷል ?ወይስ አልስረዳም ?የሚለውን ለመመለስ የቀረበውን ማስረጃ መመዘን ያስፈልጋል ፡፡ ስለዚህም አስረድቷል ? ወይስ አላስረዳም ? የሚለውን ለመወሰን የቀረቡ ማስረጃዎች ይመረመራሉ፣ይገናዘባሉ፣ይተቻሉ፡፡ በዚህ ሂደት ድክመትን ጥንካሬያቸው ተጣርቶ ይወጣል ፡፡ ከዚህ ሂደት የሚገኘው ውጤት ደግሞ ማስረጃዎች አስረድተዋል፣ወይም አላሟሉም ስለዚህ አላስረዳም የሚል መደምደሚያ ላይ ያደርሳል ፡፡

የቀጠለ ...

2. የዚህና የተከታይ ሁለት ምዕራፎች ትኩረትም የቀረቡ ማስረጃዎችን በመመዘን ሂደት መሰረታዊ የሆኑና ግምት ውስጥ ሊገቡ ስለሚገባቸው ጉዳዮች መግለጽ ይሆናል ። የማስረጃ ምዘና ሂደት ፍሬ ነገርን ያስረዳል ወይም ያስተባብላል በሚል በሚቀርበው የማስረጃ ዓይነት ላይ የሚመሰረት በመሆኑ ከቀረበው የማስረጃ ዓይነት አንፃር ልዩነት ሊያሳይ ይችላል ። በዚህም መሰረት በዚህ ምዕራፍ የምስክሮች ቃላ ሲመዘን ግምት ውስጥ ሊገቡ የሚገባቸው ጉዳዮች የሚገልጽ ሲሆን በተከታታይ ሁለት ምዕራፎች ደግሞ የሰነድ ኤግዚብትና የዕምነት ቃል ማስረጃዎች ምዘናን የሚመለከቱ ጉዳዮች ይታያሉ።

3. በሌላ በኩል ደግሞ ወደ ማስረጃው አመዛዘን ዝርዝር ጉዳዮች ከመግባት አስቀድሞ የሚከተሉት ነጥቦች ትኩረት ሊሰጥባቸው ይገባል ። በመጀመሪያ ደረጃ ማስረጃው ያስረዳባቸዋል የተባሉት ፍሬ ነገሮች ማስረጃው ከመቅረቡ በፊት በሚገባ ተለይተው መታወቅ አለባቸው ። ማስረጃው ተፈላጊውን ፍሬ ነገር በሚገባ ተለይቶ ሊታወቅ ይገባል ።

• የቀጠለ ...

• ይህ ከጭብጥ አያያዝ ጋር ተያያዞ ተገልፆአል ።በሁለተኛ ደረጃም በፍ/ሔር ሆነ በወንጀል ጉዳዮች የምክንያትና የውጤት ግንኙነቶች ማስረጃን በመመዘን ረገድ ትኩረት ሊሰጥባቸው ይገባል ። ማለትም የቀረበው ማስረጃ ከሚገልፀው ፍሬ ነገር አንፃር ተከራካሪውን ወገን የሚኖረው መብት ወይም ኃላፊነት ተጣርቶ ሊታወቅ ይገባል ። በተለይ ብዙ ሰዎች በአንድነት ከሳሽ ወይም ተከሳሽ በሆኑበት ሁኔታ የእያንዳንድን ተከራካሪ ወገን መብትና ኃላፊነት መለየትና ከተገኘው ውጤት ጋር ያለውን ግንኙነት ማገናዘብ አስፈላጊ ነው ። ለምሳሌ በርካታ ሰዎች በአንድነት በተከሰሱበት ጉዳይ የቀረቡት ማስረጃዎች ክሱን አስረድተዋል ወይስ አላስረዱም? የሚለውን ለመወሰን ማስረጃዎቹ በሚመረምሩበት ወቅት ፣

ማስረጃዎች እያንዳንዱን ተከሳሽ በተመለከተ ፈፀመ ወይም ተሳተፈ በሚል ያስረዱት መለየትና መመዘን አለበት ።

•የቀጠለ . . .

•እያንዳንዱ ተከሳሽ ፈፀመ ተብሎ በማስረጃ የተነገረበት ድርጊት ተፈላጊውን ውጤት ለማስከተል ያለው ብቃት ወይም አስተዋጽኦ እስከ ምን ድረስ እንደሆነ ተለያይቶ መመዘን አለበት ፡፡

## 7.2 ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ማስረጃ ምዘና መሰረታዊ ነጥቦች

1. ከተፈላጊው እና በጭብጥ ከተያዘው ፍሬ ነገር ጋር ካለው ግንኙነት አንፃር ማስረጃው ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ በሚል ሊፈረጅ እንደሚችል በምዕራፍ 1 ውስጥ ተገልጾአል ፡፡ የማስረጃ ምዝናን በተመለከተ ጉዳዩ ወንጀልም ሆነ ፍ/ሐር (የአስረጂነት ደረጃው የሚያሳየው ልዩነት እንደተጠበቀ ሆኖ ) ሁለቱም ዓይነት (ማለትም ቀጥተኛም የሆነ ቀጥተኛ ያልሆኑ ማስረጃዎች አግባብነት እስከላቸው ድረስ እና አይቀርቡም እስካልተባሉ ድረስ ቀርበው ይመዘናሉ ፡፡

2. በሌላ በኩል ደግሞ ቀጥተኛ ማስረጃ ቀጥተኛ ካልሆነ ማስረጃ የተሻለ አስረጂነት አለው ብሎ መገመት ስህተት ሊሆን ይችላል ፡፡ በፍ/ቤት የቀረበ የዓይን ምስክር (የሚያስረዳው ፍሬ ነገር ሲፈፀም ያየ )ወይም ስለ ፍሬ ነገሩ ቀጥታ መሆኑ ሁኔታ አውቃለሁ በሚል የሚመስክር ምስክር አካባቢያዊ ሁኔታዎችን ገልጾ ከሚያስረዳ ማስረጃ የተሻለ አስረጅነት አለው ብሎ መደምደም ተገቢነት የለውም ፡፡ ዋናው ቁም ነገር የቀረበው ማስረጃ ከብዙ አጋጣሚዎች አንፃር ሲመዘን የሚኖረውን የአስረጅነት ብቃት እንጂ ቀጥተኛ መሆን አለመሆን ላይ አይደለም ፡፡

## የቀጠለ . . .

. በዚህም መሰረት ማስጃ ሲመዘን

• ድርጊቱ ሲፈፀም በአይን አየሁ የሚል የምስክርነት ቃል ፍሬ ነገሩን ለማስረዳት ብቸኛው ተዓማኒ ወይም ሁል ጊዜም የተሻለ አስረጅ ነው ለማለት አይቻልም ፡፡ አይቻለሁ በሚል ምስክሩ የተናገረ ቢሆንም ወረድ ብለን እንደምንመለከተው ምስክሩ በጉዳዩ አወሳሰን አንፃር ካለው የግል ፍላጎት ድርጊቱ ለማየት አጋጣሚውን ካገኘበት ሁኔታ አኳያ ሲመዘን እውነተኛ ላይሆን ይችላል ፡፡ ስለዚህ ማስረጃው የዓይን ምስክር (ወይም በጠቅላላው አነጋገር ቀጥተኛ ማስረጃ መሆኑ )ተፈላጊው ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖሩን በተመለከተ ለመድረስ የምንወስድውን ግምት (inference)ይቀንስልን ወይም ያሰወግድልን እንደሆነ እንጂ በራሱ ከአካባቢያዊ ማስረጃ በላቀ ሁኔታ ሙሉ በሙሉእምነት የሚጣልበት ነው አያሰኝም ፡፡

• የቀጠለ

• ማስረጃን የተለየ የሚያደርገው ማስረጃው ሊያስረዳው ከተፈለገው ፍሬ ነገር አንፃር ቀጥተኛ ግንኙነት የሌለው በመሆኑ ወደ ተፈላጊው ወደ ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖር የሚያመራን በቀጥታ ሳይሆን በመገመት(inference) መሆኑ ነው ነገር ግን አካባቢያዊ ማስረጃ ዝቅተኛ ግምት የሚሰጠው ነው ሊባል አይገባም ፡፡፡ በርካታ ወንጀሎች በባህሪያቸው የዓይን ምስክር በሌለበት ሁኔታ ሊፈፀሙ የሚችሉ መሆናቸው ሲታወቅ አካባቢያ ማስረጃ ጠቀሜታው ከፍተኛ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል ፡፡ አካባቢያዊ ማስረጃም ይገመገማል ፣ይመዘናል፣በምዘናው ሂደት ክብደት አጥቶ እንደሚወድቅ ሁሉ አሳማኝ በሆኑ ሆኔታ ሊያስረዳም ይችላል ፡፡ ስለዚህ አካባቢያዊ ማስረጃ ቀጥተኛ ማስረጃዎችን የመደገፍ ሚና ብቻ እንደሚጫወት የሚወስድ አቋም ትክክለኛ አይደለም ፡፡

የቀጠለ . . .

**4.የሰሚ ሰሚ ማስረጃ** በተመለከተ አግባብነት እስካለው ድረስ በአስረጂነት ሊቀርብ ይችላል (በህጋችን ማለት ነው )። ነገር ግን ይህ ማስረጃ ሲመዘን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል ። በፍ/ሔር ጉዳይ የሰሚ ሰሚ ማስረጃ ጥብቅ ምዘና ባይካሄድበትም የሚያስከትለው ጉዳት የተወሰነ ነው ። በወንጀል ጉዳይ ግን ጥፋተኛ ያልሆነ ሰው ጥፋተኛ ተብሎ ቢቀጣ ከሚያስከትለው ጉዳት አንፃር የሰሚ ሰሚ ማስረጃ በጥንቃቄ መመዘኛ ይኖርበታል። በተለይ ደግሞ ዋናው ማስረጃ (ማለትም ድርጊቱ ሲፈፀም ያየ የሰማ............) ያልቀረበበትና የሰሚ ሰሚ ማስረጃ ተከቶት እንዲቀርብ የተደረገ ምክንያት በትክክል መታወቅ ይኖርበታል ። ዋናው ቀጥተኛ ማስረጃ ሊቀርብ እየቻለ እንዳይቀርብ ተደርጎ ትርጉም ያለው መስቀልኛ ጥያቄ የማይቀርብበት የሰሚ ሰሚ ማስረጃ ቀርቦ ቢመሰክር ወይም የፍሬ ነገርን መኖር ወይም አለኖር ቢገልጽ ለዚህ ቃል ክብደት መስጠት ተገቢ አይደለም ።

• የቀጠለ

•ሰሚ ሰሚ ማስረጃው የመረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለገለው ዋናው ወይም ቀጥተኛ ማስረጃ ፍሬ ነገሩን ከማወቅ ረገድ ያለው ቅርበት፣ዕድል፣ወይም አጋጣሚ የሰሚ ሰሚ ማስረጃ መረጃውን ለማግኘት የቻለ ከሆነ ለማስረጃው አስረጅነት የተሻለ ክብደት የሚሰጠውን ያህል የመረጃ ምንጭ ከተፈላጊው ፍሬ ነገር ጋር ያለው ግንኙነት ቀጥተኛ ከመሆኑ በራቀ ቁጥር በሰሚ ሰሚ ማስረጃው (ወይም ምስክሩ)የሚሰጠው ምስክርነት ወሬ የመሆን እድሉ እየሰፋ እንደሚሄድ ሊታወቅ ይገባል ፡፡

## 7.3 ዕድልና አጋጣሚን መሰረት በማድረግ የምስከሮችን ቃል

ምስክሮች የሰጡት ቃል ትክክለኛነት ከሚመዘንባቸው መስፈርቶች መካከል አንዱ ዕድልና አጋጣሚ ነው ፡፡ ማለትም ምስክሩ ችሎት ቀርቦ የገለፀውን ፍሬ ነገር እሱ እንደሚለው ለማየት፣ለመስማት-----ወዘተ እንዴት ቻለ? በሚል መጠየቅ ያስፈልጋል ፡፡ ይህ ጥያቄ አግባብነት ለፍ/ሔር ለወንጀል ጉዳዮች ሲሆን ከጊዜ ፣ከቦታ እና ድርጊቱ ሲፈፀም የነበረው የምስክሩ ባህርይን መሰረት በማድረግ ሊታይ የሚችል ነው ፡፡

## የቀጠለ

### 7.3.1. ድርጊቱ ከፌፀመበት ቦታ አንፃር

•ድርጊት የተፈፀመበት ቦታ ማስረጃ ለመመዘን ከፍተኛ ድርሻ አለው፡- በዚህም መሰረት ፡- ማስረጃው (ምስክሩ) ያስረዳው ድርጊት የተፈፀመበት ቦታ ለመገኘት የቻለበት ዕድል ወይም አጋጣሚ ሊመረመር ይገባል ። ለምሳሌ በመኖሪያ ቤት ውስጥ ተፈፀመ የተባለን የወንጀል ድርጊት ያስረዳል በሚል የቀረበ ምስክር ድርጊት ሲፈፀም አይቻለሁ የሚል ቢሆን በዚያ ቤት ውስጥ ሊገኝ የቻለበት ዕድል ወይም አጋጣሚ (ቤተሰብ ፣አንግዳ፣ጩኸት ሰምቶ የደረሰ ....) ለሚረመር እና ትክክለኛነቱ ሊመዘን ይገባል *ማስረጃው ያስረዳበትን ፍሬ ነገር ለማወቅ የቻለው የተለየ የስራ ግንኙነት በመኖሩ ሊሆን ይችላል ። በዚህ ጊዜ ምስክሩ በዚያ ስፍራ ሊገኝና ሊያወቅ የቻለበት ምክንያት ሊመዘን ይገባል ። የመንግስት ንብረት ከመጋዘን ሲወሰድ አይቻለሁ የሚል ሰው ድርጊቱን ለመፈፀም የቻለበት ዕድል ወይም አጋጣሚ የሚመረመር ሲሆን ገንዘብ ማጉደሉን አስረዳለሁ የሚል ምስክር የተከሳሹን ሂሳብ ለመመርመር ያለው ዕድል ወይም አጋጣሚ መታወቅ አለበት ። ይህ የሚጠቅመውም ምስክሩ የተናገረው በትክክል የሚያውቀውን ወይም ግምቱን መሆኑን ለመለየት ያስችላል ።

የቀጠለ . . .

## 7.3.2. ድርጊቱ ከፈፀመበት ጊዜ አንፃር

ማስረጃው ያስረዳው ድርጊቱ የተፈፀመበት ጊዜን በማረጋገጥ በማስረጃ ምዘና የተለየ ቦታ ይኖረዋል፡፡ ከጊዜ አንፃር ምስክሩ ድርጊቱ ተፈፀመ በተባለበት ቦታ ሊገኝ መቻል አለመቻሉን የተገኘ ቢሆን እንኳን መለየት መቻል አለመቻሉን ለማረጋገጥ ይጠቅማል ፡፡ በዚሁ መሰረት

- ድርጊቱ የፈፀመው በቀን ወይም በሌሊት መሆኑ የምስከሩ ቃል ለማመንም ሆነ ላለማመን መሰረት ሊሆን ይችላል፡፡ **በጨለማ የተፈፀመ ከሆነ** የተለየ ሁኔታ ከሌለ በቀር የድርጊቱን አፈፃፀም ዝርዝርና ድርጊት ፈፃሚውን ለመለየት መቻልን አጠራጣሪ እንደሚያደርገው ዓይነት ማለት ነው ፡፡ ጨለማ ከመሆኑ የተነሳ እዚያ ቦታ ለመገኘት የቻለበት ምክንያት አጥብቆ እንዲጠየቅ በር ይከፍታል ፡፡
- ድርጊቱ የፈፀመበትን ጊዜ ማወቅ ምስክሩ ምስክርነት የሰጠበት ፍሬ ነገር ለማወቅ የተቀመጠባቸውን መንገዶች ተዓማኒነት ለመመዘን ከፍተኛ ቦታ አለው ፡፡ **ለምሳሌ** ድርጊቱ የተፈፀመው በሌሊት ሆኖ ምስክሩ ድርጊቱን የፈፀመውን ሰው ለመለየት የቻለው በድምጽ ነው ቢል ከዚህ ድምጽ ጋር ያለው ትውውቅ ፣በጨረታ ብርሐን ነው ቢል ምስክሩ ከነበረበትና ድርጊቱ ከተፈፀመበት ቦታ ርቀት አንፃር በጨረቃ ብርሃን መለየት መቻል አለመቻሉን ......... ወዘተ መመርመር ያስፈልጋል ፡፡

## የቀጠለ

## 7.3.3. ያልተለመዱት ባህሪያት

ምስክሩ ያስረዳው ድርጊት ተፈፀመ በተባለ ጊዜና ቦታ የነበረና የተገለፀ የምስክር ባህሪይ ያልተለመደ መሆን በማስረጃ ምዘና ጊዜ መጠቀም አዘውትሮ የሚሰራበት ነው (በተለይም ለወንጀል ጉዳይ )። አንዳንድ ምስክሮች ከድርጊቱ አፈፃፀም አንፃር ከገለፁት ፍሬ ነገር በመነሳት ያንን ድርጊት በስፍራው ሆነው መከታተል መቻላቸው ያልተለመደ ባህርይ (unnatural conduct ) የሚባልበትና በዚህ የተነሳ ማስረጃው አውነተኛ አይደለም የሚል ዝንባሌ የሚፈጥር ሊሆን ይችላል ። በመሰረቱ የዓይን ምስክር የነበረ ሰው ድርጊቱ ሲፈፀም መሸሽ ወይም መጮህ ነበረበት በሚል ምክንያት ውድቅ ሊደረግ አይገባም (Retanla Dhirajila p.50) በዚሁ መሰረትምስክሩ ሳይሸሽ በስፍራው ሆኖ የድርጊቱን አፈፃፀም እስከ መጨረሻው ተከታትየዋለሁ ማለቱ ያልተለመደና የማይጠበቅም በመሆኑ ቃሉ ሊታመን አይችልም በማለት ውድቅ ማድረጉ ተገቢ አይደለም ። ነገር ግን የምስክሩ ያልተለመደ ባህሪይ የሰጠውን ቃል ትክክለኛነት በጥንቃቄ እንድንመረምር

ያደርጋል ። ማስረጃዎች ጋር አገናዝበን መመርመር ይገባናል ።

## የቀጠለ . . .

### 7.4 የምስክሮች ቃል ልዩነትን እና አንድነትን መሰረት በማድረግ መመዘን

በችሎት የቀረቡ ምስክሮች የሰጡት ቃል ትክክለኛነት ከሚመዘንባቸው መንገዶች መካከል አንዱና ዋነኛው እርበርስ ያለው ግንኙነት ነው ፡፡ የማስረጃው ምዘና ዓላማው ምስክሮች የሰጡት ቃል የተሳሳተ ወይም ትክክለኛ መሆኑን፣እውነት ወይም ሐሰት መሆኑን ፣አጠራጣሪ ወይስ እርግጠኛ መሆኑን ለመለየትና ተፈላጊው የሆነውን የአስረጅነት መመዘኛ አሟልቷል ወይስ አለሟለም ? የሚለውን ለመወሰን በመሆኑ በዚህ ረገድ ምስክሮች የሰጡት ቃል እርስ በርሱ ሲገናዘብ የሚስማማ ወይም የሚለያይ መሆኑን መመርመር አስፈላጊ ነው ፡፡ የማስረጃው ቃል እርስ በርሱ ይገናዘባል ሲባል ደግሞ እያንዳንዱ ምስክር ለዋና ፣ለመስቀለኛ፣እና ድጋሚ ጥያቄ የሰጠው መልስ ካለው ግንኙነት ፣አንድ ምስከር የሰጠውን ቃል ከሌላ ምስክር ቃል ጋር ያለው ግንኙነት መመርመርና መመዘን ያጠቃልላል ፡፡ በምስክሮች ቃል እና በሰነዶች መካካል የሚኖር ቅራኔ ወይም ልዩነት ምዘና በሚመለከት በተከታዩ ምዕራፍ ይታያል ፡፡

## 7.4.1 የምስክሮች ቃል ልዩነት ምዘና

### ሀ. መሰረት

1. የምስክሮች ቃል ልዩነት በሚከተለው መርህ ላይ የተመሰረተ ነው ። ይኸውም ሀሰተኛ ወይም የማይታመን ማስረጃን በመቀበል በዚህ መሰረት መወሰን ተገቢ አይደለም የሚለው ነው ። የአስረጂነት ደረጃው ፍ/ሔር ወይም ወንጀል ከመሆኑ አንፃር ልዩነት ይኖረዋል ። ነገር ግን ሀሰተኛ ወይም የሚታመን ማስረጃ የአስረጂነት ደረጃውን እንደአሟላ ሊቆጠር አይችልም ። ከዚህ አንፃር የምስክሮች ቃል ልዩነት በመመርመር መመዘን የምስክርነት ቃሉ ሐሰተኛ ወይም የማይታመን መሆን አለመሆኑን ለመወሰን ዋነኛው መሳሪያ ነው ።ከዚህ በተጨማሪም ማስረጃ የሚታመን ወይም የማይታመን አውነት ወይም ሀሰት መሆን ሲመዘንና ሲወሰን የሰዎችን የግንዛቤ ደረጃ ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል ። ስለዚህ በምስክሮች ቃል መካከል ልዩነት መኖሩ አጠራጣሪ ፣ሀሰተኛ ወይም የማይታመን ነው ለማለት ግዴታን አያስከትልም ። ሰዎች ስለአንድ ያላቸው የግንዛቤ ደረጃ የተለያየ ስለሚሆን ልዩነት የሚጠበቅ ነው ። ዋናው ቁም ነገሩ ልዩነቱ ፍሬ ነገሩ መኖር አለመኖሩን በተመለከተ በሚወሰድ መመዘኛ ላይ የሚያስረዳው ተፅዕኖ ነው ።(Retanla and Dhirajila p.28) ስለዚህም በምስክሮቹ አመስካከር መካከል የሚታዩ ልዩነቶች አንዳንዶቹ መሰረታዊ በመሆቸው የተነሳ የማይታመን ፣ወይም

## •የቀጠለ

•ሐሰተኛ ወደሚል መደምደሚያ ላይ ሊያደርሱ የሚችሉ ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ ቀላል (minor) ወይም የማይጎዱ (tolerable) ሊሆኑ ይችላሉ ፡፡

3. በሌላ በኩል ደግሞ በምስክሮች መካከል ያለው ተቃርኖ ወይም ልዩነት መሰረታዊ መሆኑ ወይም ቀላል ወይም የማይጎዳ መሆኑን መወሰን ቀላል አይደለም ፡፡ ይህንን በርግጠኛነት ለመለየት የሚያስችል ሁሉንም የሚያስማማ (checklist)ለማዘጋጀት አይቻለም ከዚህ በተጨማሪ የልዩነት ከባድነት ቀላልነት እንደ ጉዳዩ ዓይነት ( ወንጀል ወይም ፍ/ሔር )፣እንደ ምስክሮች አቋም (ፍላጎት የሚያሳዩ ወይም ገለልተኛ እንደመሆናቸው ) ምስክሮች ለፍሬ ነገሩ እንዳላቸው ቅርበት (ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ) ፣እንደምስክሮች የግል ሁኔታ (ህፃን ወይም አዋቂዎች ) ሊወሰን የሚችል ነው ፡፡ ስለዚህ እነዚህን ጉዳዮች ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል ፡፡

4 .ከላይ የተገለፀው ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተለው አጠቃላይ መርህ ተቀባይነት ይኖረዋል ፡፡ምስክር በተናገራቸው ቃላት መካከል ፣ወይም የምስክሮች ቃል እርስ በርሱ ሲገናዘብ የሚታየው ልዩነት ሊያስረዱበት ከመጡት ፍሬ ነገር አንፃር መረታዊ (Substantial )ከሆነ የማይታመን ሊሆን ይችላል ፡፡ ለምሳሌ

ሀ) ምስክሩ ለዋና ጥያቄ በሰጠው መልስ " ተከሳሽ ድርጊቱን ሲፈፀም በስፍራው ሆኜ አይቻለሁ" ካለ በኋላ "አንተ በዚያን ጊዜ ወህኒ ቤት አልነበርክም ወይ ?" በሚል ለቀረበለት መስቀልኛ ጥያቄ በመሰጠው መልስ " አይቻለሁ" ያሉኩት በስህተት ነው ። ዛሬ ከእኔ ጋር ምስክር ሆኖ የቀረበው ሰው ነግሮኝ ነው " ቢል ልዩነቱ መሰረታዊ ነው ። ምክንያቱም ተከሳሹ ድርጊቱን ፈጽሟል የሚለውን መደምደሚያ አያሰጥምና ።

ለ) ምስክሩ ለዋና ጥያቄ በሰጠው መልስ "ተከሳሹ ድርጊቱን ሲፈጽም በስፍራው ሆኜ አይቻለሁ "ከአለ በኋላ "በጨለማ አንተ በዚያ ቦታ ምን ታደርጋለህ ?" በሚል ለቀረበለት ጥያቄ "እኔ መግደሉን ያወቅኩት በዚያን ዕለት ቀን ላይ ዛሬ ማታ ዋጋውን እሰጠዋለሁ እያለ ሲዝት በመስማቴ ነው" የሚል መልስ ቢሰጥ ይህ ልዩነት መሰረታዊ ነው ። ምክንያቱም ምስክሩ አይቻለሁ በሚል በቀጥተኛ ምስክርነት ከሰጠ በኋላ ደረጃውን ወደ አካባቢያዊ ማስረጃ የለወጠ ሲሆን ተከሳሹ ገድሏል በሚል ለመደምደም አያስችልም ።

የቀጠለ . . . .

ሐ) 1ኛ ምስክር ሆኖ የቀበው ሰው በሰጠው የምስክርነት ቃል " ድርጊቱ ሲፈፀም በስፍራው የነበርኩና ያየሁ እኔ ብቻ ነኝ ሌላ ሰው ባለመኖሩ ተከሳሹን ማስያዝ አልቻልኩም “ " ድርጊቱ ሲፈፀም በቦታው የነበርኩት እኔ ነበርኩ ቢል ወይም " 1ኛው ምስክር በስፍራው አልነበረም እኔ ቤት ሔጄ ቀስቅሼው መጣ እንጂ ተከሳሹ ድርጊቱን በፈፀመ ጊዜ አልነበርንም“ ቢል በሁለት ምስክሮች ቃል መካከል ያለው ልዩነት መሰረታዊ ነው ። ምስክሮቹ በስፍራው የነበሩና የተመለከቱ ናቸው ለማለት አያስችልም ።(Retanla and Dhirajila p.28)

5. በዚህ ዓይነት በርካታ ምሳሌዎች መጥቀስ ይቻላል ። ዋናው ልዩነት ተፈላጊውን ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖር ለማረጋገጥ የሚያስችል መሆኑ ነው ። መሰረታዊ ያልሆነ ልዩነት በተመለከተም ለምሳሌ ፦የዓይን ምስክር ሆኖ የቀረበ ሰው ለዐ/ህግ ዋና ጥያቄ በሰጠው መልስ እያንዳንዱ ተከሳሽ ስለፈፀመው ድርጊት ሳያስረዳ “1ኛ ተከሳሽ በዱላ ጀርባው ላይ ደጋግሞ መታው፣2ኛው ተከሳሽ በድንጋይ እግሩ ላይ ደጋግሞ መታው ፣3ኛው ተከሳሽ በጩቤ አንገቱን ላይ ደጋግሞወጋው "በሚል ከመሰከረ በኋላ ለመስቀልኛ ጥያቄ በሰጠው መልስ 1ኛው ተከሳሽ በዱላ እግሩ ላይ ደጋግሞ መታው ፣2ኛው ተከሳሽ በድንጋይ ጀርባው ላይ 1 ጊዜ መታው ፣3ኛው ተከሳሽ በጩቤ አንድ ጊዜ አንገቱን ወጋው" ቢል ይህ ልዩነት መሰረታዊ ነው ለማለት አያስቸልም ። ምክንያቱም 3ቱም ተከሳሾች በድርጊቱ ተሳታፊ እንደነበሩ እና ከያዙዋቸው መሳሪያዎች ጭምር ተመሳሳይነት በመኖሩ ነው ።

## •የቀጠለ. . .

6. ቀላል ልዩነቶች የሚታለፍበት ምክንያት የአንድን ድርጊት አፈፃፀም በሚለከቱ ዝርዝር ጉዳዮች ላይ በሰዎች መካከል የመታዘብ (observation ) የማስተዋል (perception) እና

• የማስታወስ (memory ) ልዩነት በመኖሩና ይህም ተፈጥሮአዊ በመሆኑ ነው የሆነ ሆኖ በጥንቃቄ ሊመረመር የሚገባው ጉዳይ ነው ፡፡

## ለ)ከፊል እውነት ያላቸው የምስክሮች ቃሎች (PARTIAL TRUTH)

ምስክር የሰጠው ቃል እርስ በርሱ ሲመረመር ልዩነት የሚታይበት ሆኖ ነገር ግን አንድነት የሚታይበትና ሊታመን የሚችል ቃልን ያቀፈ ሊሆን ይችላል ፡፡

ወይም በአንድ ፍሬ ነገር ላይ የቀረቡ ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል ልዩነት የሚታይበት ሆኖም እያለ ስምምነት የማይታይባቸውና ሊታመኑ የሚችሉ ቃሎችም ይኖራሉ ፡፡ ነገር ግን ልዩነቱ ሲመዘን መሰረታዊ ሆኖ የታየውን ስምምነት የሚያናጋ ከሆነ( ለምሳሌ ከላይ መሰረታዊ ልዩነት ነው በሚል በተገለፁት ምሳሌዎች ላይ ያለው ልዩነት ምስክሮች በስፍራው አልነበሩም የሚል መደምደሚያ ላይ እንደአደረሰው ዓይነት ማለት ነው ) መሰታዊ ልዩነት በመሆኑ ይመሳሰላሉ የሚባሉት ፍሬ ነገሮችም አብረው ይጣላሉ ፡፡

ነገር ግን **ምስክሮች በቦታው ላይ እንደነበሩ የሚታወቅ ሆኖ** አንዱ በጀርባው በኩል ተኩሶበት ቢልና ሌላኛው በደረቱ በኩል ተኩሶበት ቢሉ በየት በኩል ተኩሶ በሚለው ላይ ልዩነት ቢኖረም በሌሎች ፍሬ ነገሮችም አብረው ይጣላሉ ፡፡

## የቀጠለ . . .

ነገር ግን ምስክሮች በቦታው ላይ እንደነበሩ የሚታወቅ ሆኖ አንዱ በጀርባው በኩል ተኩሶበት ቢልና ሌላኛው በደረቱ በኩል ተኩሶበት ቢል በየት በኩል ተኩሶ በሚለው ላይ ልዩነት ቢኖርም በሌሎች ፍሬ ነገሮች ላይ የሰጡት ምስክርነት በስፍራው ነበሩ የሆነትን ፍሬ ነገሮች መሰረት በማድረግ ፣ከድርጊቱ አፈፃፀም አካባቢያዊ ሁኔታ ጋር እና ከሌሎች ደጋፊ ማስረጃዎች (ለምሳሌ የህክምና ማስረጃ )ጋር በማገናዘብ መመዘን ያስፈልጋል ፡፡

ሐ) አንድ ምስክር ለዋና ጥያቄ መልስ መሰጠት ሲጀምር የተናገረው ቃል ጠያቂውን ያላረካው በመሆኑ ለሚቀርብለት ቀጣይ ጥያቄ ቀደም ሲል የሰጠውን መልስ የሚያርም ወይም የሚያስተካክል መልስ ሊሰጥ ይችላል ፡፡ እንዲሁም ለመስቀለኛ ጥያቄ መልስ መሰጠት ጀምሮ ለዋና ጥያቄ የሰጠው መልስ የተባላሸበት መስሎ ሲሰማው በማስተካከል መልስ የሚሰጥበት ሁኔታ ይኖራል ፡፡ ወይም ደግሞ ለድጋሚ ጥያቄ በሚሰጠው መልስ ለመስቀለኛ ጥያቄ የሰጠውን መልስ የሚያርም ወይም የሚያስተካክል መልስ ሊሰጥ ይችላል ፡፡ እንዲህ ዓይነቱ የምስክርነት ቃል በማቅናት የተሰጠ (improvement ) ይባላል ፡፡ ከማስረጃ ምዘና አንፃር የሚፈጥረው ችግር ተፈላጊውን ፍሬ ነገር ከማስረዳት አኳያ መጀመሪያ የተሰጠው መልስ እና ተቃንቶ የተሰጠው መልስ የተለያዩ መደምደሚያ ላይ ሊያደርሱ የሚችሉበት ዕድል ሊኖር መቻሉ ነው ፡፡

## የቀጠለ

2.በመሰረቱ ይህ በማቅናት መልስ መስጠቱ በራሱ ምስክርነቱን ውደቅ አያደርገውም ። እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሲፈጠር ምስክሩ ቃሉን ለማቅናት የቻለበት ምክንያት ሊመረመር ይገባዋል ።

ማለትም

- በአነጋገር የተሳተውን ለማስተካከል መሆኑ፣ወይም
- ጥያቄውን በሚገባ ሳይረዳ የሰጠውን መልስ ለማስተካከል መሆኑ ከታወቀ ተቀባይነት እንዲኖረው ማድረግ የሚቻል ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በማቅናት መልሱን የሰጠው ትክክለኛውን ነገር ለመሰወር ከሆነ ወይም ለማቅናት ምክንያት የሆነው ነገር የማይታወቅ ከሆነ መጀመሪያ የሰጠው ቃል ይወሰዳል

### መ)ማጋነን የሚታይበት የምስክርነት ቃል (EXAGGERATION)

- አንዳንድ ምስክሮች የሚሰጡት የምስክርነት ቃል ሊያስረዱበት ከቀረቡበት ፍሬ ነገር አፈፃፀም አንፃር የተጋነነ ሊሆን ይችላል ። በተመሳሳይ ጉዳይ ለማስረዳት የቀረቡት ምስክሮች ከገለፁት በተለየ የድርጊቱን አፈፃፀም ወይም የተከሳሽ ተሳትፎን በማጋነን የምስክርነት ቃል ሊሰጡ ይችላሉ ። ሌሎች ደግሞ ምስክርነታቸውን እንዲታመኑላቸው ሲሉ የመገንዘብ ችሎታቸውን ከፍ በማድረግ ወይም በማጋነን ይገልፃሉ ። ሊመሰከርበት የመጣው ጉዳይ በጨለማ የተፈፀመ በሆነበት ሁኔታ ጨለማም ቢሆን የማየት ብቃት እንዳለው ለማስመሰል "በሌሊት ጥበቃ ሥራ የረጅም ጊዜ ልምድ ስላለኝ ከጨለማ ጋር ተለማምጃለሁ " እንደሚል ምስክር ዓይነት ማለት ነው ።

•**የቀጠለ . . .**

•**የተጋነነ የምስክርነት ቃል የሚኖረው ዋጋ** የሚለካው ከተያዘው ጉዳይ አንፃር እየታየ (case by case ) ሲሆን ማስረጃው ሲመዘንም ከሌሎች ጋር ያለው ዝምድና ወይም ግንኙነት በጥንቃቄ እየተፈተሸ መሆን አለበት ፡፡ የተጋነነውን ነጥሎ ማውጣት አስፈላጊ ይሆናል ፡፡ እንዲሁም ምስክሩ ሊያስረዳበት የመጣው ፍሬ ነገር አፈፃፀምና አካባቢያዊ ሁኔታዎች ግምት ውስጥ ሊገቡ ይገባል ፡፡የምስክሮች በሁለተኛ ድርጊት ላይ የሰጡት ምስክርነት ሀሰተኛ መሆኑ በመጀመሪያው ድርጊት ላይ የሰጡን የምስከርተ ቃል ውድቅ ያደረገዋ?

## 7.4.2. የምስክሮች ቃል ተመሳሳይነት ስለሚያስከትለው ውጤት

1.የምስክሮች ቃል ዕርስ በርስ ሲገናዘብ ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፍተኛ ደረጃ ተመሳሳይ መሆን የሚደገፍ ነው ፡፡ ነገር ግን ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል ሙሉ ለሙሉ መመሳሰል የምስክሮች ቃል ምንም የማይወጣለት እውነት ነው ብሎ በርግጠኛነት መደምደም አይቻልም ፡፡ ስለዚህም ማስረጃው ተመሳሳይ ሆኖ ቢገኝ እንኳን መገምገምና መመዘን አስፈላጊ ነው ፡፡

## •የቀጠለ. . .

•የአገራችን ፍ/ቤቶች ማስረጃ ተመሳሳይ በሆነ ጊዜ የሚወስዱት አቋም ሲታይ በአብዛኛው የማስረጃው ግምገማ የሚያተኩረው በመከላከያ ማስረጃዎች የምስክርነት ቃል ነው ፡፡የዐ/ህግ ምስክሮች ቃል ተመሳሳይ ሲሆን " ደግሞ "የመከላከያ ምስክሮች የሰጡት ቃል ተመሳሳይነት ቢኖረውም በጥናት ላይ የተመሰረተ ነው " በማለት ውድቅ ሲያደርጉት ይስተዋላል ፡፡ ይህ አንደ አቋም መወሰድ የሌለበት ነው ፡፡የምስክርነት ቃሉ ተመሳሳይነት ቢኖረውም የተለያዩ የመመዘኛ ስልቶች በመከተል እውነትነቱ ሊጣራ የሚገባው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ምዘናው ግን የዐቃቤ ህግንም ሆነ የመከለከያ ማስረጃን የሚያጠቃልል ነው ፡፡ በዚሁ መሰረት እንዲሁም ዓይነት የምስክርነት ቃል ሲመዘን

•የምስክሮቹ ቃል ትክክለኛነት ሊያስረዱ ከቀረቡበት ጭብጥና ከተከሰተበት ጊዜና ቦታ አንፃር ሊመዘን ይገባል ፡፡ ምስክሮች በዚያ ጊዜና ቦታ ለመገኘት ያላቸው አጋጣሚ ይመረመራል ፡፡

•ምስክሮች ያስረዱበታል የተባለው ድርጊት ተከሰተ በተባለበት እና ምስክሮች ችሎት ቀርበው በመስከሩበት ጊዜ መካከል ያለው ርቀት ግምት ውስጥ ሊገባ ይገባል ልዩነቱ -ሰፊ በሆነ መጠን በተመሳሳይ ሁኔታ የሚታወስ ዕድል ሊኖር መቻሉ ነው ፡፡

• የቀጠለ. .

•ሊያስረዳ የቀረበበተ ፍሬ ነገር ዓይነት ግምት ውስጥ ሊገባ ይችላል (አደጋን ሐይማኖታዊ በዓላትን በሚገባ በማስተዋል ከረጅም ጊዜ በኋላም ለማስታወስ የሚቻል ሲሆን ተራ ክስተቶችን ግን ብዙ ሰዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ለረጀም ጊዜም በኋላም ለማስታወስ ይከብዳቸዋል ።)

•ምስክሮች የሚመሰክሩበት ፍሬ ነገር አንድ ላይ ሆነው እንዴት ለመከታተል እንዲችሉ መመርመር አለበት ።

•ምስክሮ ከምስከር አቅራቢው ሰው (የዐ/ህግ ምስር ከሆነ ከግል ተበዳይ )ጋር ያላቸው የግል ወይም ህበራዊ ግንኙነቶች ሊታይ ይገባል ። በዝምድና ፣በወዳጅነት የሚተሳሰሩ ምስክሮች ከማይተዋወቁ ምስክሮች የተሻለ የመጠናናት ዕድልና ፍላጎት ሊኖራቸው ይችላል ።

## 7.5 ሳይጠቀሱ የታለፉ ፍሬ ገገሮች(OMISSIONS) የሚያስከትሉት ውጤት

•ስለ አንድ ፍሬ ነገር ወይም አለመኖር ፣ለማስረዳት የቀረቡ ምስክሮች በቂና የተሟላ መረጃ በሲጡ ምስክሮች የሰጡት ቃል የአስረጅነት መመዘኛውን አለሟሟላቱን ለመወሰን የበለጠ እንዲሚረዳ የሚታወቅ ነው ። ሆኖም የቀረቡት ምስክሮች ሳይጠየቁ በመቅሬታቸው ወይም ተጠይቀውም ማስታወስ ባለመቻላቸው ምክንያት ያልተጠቀሱ ነገሮች ይኖራሉ ። ከዚህ አንፃር ሳይጠቀሱ የተላፉ ነገሮች በማስረጃ ምዘና ላይ የሚያሳድሩት ተፅህኖ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ። ጉዳዩ ወንጀል ወይም ፍ/ሔር መሆኑ ልዩነት ሊፈጥር የሚችል ቢሆንም ሳይጠቀሱ የሚታለፉ ፍሬ ነገሮች በሁለቱም ጉዳዮች ላይ ተጽህኖ ሊያስከትሉ እንደሚችሉ ማወቅ ይገባል ።

## የቀጠለ. . .

2. ሳይጠቀሱ ወይም ሳይገለፁ ወይም ሳይቀርቡ የሚታለፍ ፍሬ ነገሮች በመሰረቱ ምስክሮች በሰጡት ቃል ውስጥ የሚንፀባረቁ ቢሆኑም ከዚህ አልፎም ሌሎች ማስረጃዎችንም ሊመለከት ይችላሉ ፣ ከዚህ አንፃር ሊታይ የሚገባው ነው በዚሁ መሰረት

- ድርጊቱን ለመፈፀም ያነሳሳ **ምክንያት (motive** ) ሳይገለጽ ቢቀር፣
- ድርጊቱን መፈፀሙን ወይም ተፈጽሞም ከሆነ የምክንያትና ውጤት ግንኙነት ለማጋገጥ የሚያስችል ማስረጃ አለመቅረብ (የህክምና ማስረጃ አለመቅረብ )
- ደርጉቱ የተፈፀመበት መሳሪያ አለመቀርብ ወይም አለመታወቅ
- ጊዜና ቦታው አለመገለጽ አዘውትረው የሚያጋጥሙ ሲሆኑ ዋና ዋናዎቹ (ማለትም መነሻ ምክንያት አለመግለጽ የህክምና ማስጃ አለመቅረብና ድርጊቶች የተፈፀሙበት መሳሪያ አለመቅረብ ) የምስክሮችን ቃል በመመዘን ረገድ የሚያስከትለውን አስተዋጽኦ ቀጥሎ ይገልፃል ።

## 7.5.1. ድርጊቱ ለመፈፀም ያነሳ (MOTIVE) አለመገለጽ

**1.** ማስረጃ ሊያስረዳበት የቀረበው ጭብጥ ወይም ፍሬ ነገር አንድ አድራጎትን የሚመመለከት የሆነ እንደሆነ ይህንን ድርጊት ለመፈፀም ያነሳሳ ምክንያቶ መታወቅ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው ። በተለየም በወንጀል ጉዳይ ላይ ይህ መታወቁ አስፈላጊነቱ ከፍተኛ ነው የጥፋተኛነት ውሳኔን ከማስገኘት አንፃር ወንጀሉን የሚያቋመውን የሀሳብ ክፍል ለማረጋገጥ ድርጊቱን ለመፈፀም ያነሳሳው ምክንያት መታወቅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው ። ለምሳሌ የስርቆት ወንጀልን ለማረጋገጥ ″ ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለራስ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ″ መወሰዱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ መኖር ተገቢ ነው ።

## የቀጠለ

2. በሌላ በኩል ደግሞ የቀረበው ማስረጃ ድርጊቱን መፈፀሙን ቢያስረዳም ለመፈፀም ምክንያት የሆነው ፍሬ ነገር አለመጠቀሱ ማስረጃውን ሁል ጊዜም ሚዛን ያሰጠዋል ለማለት አይቻልም ፡፡በብዙ የወንጀል ጉዳዮች ላይ ድርጊቱን ለመፈፀም ያነሳሳ ምክንያት ከሀሳብ ክፍሉ ጋር የማይገናኝ ሊሆን እንደሚችል መታወቅ አለበት ፡፡ ለምሳሌ በቸልተኛነት ለሚፈፀም ወንጀል የሀሳብ ክፍሉ ተገቢ ጥንቃቄ አላማድረግ ስለሚሆን ከዚህ አልፎ ድርጊቱን ለመፈፀም ያነሳሳው ምክንያት (motive ) መረጋገጥ አለበት የሚል አቋም መውሰድ አይገባም ፡፡ በተጨማሪም የድርጊቱን አፈፃፀም የሚያስረዳ ማስረጃ እግረ መንገዱን ምክንያቱን ለማረጋገጥ ሊረዳ ይችላል ፡፡ከባለቤቱ ፍቃድ ውጭ የሰው ቤት ዘው ብሎ ገብቶ ዕቃ ወስዶ የተገለገለበት እንደሆነ ንብረቱን የወሰደው << ተገቢ ያልሆነ ልጽግና ለራሱ ለማግኘት በማሰብ >> መሆኑን ድርጊቱ ራሱ ያረጋግጥልናል ፡፡ ስለዚህ ድርጊቱን ለመፈፀም መነሻ ምክንያት መጠየቅ አስፈላጊ መሆኑን አስቀድሞ መመርመር ያስፈልጋል ፡፡

- ድርጊቱን ለመፈፀም ምክንያቱ ከድርጊቱ አፈፃፀም ሊታወቅ የሚችልበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል ማወቅ ያስፈልጋል ፡፡

• **የቀጠለ**

• ይኸው ምክንያት አስፈላጊ መሆኑ ተረጋግጦ ነገር ግን የቀረበው ማስረጃ ላይ ያልተገለፀና ከተጠቀሰው የማስረጃ ቃልም የማይገኝ ከሆነ በውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሚያስከትለውን ውጤት ከድርጊቱ አፈፃፀም አካባቢያዊ ሁኔታዎች ጋር በማገናዘብ መመርመር ያስፈልጋል ፡፡

## 7.5.2 . የህክምና ማስረጃ ስለማቅረብ

1. በአካል ወይም በህይወት ላይ በደረሰ ጉዳት ምክንያት ለሚቀርብ የወንጀል ወይም የፍ/ሐር የጉዳት ካሳ ጉዳይ የህክምና ማስረጃ መቅረቡ የሚሰጠው አገልግሎት ከፍተኛ ነው ፡፡ ይህ ማስረጃ መቅረቡ ፡-

• ምክንያትና በውጤት መካከል ያለውን ግንኙነት ለማረጋገጥ ያስችላል ፣

• የተከሰሰው ሰው ፈፀመው የተባለውን በምስክሮች የተናገረው ድርጊት (ግድያ ወይም አካል ማጉደል )በርግጥም የተፈፀመ መሆኑን ለማረጋገጥ ፣

የጉዳቱን ደረጃና መጠን ለማወቅ (በወንጀል ከባድ የአካል ጉዳት ነው ወይስ ቀላል የሚለውን ለማወቅ ፣በፍ/ሐር ደግሞ የጉዳቱን ደረጃና የካሳውን መጠን ለመወሰን ) ያገለግላል ፡፡

የቀጠለ.

በሌላ በኩል ደግሞ ተፈላጊው ፍሬ ነገር መኖሩን ወይም አለመኖሩን ለማረጋገጥ የህክምና ማስረጃ የግዴታ መቅረብ አለበት መባል የለበትም። ሰው ሲሞት ወይም የአካል ጉዳት ሲደርስበት በሐኪም መመርመር አለበት የሚል አስገዳጅ ደንብ በሌለበት ሁኔታ፤ ህክምና ለማግኘት የማይቻልበት በርካታ ምክንያት መኖሩ እየታወቀ ፍሬ ነገሩ መኖሩ ወይም አለመኖሩ በህክምና ማስረጃ አልተረጋገጠም፤ ወይም አልተደገፈም በሚል ምክንያት ምስክሮች የሰጡትን ቃል መመዘንና ይኸው ቃል በራሱ ፍሬ ነገሩ መኖሩን የሚያረጋግጥ ከሆነ ወደዚህ መደምደሚያ ላይ መድረስ ይገባል። ስለዚህ ጠንካራ መሰረት ያለው የምስክርነት ቃል በህክምና ማስረጃ አልተደገፈም ተብሎ ውድቅ ሊደረግ አይገባም።

## የቀጠለ.

. **ሌሎች ያለተገለፀ ፍሬ ነገሮች ወይም ማስረጃዎች**

1. በወንጀል ጉዳይ ወንጀል የተፈፀመበት መሳሪያ ወይም የወንጀል ውጤት የሆነ ነገር በማስረጃነት ሳይቀርብ ሊታለፍ ይችላል፤ ወይም ምስክሮች ሳይገልፁት ሊያልፉ ይችላሉ ወይም  ቀርቦ እያለ ምስክሮች ለይቶ ለማመልከት ሊቸገሩ ይችላሉ። ወይም ድርጊቱን ፈፀመ በሚል ስሙን የገለፁትን ሰው እንዲያሳዩ ሲጠየቁ ማሳየት ሊያቅታቸው ይችላል። ይህ በምስክሮች ቃል ምዘና ላይ የሚያስከትለው ተፅዕኖ ምንድነው? የሚለው በጥንቃቄ መታየት የሚገባው ነው።
2. ወንጀል የተፈፀመበትን መሳሪያ ወይም የወንጀል ፍሬ የሆነ ዕቃ በኢግዚቢትነት መቅረቡ ማስረጃውን ውድቅ ያደርገዋል በሚል መደምደም አይቻልም። ኤግዚቢቱን በማየት ፍ/ቤቱ የተሻለ ግንዛቤ መውሰድ ይችል የነበረውን ዕድል ያስቀርበታል። ነገር ግን የምስክርነት ቃሉን ራሱን ችሎ እንዳይመዘን ከማድረግ አይከለክልም።

የቀጠለ...

ምስክሩ ድርጊቱ የተፈፀመበትን መሳሪያ ሳይገልፅ ቢያልፍ ወይም ደርጊቱ ያስገኘውን ዕቃ ሳይገልፅ ቢቀር ይህ ጉድለት ለሚለካው የክስን መሠረታዊ ፍሬ ነገሮች ለማረጋገጥ ካለው ድርሻ አንፃር ነው። ሰርቋል የተባለውን ንብረት ምስክሩ ሳይገልፅ ከቀረ የስርቆት ወንጀል ተፈፅሟል ለማለት አያስችልም። ገድሏል ተብሎ ለቀረበ ክስ ድርጊሩ የተፈፀመበት መሳሪያ ሊገልፅ ይገባዋል። ይህ መሰረታዊ ነገር ነው። ነገር ግን በጠመንጃ መሆኑ ተገልፆ ባለበት ሁኔታ "የጠመንጃውን አይነት ለይቶ አልገለፀም በሚል""ገድሏል" የሚለውን የምስክርነት ቃል ውድቅ ማድረግ አይቻልም።

4. ችሎት የቀረበው ምስክር የምስክርነት ቃሉን ከሰጠ በኋላ ድርጊቱን ፈፅሟል። በሚል የጠቀሰውን ሰው ወይም ፈፅሞበታል ያለውን መሳሪያ እንዲያሳይ ሊጠየቅ ይችላል። ይህ የሚስከትለው ውጤት ግን በጥንቃቄ ሊመዘን ይገባዋል። በዚህም መሰረት፡-

## • የቀጠለ...

• ምስክር ድርጊቱን ፈፀመ በማለት በስም የጠቀሰውን ሰው እንዳያሳይ ወይም እንዲለይ ተጠይቆ ማሳየት ቢያቅተው ይህ ሁኔታ በማስረጃ ምዘና ላይ ከሚያስከትለው ተፅዕኖ አንፃር ሊፈተሽ ይገባዋል። ድርጊቱን ፈፅሟል የተባለውን ሰው በጊዜው እንዴት አወቀው? ስሙን ማን ነገረው? አሁንስ እንዴት ማሳየት አቃተው? የሚሉት ጥያቄዎች ሊቀርቡና ማስረጃው ለነዚህ ጥያቄዎች በሚሰጠው ምላሽ መሰረት ሊመዘን ይገባል፤

• ማስረጃውን ወይም ዕቃውን ማሳየት አለመቻልም እንዲሁ ምስክሩ ድርጊቱ ሲፈፀም ከነበረው ቅርበት፣ ከጊዜው ሁኔታ ... አንፃር መለካት አለበት።

የቀጠለ...

## 7.6. ጥቅም ያላቸው ምስክሮች የምስክርነት ቃል ምዘና

በወንጀልም ሆነ በፍትሐብሔር ጉዳይ (አስረጅነት ደረጃው እና በማስረጃ ምዘና ሂደት የሚሰጠው ክብደት የተለያየ ቢሆንም) በምስክርነት የሚቀርቡ ሰዎች በሚመሰከሩበት ጉዳይ አወሳሰን ላይ የተለየ ጥቅም ወይም ፍላጎት ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ተከራካሪ ወገኖች በራሳቸው ጉዳይ ምስክር በመሆን (በወንጀል ጉዳይ የግል ተበዳዩን ይጨምራል)፣ ወይም ምስክሮቹ ከተከራካሪ ወገኖች ጋር ባላቸው ፀብ፣ ዝምድና ወይም የተለየ የጥቅም ተጋሪነት ወይም ወዳጅነት መነሻ ወገንተኛነት በማሳየት በጉዳዩ አወሳሰን የተለየ ፍላጎት ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ወይም ደግሞ አብረው በግብረ አበርነት ከተከሰሱት መካከል ወይም በፍትሐብሔር ጉዳይ ተጣምረው ከከሰሱት መካከል አንደኛው በሌላኛው ላይ ወይም ሌላኛው ምስክር ሆነው ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ግንኙነት ያላቸው እና ወገንተኛ ይሆናሉ ተብለው የሚጠረጠሩ ሰዎች የተለየ ጥቅም ያላቸው ምስክሮች **(interested witnesses)** የሚባሉ ሲሆን የምስክርነት ቃላቸው ሲመዘን ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህ ክፍል እንደነዚህ ዓይነት ምስክሮች የሚሰጡት ቃል ሲመዘን ግምት ውስጥ ማስገባት የሚገቡ ነገሮች በአጭሩ ይገለፃሉ፡፡

የቀጠለ . ..

## 7.6.1. ፀብ ወይም ዝምድና

1.ምስክሮች ከተከራካሪ ወገኖች ጋር ፀብ ወይም ዝምድና ቢኖራቸውም ከመመስከር ሊከለከሉ አይችሉም። ሆኖም ፀብ ወይም ዝምድና መኖሩ ከታወቀ የምስክርነት ቃላቸው እውነት መሆኑ ወይም ደግሞ በዚህ ፀብ ወይም ዝምድና መነሻ የተፈጠረ፣ የተጋነነ ወይም የተምታታ መሆኑ በጥንቃቄ ሊመዘን ይገባዋል።

2. ፀብ ወይም ዝምድና መኖሩ አስቀድሞ ሊረጋገጥ የሚገባው ነገር ነው። ዝምድና ትርጉሙ ሊሰፋም ሊጠብም የሚችል መሆኑ መታወቅ አለበት። በጎሳ ላይ የተመሰረተ ዝምድና ሊጠቀስ የሚችለውን ያህል ቅርብ የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድናም ከዝምድና የማይቆጠርበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል። ፀብን በተመለከተም ማናቸውም ዓይነት አለመግባባት ፀብ ያሰኛል ማለት አይቻልም። የሆነ ሆኖ ፍ/ቤቱ የምስክርነት ቃሉን ሲመዘን ይመሰክሪበታል ከተባለው ፍሬ ነገር ወይም ጭብጥ አካባቢያዊ ሁኔታ አንፃር ማየትና የተሰጠው የምስክርነት ቃል እውነተኛ መሆኑን፣ ወይም ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት በማሰብ የተቀነባበረ፣ የተጋነነ ወይም የወረደ መሆኑን ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል።

## የቀጠለ . ..

## 7.6.2. የተከራካሪ ወገን ምስክርነት

1. በወንጀልም ሆነ በፍትሐብሔር ተከራካሪ ወገኖች በራሳቸው ጉዳይ የምስክርነት ቃል ሊሰጡ ይችላሉ። በወንጀል ጉዳይ የግል ተበዳዩ (በከሳሽ ዐቃቤ ህግ በኩል) እና ተከሳሹ በፍትሐብሔር ጉዳይ ደግሞ ከሳሽና ተከሳሽ በራሳቸው ጉዳይ ምስክር መሆን ይችላሉ።

2. በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህ ምስክሮች በጉዳዩ አወሳሰን የተለየ ፍላጎት ሊኖራቸው እንደሚችልና እንደሚጠበቅም መታወቅ አለበት። ከዚህ አንፃር፡-

- ከግል ተበዳይ ውጭ ያሉ ከሳሽም ሆነ ተከሳሽ የሚሰጡት ቃል ክርክራቸውን የሚጠናክር በመሆኑ ምስክርነታቸው ክብደት ሊሰጠው አይገባም።
- በወንጀል ጉዳይ የግል ተበዳይ ምስክር ሆኖ በራሱ ላይ ስለ አደረሰው ጉዳት የሚሰጠው የምስክርነት ቃል እውነተኛነቱ ተፈፀመ ከተባለው ድርጊት ከባድነት እና ከአፈፃፀሙ አካባቢያዊ ሁኔታ አንፃር ሊገመገም ይችላል። ከባድ የአካል ጉዳት ደረሰበትና (ለምሳሌ አይን መጥፋት) ይህንን ለማስረዳት የመጣ የግል ተበዳይ አይኑ መጥፋቱ እስከተረጋገጠ ድረስ አይኑን ያጠፋውን ሰው ትቶ ሌላ ሰው ይወነጅላል ለማለት አዳጋች ሊሆን ይችላል። በዚህ ጊዜ ዋናው መመዘኛ ምስክሩ ድርጊቱን የፈፀመው ተከሳሽ መሆኑን ሊያረጋግጥ የቻለበት ሁኔታ ነው።

## የቀጠለ . . .

በሌላ በኩል ቀላል ጉዳት ወይም የእጅ እልፊት ወይም ስም ማጥፋትን ለማስረዳት የሚቀርብ የግል ተበዳይ የሰጠው የምስክርነት ቃል ከሆነ እውነቱ በከፍተኛ ጥንቃቄ ሊመረመር ይገባል፡፡

- እንዲሁም አንዳንድ ወንጀሎች በባህሪያቸው ከግል ተበዳይ ሌላ ማስረጃ ሊገኝ የማይገባቸው፤ ወይም የግል ተበዳይ በርግጥ ካለተፈፀመበት በስተቀር አደባባይ የማያወጣቸው ሊሆኑ ስለሚችሉ ይህም በማስረጃ ምዘና ግምት ውስጥ ሊገባ ይገባል፡፡ ለምሳሌ በአብዛኛው የመደፈር ወንጀል የሚፈፀመው ከግል ተበዳይ ውጭ ሌላ ሰው በሌለበት ሁኔታ ሲሆን ተደፍራለች የተባለችው ሴትም መደፈርዋ እርግጥ ካልሆነ በስተቀር (አንዳንዴ ተደፍሬያለሁ የሚባልበት የተለየ ምክንያት ቢያግጥምም) ተደፍሬያለሁ ብላ አደባባይ ስለማትወጣ ማስረጃው ክብደት ሊሰጠው ይገባል፡፡ በሌላ ደጋፊ ማስረጃ አላስረዳህም የሚል ግዴታ መጣልም አይቻልም፡፡

### 7.6.3. የግብረ አበር ምስክርነት

በመሰረቱ ግብረ አበር የሆነ ሰው አብሮት በተከሰሰው ላይም ሆነ ለዚሁ ሰው ምስክር እንዳይሆን የሚከላከል ህግ የለም። በፍትሐብሔር ጉዳይ በጣምራ የከሰሱ ወይም የተከሰሱ ሰዎችም አንደኛው ለሌላኛው ሊመሰክሩ ይችላሉ። ያም ሆኖ ግን አብሮት ለከሰሰው ወይም ለተከሰሰው ሰው በመርዳት ወይም ኃላፊነቱን ከራሱ አውርዶ አብሮት የተከሰሰው ሰው ኃላፊነቱን እንዲሸከም በማድረግ ዓላማ በመጉዳት የምስክርነት ቃሉን ሊሰጥ ይችላል። ስለዚህ የምስክርነት ቃላቸው ሲመዘን በዋናነት ለመመስከር የተነሳሱበት ምክንያት ግምት ውስጥ መግባት አለበት።

## 7.7. ልዩ መደብ ያላቸው ምስክሮች ቃል ምዘና

### 7.7.1. የህፃናት ምስክርነት ቃል ምዘና

1. ህፃናት የሚጠየቁትን ጥያቄ መገንዘብና መልስ መስጠት እስከቻሉ ድረስ በምስክርነት ከመቅረብ እንደማይከለከሉ አስቀድሞ ተገልፆአል። ነገር ግን የሚሰጡት የምስክርነት ቃል በጥንቃቄ ሊመዘን ይገባዋል። በጥንቃቄ ሊመዘን ይገባል የተባለውም "ህፃናት ማስረጃ ስለሚሆኑበት ጉዳይ በሌሎች ሰዎች ተፅዕኖ" ስር በቀላሉ ሊወድቁ ስለሚችሉና ሊደለሉም ስለሚችሉ ከተገነዘቡት ፍሬ ነገር ውጭ በሰዎች ግፊት ትክክለኛ ያልሆነ ምስክርነት ይሰጣሉ" የሚል ስጋት ነው። (May, p 462)

የቀጠለ . . .

2. በዚህም መሰረት የህፃናት የምስክርነት ቃል ሲመዘን፡-

• ዕድሜያቸው ግምት ውስጥ ሊገባ ይገባል። ዕድሜያቸው ትንሽ በሆነ መጠን የመደለል ወይም በሌላ ተፅዕኖ ሥር የመውደቅ ዕድላቸው የሰፋ ሊሆን ይችላል።

• የሰጡት የምስክርነት ቃል ከሌሎች ማስረጃዎች ጋር ያለው አንድነትና ልዩነት መገናዘብ ይኖርበታል፤

• ይመሠከሩበታል የተባለው ፍሬ ነገር በተከሰተበትና ቀርበው በመሰከሩበት ጊዜ መካከል ያለው ልዩነት ግምት ውስጥ ሊገባ ይገባል። ጊዜው ሰፊ በሆነ ቁጥር የማስታወሱ ሁኔታ እየደከመ ይሄዳል ተብሎ ይገመታል። (May, p 463)

## 7.7.2. በዕድሜ የገፉ፣ የአካል ወይም የአእምሮ ጉድለት ያለባቸው ምስክሮች ቃል ምዘና

በማስረጃነት የቀረቡት ምስክሮች የዕድሜ መግፋት የተነሳ የማስታወስ ችሎታቸው የጠፋ ባይሆንም የደከመ ሊሆን ይችላል። ወይም በአእምሮ ወይም በአካል ጉዳት የተነሳ ምስክርነታቸው የተሟላ ላይሆን ይችላል። ያም ሆነ ይህ በምስክርነት እስኪቀርቡና ቃላቸውን እስኪሰሙ ድረስ የሰጡት የምስክርነት ቃል ሊመዘን ይገባዋል። እነዚህ ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃልም በሌላ ደጋፊ ማስረጃ መታገዝ አለመታገዙን ማረጋገጥ ጠቃሚ ነው።

## 7.8.3. የኤክስፐርት ማስረጃ ምዘና

1. ኤክስፐርት ወይም ልዩ አዋቂዎች ችሎት ቀርበው የምስክርነት ቃላቸውን በሚሰጡበት ጊዜ ምስክርነታቸው ሳይመዘን በቀጥታ አስረጅነትን ያገኛል ማለት አይቻልም። ኤክስፐርት የሰጠው ምስክርነት ነው ስለተባለ ፍ/ቤቱ እንዳለ በጥሬው መቀበል አይገባውም። ከሌሎች ማስረጃዎች የተለየ ክብደት ይሰጠዋል ማለትም አይደለም። (አለማየሁ ኃይሌ ይኬ፣ ገፅ 63)

2. ስለዚህም ፍርድ ቤቶች የኤክስፐርት ማስረጃን እንዳለቀ ነገር አድርገው ለመቀበል የማይገደዱ ሲሆን ይህንን ማስረጃ፡-

- ስለተሰጠው የኤክስፐርት አስተያየት ትክክለኛነት የቀረቡ ማረጋገጫዎችን
- ኤክስፐርቱ አስተያየቱን ወይም መደምደሚያውን የሰጠው የራሱን እውቀትና ምርመራ ተጠቅሞ ወይም ሌላ ባለሞያነቱን ፍ/ቤቱ ያላረጋገጠውን ሰው ጠይቆ ያገኘውን መረጃ መሰረት በማድረግ መሆኑን፣
- ኤክስፐርቱ በተያዘው ጉዳይ ላይ ያለውን ገለልተኛነት (ማለትም ኤክስፐርቱ የተጠራው በማን ወገን ነው ከጉዳዩ ጋር ያለው የግል ግንኙነትስ ምን ይመስላል ከሚሉት ጥያቄዎች አንፃር)፣
- ኤክስፐርቱ እንዲያረጋግጥ ወይም አስተያየት እንዲሰጥ ከተሰጠው መመሪያ ወይም ጥያቄ ጋር የተሰጠው አስተያየት ያለውን ግንኙነት ... ወዘተ

መሰረት በማድረግ ሊገመግመው ይገባል። (አለማየሁ ኃይሌ ገፅ 63፣ የጠ/ፍ/ቤት ፍ/ይ/መ/ቁ. 201/77)

# ምዕራፍ 8

## የሰነዶችንና ኤግዚቢት ማስረጃዎችን አስረጂነት ስለመመዘን

### 8.1. ጠቅላላ

1. በፍትሐብሔርም ሆነ በወንጀል ጉዳይ ፍሬ ነገርን ለማስረጃነት ወይም ለማስተባበል ሰነዶችና ኤግዚቢቶች በማስረጃነት ሊቀርቡ እንደሚችሉ፤ በማስረጃነት ሲቀርቡ ግን አግባብነት እንዳላቸውና መቅረባቸውን የሚከላከል ህግ አለመኖሩ ሊረጋገጥ እንደሚገባ በምዕራፍ 3 ላይ ተጠቅሷል። የአንዳንድ ፍሬ ነገሮችን መኖር ለማረጋገጥ ወይም ለማስተባበል የሰነድ ማስረጃዎች ብቻ ሊቀርቡ እንደሚገባ ህግ የሚደነግግበት ሁኔታ መኖሩን ተመልክቷል።

2. በዚህ ምዕራፍ የሚገለፀው ደግሞ የሰነድ ማስረጃዎች ወይም ኤግዚቢቶች ማስረጃ ሆነው ከቀረቡ በኋላ የሚመዘኑበት ሁኔታ ነው። ማለትም የሰነድ ማስረጃ ወይም ኢግዚቢቶች የተፈለገውን ፍሬ ነገር መኖር ማስረጃነቱን ወይም ማስተባበሉን ለመወሰን ማስረጃ ምዘና ተግባር ሲከናወን ግምት ውስጥ ሊገቡ ስለሚገባቸው ጉዳዮች በዚህ ምዕራፍ ትኩረት ይሰጣል።

3.ወደ ዝርዝር ጉዳዮች ከመገባቱ አስቀድሞ ግን የሚከተለው ሐሳብ በማስታወሻነት ሊያዝ ይገባዋል። ይኸውም ሰነዶችና ኤግዚቢቶች አግባብነት አላቸው የተባሉትን ፍሬ ነገሮች ከማስረዳት አንፃር አስተማማኝ ቢመስሉም ነገር ግን በጥልቀት ሲመረመሩ እና ሲመዘኑ አስተማማኝነታቸው ከምስክሮች ቃል የተሻለ ላይሆን ይችላል። የጽሁፍ ሰነድ፣ ወይም ካሴት፣ ወይም ፎቶግራፍ ... ወዘተ ቀረበ ስለተባለ ከምስክር ቃል የበለጠ በአስተማማኝነት የሚያስረዳ መስሎ ቢታይም ነገር ግን አስተማማኝነቱን ሊሸረሽሩ ለሚችሉ በርካታ ጥያቄዎች የተጋለጠ ነው። ምስክሮች የፈለገ ተዘጋጅተው ቢቀርቡ ችሎት ላይ ከሚከናወን መስቀለኛ ጥያቄ ጋር ፊት ለፊት ስለሚጋፈጡ የሰጡት መልስ እውነተኛነት፣ ወይም ሐሰተኛነት፣ ተአማኒነት ወይም አጠራጣሪነት በቀላሉ ሊታወቅ ይችላል። ችሎት የምስክሮች እውነተኛነትና ሐሰተኛነት ማረጋገጫ መድረክ ነው። በሰነድ ላይ የተገለፀ ፍሬ ነገር ግን ከችሎት ውጭ የተፈጠረ እንደመሆኑ ማን እንደፈጠረው መቼ እንደፈጠረው እና ለምን አላማ እንደፈጠረው ሰነዱ ራሱ አይናገርም፣ ወይም ቢናገርም አስተማማኝነቱ ጥያቄ ሊያስነሳ የሚችል ነው። እነዚህን ለመሰሉ ጥያቄዎች የሚሰጠው መልስ በሌላ ደጋፊ ማስረጃ ላይ የተመረኮዘ ነው። ስለዚህ የሰነድ ማስረጃ ቀረበ ማለት በሰነዱ ላይ የተገለፀው ፍሬ ነገርን ባለቀለት ሁኔታ አስረዳ ማለት አይደለም፣ በሚገባ ሊመዘን ይገባዋል።

. የቀጠለ. . .

4. ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪም የሰነድ ወይም ኤግዚቢት ማስረጃዎች ምዘና በማስረጃው አይነት የተነሳ የተለየ ምዘና ሂደት የሚከተል ቢሆንም ከምስክሮች
ጋር ምዘና ጋር በተያያዙ የተገለፁት፡-

•ማስረጃው ያስረዳቸዋል የተባሉትን ፍሬ ነገሮች በሚገባ የመለየት

•በምክንያትና በውጤት መካከል ያለውን ግንኙነት በሚገባ የመለየት

•እንዲሁም ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ማስረጃ ምዘና

ፋዳዮች በሰነድና ኤግዚቢት ማስረጃ ምዘና ላይም እንደአግባብነታቸው ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

5. አስቀድሞ እንደተገለፀው የዚህ ምዕራፍ ትኩረት የሰነድ እና ኢግዚቢት ማስረጃዎች ምዘና ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የሰነድ ማስረጃ ምዘና የሚመለከታቸው
በፅሁፍ የቀረቡ ሰነዶች፣ ቴፕና የቪዲዮ ካሴቶች፣ የፎቶግራፍ ማስረጃዎች ...ወዘተ ሲሆኑ ኤግዚቢቶች ተብለው የሚለፁት ደግሞ ፍሬ ነገርን ያስረዳሉ ተብለው የቀረቡ ነገሮች
(ዕቃዎች፣ መሳሪያዎች ...) ናቸው በዚህ ምዕራፍ ትኩረት የሚሰጥባቸውም በስራ አጋጣሚ አዘውትረው በማስረጃነት ሲቀርቡ የሚስተዋሉት በፅሁፍ የተደረጉ ሰነዶች
እና የቴፕና የቪዲዮ ካሴት እንዲሁም የፎቶግራፍ ማስረጃዎች ሲሆኑ በምዕራፉ የተገለፁት ሀሳቦች ከፍርድ ውሳኔዎችን ከሌሎች አገሮች ህጎች (ወይም ጸሁፎች) እንዲስማሙ ተደርገው የተወሰዱ ናቸው፡፡ ገለፃውም በአጠቃላይ ነጥቦች ላይ ብቻ የሚያተኩር ነው፡፡

## የቀጠለ .. .

2.ከላይ የተገለፀውን የበለጠ ለማብራራት ያህል።

•የባህል ሐኪም ነኝ የሚል ሰው ሟች የሞተው በዚህ ምክንያት ነው የሚል ማረጋገጫ ቢሰጥ ክብደት ሊሰጠው ይገባል ወይ ?

•የፍቺ ማስረጃ መሰጠት የሚችለው ፍ/ቤት ነው የሚል ህግ እያለ የቤተዘመድ ሽምግልና ዳኞች የሰጡ የፍቺ ወረቀት ፍቺና ለማረጋገጥ ብቃት አለው ወይ ?

•የሬሳ ምርመራ ውጤት ከአንድ አነስተኛ የጤና ኬላ ቢቀርብልንና ማስረጃውን የሰጠው ሰው "ጤና ረዳት " በሚል የገለፀ ቢሆን ክብደት ሊሰጠው ይገባል ወይ?ወዘተ በማለት መጠየቅ ይኖርብናል ።

## 8.2.2. የጹሑፍ ሰነዶች በሚቀራኑበት ጊዜ ስለማስፈፀም የማስረጃ ምዘና

1. በማስረጃነት የቀረቡት የጹሑፍ ሰነዶች እርስ በርስ ሊቃረኑ ወይም ልዩነት ሊፈጥር ይችላሉ ። ወይም ደግሞ በሰነድ ማስረጃ ላይ የተገለፀው ፍሬ ነገር ምስክር ከሰጠው ምስክርነት ጋር የተለያየ ሊሆን ችላል ። ለማስረዳት ያህል፡-

•ከላይ በጥያቄ መልክ የተጠቀሰውን የቀን ገቢን አስመልክቶ ከትራንስፓርት ባለንብረት ባለንብረቶች ማህበር የተፃፈለት ደበዳቤ እና ተከሳሹ በበኩሉ ከአገር ውስጥ ገቢ መ/ቤት ስለከሳሽ የቀን ገቢ ያቀረበው ደብዳቤ፣

•ስለ አንድ የገንዘብ ጉድለት ጉዳይ የተሰሩ የተለያዩ የኦዲት ሪፓርቶች የተለያየ የገንዘብ ጉድለትን የሚያመለክቱ ቢሆኑ፣

•ሰለ አንድ ንብረት ሽያጭ የተደረጉ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ውሎች (አንዱ ውል ላይ ቤቱን ለከሳሽ የተሸጠ መሆኑ ሲገለጽ በሌላው ላይ ደግሞ ቤቱ ለተከሳሽ የተሸጠ መሆኑን የተገለፀበት )

የቀጠለ . . .

## 8.2. የጽሁፍ ሰነድ ማስረጃዎች ምዘና

### 8.2.1. ብቃትንና ቅርበትን መሰረት ያደረገ ምዘና

1. የሰነድ ማስረጃ ሲመዘን ትኩረት ሊደረግባቸው ከሚገቡ ጉዳዮች አንዱ ማስረጃውን ያዘጋጀው ወይም የሰጠው አካል ይህንን ለመፈፀም ያለው ብቃት ወይም ቅርበት ነው፡፡ የጽሁፍ ሰነዱ ያዘለው ፍሬ ነገር ውሳኔ ለመስጠት አስፈላጊ የሆነውን ፍሬ ነገር ያስረዳ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ፍሬ ነገሩ ተፈላጊውን ፍሬ ነገር ወይም ጭብጥ ያስረዳል ስለተባለ ብቻ ክብደት ይሰጠዋል ማለት አይቻልም፡፡ ሟች የሞተበትን ምክንያት ለማወቅ የህክምና ማስረጃ አስፈላጊ የመሆኑን ያህል፤ በማስረጃነት የቀረበው ሰነድም ሟች የሞተበትን ምክንያት የመግለፁን ያህል ይህንን ያረጋገጠው ሰው ወይም ድርጅት ማስረጃውን ለመስጠት የሙያ ብቃት ከሌለው በሰነዱ ላይ ለተጠቀሰውና ስለሟች ሞት ምክንያት ለሚናገረው ክብደት ሊሰጠው አይችልም ስለዚህም የሰነድ ማስረጃ ሲመዘን፡

- ማስረጃ ሰጭው ተፈላጊውን ማስረጃ ለመስጠት ስልጣን አለው ወይ?

## የቀጠለ . . .

ስለ ሟች አሟሟት ምክንያት በምስክሮችና በህክምና ምርመራ ሪፖርት መካከል የሚታይ ልዩነት ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

2. እንደነዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙም ፍ/ቤቱ የሚከተሉትን መሰረት በማድረግ መመዘን ይችላል ፡፡

•ልዩነት ወይም ቅራኔ መኖሩን በመጀመሪያ ደረጃ መረጋገጥ ያስፈልጋል፣

•ልዩነት ወይም ቅራኔ ያለ ቢመስልም መሰረታዊ መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

•ልዩነት ወይም ግጭት በማስረጃዎች መካከል ሲፈጠር ጉዳዩን ወንጀል ወይም ፍ/ሔር ከሆኑ አንፃር ለይቶ መመዘን ያስፈልጋል ፡፡

•ማስረጃውን ያወጣው ወይም የሰጠው ሰው ማስረጃውን ለማውጣት ያለውን ብቃት ወይም ቅርበት መመርመር ያስፈልጋል ፡፡

•ማስረጃው የሰጠው ወይም ያወጣው ሰው ከተከራካሪ ወገን ጋር ያለው ግንኙነት (ገለልተኛ ነው ወይስ አይደለም ከሚለው አንፃር )መመርመር ያስፈልጋል ፡፡

•ማስረጃ የሰጠው ወይም ያወጣውን ሰው አቅርቦ መመርመር ይችላል ፡፡

የቀጠለ . . .

## 8.2.3. የኦዲት ሰነዶች ምዘናን የሚመለከቱ ተጨማሪ ሐሳቦች

1. የገንዘብ ወይም የንብረት ጉደለት ለማስረዳት የኦዲት ምርመራ ውጤቶች በማስረጃነት የሚቀርቡበት አጋጣሚ በርካታ ነው ። ከዘህ ጋር በተያያዘ የሚከቱለት ሀሳቦች ትኩረት ሊሰጥባቸው ይገባል ።

- የኦዲት ሰነዶች የተጠቀሱት ፍሬ ነገሮች (መተማመኛ ዎች ጭምር እንዳለቁ ማስረጃዎች ( conclusive evidence ) መወሰድ ያለባቸውም ። አስረጅነታቸው የመዘናል ማስተባበያም ሊቀርብባቸው ይችላል ።
- የኦዲት ሰነዶች ከፍርድ ቤት ውጪ የተሰሩ እንደመሆናቸው በደጋፊ ማስረጃዎች መጠናከራቸው (የኦዲተሮች ፣ታዛቢዎች )ለአስተማማኝነታቸው ክብድት እንዲሰጣቸው ያደርጋል ።

2. የኦዲት ሰነዶች በማስረጃነት ሲቀርብ ተከሳሾች ከሚያነሷቸው መከራከሪያዎች መካከል ሂሳብ የተሰራው ትክክለኛ የሂሳብ አሰራር ደንብ ተከትሎ አይደለም ፣ሂሳቡ የተሰራው በሌለሁበት በመሆኑ ፍ/ቤት ማስረጃ አድርጎ ሊወሰደው አይገባም ፣

• የቀጠለ

• መተማማኛ ልፈርም ያልቻልኩት በግዴታ ነው ፣ በቀረቡ መተማመኛዎች ላይ የፈረምኩ ቢሆንም ቅሬታ (Reservatino ) እንዳለኝ በዚያውም ላይ አስቀምጫለሁ ..... የሚሉት ይገኙበታል ።

3. በዚህ መሰረት ፍ/ቤቱ ማስረጃውን ሲመረምርና ሲመዝን የጉዳዩን ዓይነት ግምት ውስጥ ማስገባት (ወንጀል ወይም ፍ/ሔር )የሚጠበቅበት ከመሆኑ በተጨማሪ የመቃወሚያ ነጥቦቹ የኦዲት ሪፖርቱ ላይ የሚያስከትሉትን ውጤት ማጤን ያስፈልገዋል ። ከዚህ አንፃር ተከሳሹ ለመቃወሚያነት የሚያቀርባቸውን ነጥቦች ለማስረዳት ያቀረበውን ማስረጃ ፣እንዲሁም ሂሳቤን የመረመሩት ሰዎች የሰጡትን የምስክርነት ቃል መሰረት በማድረግ ማስረጃውን መመርመር አለበት ።

## 8.2.4. የህትመት ውጤቶች አስረጂነት ምዘና

1. ታትመው የወጡ ጹሁፎች (ጋዛጦች፣መጽሔቶች፣መጽሐፎች...)በማስረጃነት የሚቀርቡበት አጋጣሚ በርካታ ነው ። እነዚህ ጹሑፎች ውስጥ የተጠቀሱትና ማስረጃ ናቸው የተባሉት ፍሬ ነገሮች የስብሰባው መግለጫዎች------- ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ ። እነዚህ በማስረጃነት በቀረቡ ጊዜ አስረጅነታቸው የሚመዘነው ከምን አንፃር ነው? የሚለውን መመለስ የሚገባው ጥያቄ ነው ።

የቀጠለ. . .

2. የህትመት ውጤቶች የአስረጅነት ብቃት የሚላካው ማስረጃ አግባብነት አለው ተብሎ ከቀረበበት ጭብጥና ይመለከተዋል ተብሎ ከተከሰሰው ሰው አንፃር ነው ። በዚህም መሰረት የቀረበው ክስ (ወንጀልም ይሁን ፍ/ሔር )በህትመት መሰረት የተፈፀመ ወንጀልን ወይም የካሳ ክስን መሰረት ያደረገ ከሆነ (አትሞ በማውጣት ማለት ነው ) ለምሳሌ በጹሑፍ ስም ማጥፋት .............. እና የተከሰሰው ሰው አሳታሚው ወይም አዘጋጁ ከሆነ የህትት ውጤቱ ክሱን በቀጥታ የማስረዳት ብቃት ይኖረዋል (የተፃፈው ነገር ስም ማጥፋት እስከሆነ ድረስ ማለተት ነው )። እንዲያውም ለእንደዚህ ዓይነት አትሞ ማውጣትን ለሚመለከት ክስ ሰነዱ ብቸኛ ማስረጃ ነው ለማለት ይቻላል ።

3. እንዲሁም የማስረጃ አግባብነት ታት መውጣትን ለማስረዳት ከሆነ (ለምሳሌ የንግድ ማህበር መመስረቻ ጹሑፍ ታትሞ መውጣቱን ፣የስራ ቦታ ማስታወቂያ ወይም የሀራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ ታትሞ መውጣቱን ) የህትመት ውጤት ታት መውጣቱ እስከተረጋገጠ ድረስ ይህንን የሚገልፀው የህትመት ውጤት ታትሞ መውጣቱ እስከተረጋገጠ ድረስ ይህንን የሚገልፀው የህትመት ውጤት ከፍተኛ አስረጅነት አለው ።

.

<u>የቀጠለ. . .</u>.

4. በሌላ በኩል ግን ክስ አትሞ ማውጣትን ወይም ታትሞ መውጣትን ሳይሆን በህትመት የተገለፀ ዜናን ፣የስብሰባ ቃለ ጉባኤ ፣ቃለ መጠየቅ ....... ወዘተ የሚመለከት ከሆነ በጋዜጣው ላይ የተነገረው ዜና እንዲህ አለ ፣እንዲህ አደረገ ፣በሚል የገለፀውን ሰው ፣በጋዜጣ ወይም በሌላ የህትመት ውጤት ላይ በቃለ ጉባኤ ተወሰነ ተብሎ የተነገረውን ወሰኑ በተባለበት ሰዎች ላይ ወይም ቃል መጠይቅ ላይ መልስ የሰጡትን ሰዎች (ተናጋሪ Author ) በሚመለከት የህትመት ውጤት አስረጅነት ክብደት ሊሰጠው አይችልም ። ተናጋሪውን፣ወይም ውሳኔ ሰጠ የተባለው ሰው በተናገረው ወይም በወሰነው ውሳኔ ለመክሰስ ውሳኔውን ወይም ንግግሩን ያስረዳል በማለት የህትመት ውጤት በማስረጃነት ሲቀርብ (ተናገሪው ራሱ አዘጋጅ ወይም አሳታሚ ካልሆነ በቀር ) በአንግሎ አሜሪካ የህግ ስረዓት ተከታይ አገሮች በሰነድነት የቀረበ የሰሚ ሰሚ ማስረጃ ( Documentary hearsay ) በሚል በማስረጃነት አይቀበሉትም

የቀጠለ . . .

5. በኢትዮጵያ የሰሚ ሰሚ ማስረጃ እንዳይቀርብ የሚከላከል ህግ ስለሌለ ተናጋረውን ለማስጠየቅ የሚቀርብ ይህትመት ውጤትን አንቀበልም ማለት አይቻልም ፡፡ ነገር ግን ማስረጃው በሚገባ መመርመርና መመዘን አለበት ፡፡ ተናጋሪው ተናገረው ፣ወሰነው ፣አደረገው፣የተባለውን ንግግር ውሳኔ ድርጊቱ.........በርግጥ የተናጋሪውን ይሁን የህትመት ውጤቱን የፃፋው ፣የዘጋጀው ወይም ያሳተመው የፈጠረው፣ወይም አቃንቶ ያቀረበው ይሁን ሰነዱን በማየት ብቻ ማወቅ አይቻልም ፡፡ስለዚህ እንዲህ ዓይነቱ ማስረጃ አይቀርብም ማለት ባይገባም አስረጅነቱ ክብደት ሲሰጠው አይገባም ፡፡ ፍ/ቤቱ ክሱን በሉሌ ማስረጃ ማረጋገጥ ይገባዋል፡፡

የቀጠለ . . .

## 8.3. የቴፕ እና ቪድዮ ካሴቶች አስረጂነት ምዘና

1.በቴፕ ወይም በቪዲዮ ካሴቶች የተቀረፀ ወይም የተቀዱ ንግግሮች ወይም በቪዲዮ ካሴት የተቀዱ ምስሎች በማሰረጃነት የሚቀርብበት አጋጣሚ ይኖራል ፡፡ እነዚህ ማስረጃዎች" እንዲህ አለ "እንዲህ አደረገ "ወይም እንዲህ ተደረገ የሚለውን ፍሬ ነገሮች ለማስረዳት አግባብነት ሊኖራቸው ይችላል ፡፡ ነገር ግን አግባብነት አላቸው ማለት አስረድተዋል ፡፡ ማለት ላይሆን ይችላል ፡፡

2. የማስረጃ ተፈላጊነት በፍ/ሔር ጉዳይ ከሆነ ምዘናው ጥብቅ ላይሆን ይችላል አንድም የከሳሽ ማስረጃ ከተከሳሹ ማስረጃ ጋር አብሮ ሊመረመርና ሊገናዘብ ይችላል፡፡ በተጨማሪም የአስረጅነት ደረጃው በተሻለ ይመስላል የሚል በመሆኑ ነው ጉዳዩ የወንጀል ከሆነ ግን ማስረጃው በበርካታ ጥያቄዎች የተወጠረ ነው ፡፡ በዚሁ መሰረት ፍ/ቤት ማስረጃውን ፡-

## •የቀጠለ. . .

•ቴፑን የቀዳው ወይም የቀረፀው ሰው ወይም የተቀዳው ወይም የተቀረፀው ንግግር ወይም ድርጊት ሲፈፀም በስፍራው የነበረው ሰው ከመሰጠው ምስክርነት ጋር በማገናዘብ ፣

•ማስረጃው ተመሳስሎ ሊሰራ (Fabricated) ወይም ተቆራርጦ የቀረበ (Reenacted ) ወይም የተቀነባበረ (Reconstruted ) የመሆኑ ዕድሉ የሰፋ በመሆኑ አስረጅነቱ ሲመዘን ከተቀዳው ወይም ከተቀረፀው ድምጽ ወይም ምስል ሙሉ ይዘት ፣የንግግሩ ወይም ድርጊቱ ዓለማ አንፃር በማገናዘብ መመዘን ያስፈልጋል ፡፡

## 8.4 የፎቶ ግራፍ ማስረጃዎች አስረጅነት ምዘና

1. ፎቶ ግራፍ የአንድን ሰው ማንነት (identity ) ወይም የተጊጂውን የአካል ጉዳት ወይም የተሰረቀውን ንብረት ወይም ወንጀል የተፈፀመበትን ቦታ የሚመለከት ሊሆን ይችላል ፡፡ ያም ሆነ ግን የፎቶግራፍ ማስረጃ ሲመዘን ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል ፡፡

የቀጠለ. . .

2.በመሰረቱ ለቴፕና ቪድዮ ካሴቶች ከላይ የተገለፁት (ፓራግራፍ 171-172) ለፎቶ ግራፍ ማስረጃዎች ምዘናም አግባብነት አላቸው ። በተጨማሪም በማስረጃነት የቀረበው ፎቶ ግራፍ የታተመው ከመጀመሪያው ምንጭ (negative )መሆኑን ማረጋገጥ ተገቢ ይሆናል ። (May P.16)በአጠቃላይም የህትመት ውጤቶችን፣የቴፕና የቪድዮ ካሴቶችን ፣እና ፎቶ ግራፎችን አስረጂነት ለማረጋገጥ የሚያደርግን ጥብቅ የማስረጃ ምዘናን (በተለየ በወንጀል ጉዳይ ) ፍ/ቤቱ የሚከተለው << ፍርድ ቤት እውነትን ይገልፃል ብሎ በሚያምንበት ማስረጃ ላይ በመመስረት ውሳኔ መሰጠት አለበት መየቀረበው ማስረጃ በተቻለ መጠን እውነቱን የሚያረጋግጥ መሆን አለበት >> በሚለው ምክንያት መነሻ ነው

## 8.5. የኢግዚቢት ማስረጃ አስረጅነት ምዘና

የኤግዚቢት ማስረጃ ዋነኛ አስተዋጽኦው አካባቢያዊ ማስረጃ በመሆን ስለተፈለገው ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖር ግንዛቤ እንዲወሰድ ማድረግ ነው ። ስለዚህ የኤግዚቢት ማስረጃ በሌላ ማስረጃ የተነገረውን በመደገር (corroboration )ማገልገል እንጂ ሌላ ማስረጃ በሌለበት በራሱ ተፈላጊው ፍሬ ነገር መኖሩን ወይም አለመኖሩን ያረጋግጣል ማለት አዳጋች ነው ። ያም ሆኖ ግን ሌሎች ማስረጃዎችን የማጠናከር አስተዋጽኦው ከፍተኛ ነው ።

የቀጠለ . . .

ለምሳሌ በወንጀል ጉዳይ ተሰረቀ የተባለውን ዕቃ በማየት በምስክሮች ቤት ገብቶ ዕቃውን ካወጣ በኋላ ተሸክሞ ሲሮጥ አይቻለሁ ›› በሚል ከተነጋገረው ቃል ጋር በማገናዘብ ዕቃውን ሰው ተሸክሞት ሲሮጥ የሚችል መሆኑ አለመሆኑን ፍ/ቤቱ ሊረዳው ይችላል ፡፡ ግዲያ ለመፈፀም አገልግሎት ላይ የዋለ በሚል የቀረበን ዱላ በማየት ዱላው ሰው መግደል የሚያስችል መሆን አለመሆኑን ለመገንዘብና ተከሳሹ ደበደበ በሚል በተናገሩት ቃሎችና ሞተ በተባለው ሰው ሞት መካከል የምክንያትና የውጤት ግንኙነት እንዳለና እንደሌለ ለመገመት ያስችላል ፡፡ በአጠቃላይ የኤግዚቢት ማስረጃ ምዘና በሌላ ማስረጃ የተናገረውን ፍሬ ነገር ትክክለኛን ወይም ታዓሚኒነት በመገንባት ወይም በማፍረስ ላይ ያተኮረ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል ፡፡

# ምዕራፍ 9

## የዕምነት ቃል አስረጂነት ስለመመዘን

### 9.1. ጠቅላል

1. በምዕራፍ 2 ላይ "ማስረጃ ማቅረብ ስለሚያስፈልጋቸው ፍሬ ነገሮች " በሚል ርዕስ ስር ከተጠቀሱት ጉዳዮች መካከል "የታመኑ ፍሬ ነገሮች " እንደሚገኙበት የታመኑ ፍሬ ነገሮችን" ከፍ/ቤት ውጪ" እና ከፍ/ቤት ውስጥ " በሚል ከፋፍሎ ማየት እንደሚቻል ከነዚህም ውስጥ ከፍ/ቤት ውጪ የታመኑ ፍሬ ነገሮች ተፈላጊውን ፍሬ ነገር በተመለከተ በራሳቸው ማስረጃዎች ሲሆኑ ነገር ግን ማስተባበያ ማስረጃ ሊቀርብባቸው እንደሚችል በፍ/ቤት ውስጥ የታመኑ ፍሬ ነገሮች የሚባሉት ደግሞ በፍ/ሔር ጉዳይ ማስተባባያ ማስረጃ ሳይቀርብባቸው ለታመነው ፍሬ ነገር መኖር ማረጋገጫ ተደርገው ሊወሰዱ የወንጀል ጉዳይ ከሆነ ግን እንደሁኔታው በከሳሽ ማስረጃነት ከመቆጠር እና በሌላ ማስረጃ ከመደገፍ አልፈው ማስተባባያ ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልግ የጥፋተኛነት ውሳኔ ሊያስጡ እንደሚችሉ ተገልፆአል።

2. በሌላ በኩል ደግሞ "የታመኑ ፍሬ ነገሮች ላይ ማስረጃ ማቅረብ አያስፈልግም" ቢባልም እንዲህ ዓይነት መደምደሚያ ላይ መድረስ "ፍሬ ነገሮች በርግጥ ታምነዋል ወይ ? በሚል መጠየቅ ያስፈልጋል ። ፍሬ ነገሮቹ የታመኑ ናቸው ስለዚህ ማስረጃ ማቅረብ አያስፈልጋቸውም ለማለት አስቀድሞ መታመናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል ይህ ደግሞ ተከሳሹ (በወንጀልም ሆነ በፍ/ሔር )የሰጠውን ቃል ከክሱ ጭብጥ ጋር ማገናዘብን የሚጠየቅ ነው ። በዚህም መሰረት ማስረጃ በቀረበ ጊዜ ማስረጃው አስረድቷል ወይም አላስረዳም የሚለውን ለመወሰን መመዘን እንዲሚያስፈልግ ሁሉ በጭብጥ የተያው ፍሬ ነገር ታምኗል ወይስ አልታመነም ለማለት የተሰጠውን ቃል መመዘን አስፈላጊ መሆኑን ያመለክታል ። ስለዚህም "የታመነ" የተባለው ፍሬ ነገር የታመነ መሆኑን ለማረጋገጥ ‹‹ በርግጥ የዕምነት ቃል ነው ወይ? በሚል መጠየቅና መመዘን ተገቢ ነው ።

## የቀጠለ . . .

3. ከዚህ አንፃር በተከሳሽ የተሰጡ ቃሎች ላይ ላዩን የታመኑ ፍሬ ነገሮች የሚመለከቱ ቢመስሉም ነገር ግን ከተፈላጊው ጭብጥ ወይም ፍሬ ነገር አንፃር ሲገናዘቡ ታምኗል የሚያስብሉ ይሆናሉ ። ተከሳሹ ሾፌሩ ሆኖ ሳለ ከሙያው አንፃር ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ሲገባው በገባው በቸልተኝነት ሰው ገጭቶ ገድሏል " በሚል ለቀረበበት ክስ በሰጠው ቃል "መስመሬ ጠብቄ እየነዳሁ እያለ ሟች መኪና ተከልሎ በድንገት ገብቶብኝ ሊገጭ ይችሏል " ቢል በግርድፍ ሲታይ የአመነ ቢመስልም ነገር ግን ጠበቅ ተብሎ ሲመረመር ድርጊቱ የተፈፀመው በቸልተኛነት ይሁን በአጋጣሚ ለመለየት አያስችልም ።ስለዚህም ይህንን ቃል በእምነት ቃልነት ከመውሰድ ይልቅ ድርጊቱ ስለተፈፀመበት አካባቢያዊ ሁኔታ (ማለትም የተከሳሹን ፍጥነት መጠንና፣ የተፈቀደውን የፍጥነት መጠን ፣ሟች ተከልሎበታል የተባለው መኪና እይታን የሚከለክል መሆን አለመሆኑ ሟች ወደ መኪና መንገድ የገባበት ሁኔታ ) በማስረጃ ሊረጋገጥ ይገባዋል ። የዚህ ምዕራፍ ትኩረትም ተቀባይንትን መመዘኛ የአሟላ የዕምነት ነው የተባለው ቃል በርግጥም የዕምነት ቃል መሆኑ ወይም አለመሆኑ የሚመዘንበትን መሰረታዊ ነጥቦች መግለጽና ።

- **የቀጠለ**

•**በመጨረሻ** ወደ ዝርዝር ነጥቦች ከመግባት አስቀድሞ የታመነ ፍሬ ነገር ነው የተባለው ቃል አመዛዘን ከወንጀልና ፍ/ሐር ጉዳዮች አንፃር ያለው ልዩነት ሊታወቅ ይገባል ፡፡በምዕራፍ

- 2 ስር እንደተጠቀሰው አንድ ፍቴ ነገር ታምኗል የሚባልበት መመዘኛና የሚያስከትለው ውጤት እንደ ጉዳዩ ፍ/ሐር ወይም ወንጀል መሆኑ የሚለየይ በመሆኑ

- በዚህ ምዕራፍ ስለታመኑ ፍሬ ነገሮች አስረጂነት የሚገልፀውም ይህንን መሰረት በአደረገ ሁኔታ ይሆናል ፡፡

## 9.2 በወንጀል ጉዳይ የታመነ ፍሬ ነገሮች አስረጅነት ምዘና

1. በወንጀል ጉዳይ የታመነ ፍሬ ነገሮች ብለን የምንመድባቸው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥሥቁ 27/2/ እና ወይም በቁጥር 35 መሰረት ለመርማሪ ፖሊስ ወይም በምርመራ ጊዜ ቃል ለተቀበለ

ፍ/ቤት የተሰጡ ቃሎች እና ከቁጥር 132-134 ላይ በተደነገገው መሰረት ክስ ችሎት ቀርቦ ተነብቦ ተከሳሹ እምነት ክህደት ሲጠየቅ የሰጠው ቃል ናቸው ፡፡ የመጀመሪያው (በቁጥር 27 እና ወይም 35 መሰረት የተሰጠው )ቃል የዕምነት ቃል ነው በሚል ከመደምደምና ክሱን አስረድቷል ከማለት በፊት ፣

•የቀጠለ . . .

•ወንጀሉን የሚያቋቋሙትን ፍሬ ነገሮች (ድርጊቱና የሀሳብ ክፍሉን ) እንዲሁም አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ድርጊቱን ለመፈፀም ያነሳሳ ምክንያት (motive ) ተሟልቶ የታመነ መሆኑን

•ተፈላጊው ምክንያትና ውጤት ግንኙነት የተሟላ መሆኑን፣

•የተሰጠው ቃል የመከላከያ ጭብጥ የሌለበት መሆኑን፣ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

2.በተጨማሪም በተሞክሮ እንደሚታየው ሰዎች ወንጀል መፈፀማቸውን ፣አምነው ቃላቸውን እንዲሰጡም ባልተገደዱበት ሁኔታ በተለያዩ ምክንያቶች ፤

-ለምሳሌ የምርመራው ትክክለኛ አቅጣጫ ለማሳትና ሌሎች ሰዎችን በወንጀል ከመጠየቅ ለማዳን ፣ወይም የገንዘብ ጥቅም ለማግኝት ፣ማህበራዊ ተቀባይነት ለማግኘት

- ወይም ከማይፈልጉት ግዴታ ለመዳን ያልፈፀሙትን ወንጀል ፈጽመናል በማለት ቃላቸውን ሊሰጡ ይችላሉ (መዝገቡ ምትኬ ገጽ 50-52) በዚህም መሰረት ምንም እንኳን

-የሰጡት ቃል ከሌሎች ደጋፊ ማስረጃዎች ጋር በማገናዘብ የተሰጠው ቃል በትክክልም የዕምነት ቃል መሆኑን ማረጋገጥ ተገቢ ነው ። እንዲሁም ተከሳሹ የመከላከያ ማስረጃ

-የአቀረ ከሆነ የዕምነት ቃሉ እና የመከላከያ ማሰረጃዎቹ የገለፁዋቸው ፍሬ ነገሮች ተገናዝበው ሊመረመሩ ይገባል ።

3. የዕምነት ቃሉ የተሰጠው በፍ/ቤቱ ክሱ ተነብቦ ካበቃና ተከሳሹ እንዲረዳው ከተደረገ በኋላ ለተጠየቀው የእምነት ክህደት በመልስነት ተከሳሹ ያስመዘገበው ከሆነም ከላይ የተጠቀሱት (ፓራግራፍ 184) የመመዘኛ ነጥቦች ተፈፃሚነት አላቸው፡፡ የ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/134(1) ላይ እንደተገለፀው ተከሳሹ አመነ ለመባል "በክሱ ማመልከቻው ላይ የተዘረዘረውን ወንጀል ለመስራቱ በሙሉ ያመነ " መሆኑ መረጋገጥ አለበት (ፓራግራፍ 31 ተመልከት )፡፡ ስለዚህ

•በከፊል የሚሰጡ የዕምነት ቃል የሚባል ነገር የለም ፡፡ በክሱ ማመልከቻው ላይ የተገለፀውን በሙሉ ሊያምን ይገባልና ፡፡

•ተሰጠ በተባለው የዕምነት ቃል ውስጥ ከፊሉን ማለትምተከሰሹን የሚያጠይቀውን ብቻ ነጥሎ ወስዶ ጥፋተኛ ነህ ማለት አይገባም ፡፡ የሚጎዳውም የሚጠቅመውም ቃል አንድ ላይ ተወስዶ ከቀረበው ክስ አንፃር የዕምነት ቃል ነው ለማለት ያስችላል ?ወይም አያስችልም ? የሚለው መወሰን አለበት ፡፡

### 9.3 በፍ/ሔር ጉዳይ የታመኑ ፍሬ ነገሮች አስረጅት ምዘና

በፍ/ሔር ጉዳይ የዕምነት ቃል ሊሰጥባቸው የሚችሉባቸው ሁኔታዎች በምዕራፍ 2 ላይ ተመልተዋል (ፓራግራፍ 33-34 ተመልከት )ከዚህ አንፃር የመጀመሪያው እርምጃ ፍሬ ነገሮቹ የታመኑ መሆናቸውን ማረጋገጥ ሲሆን ይህም በአቤቱታ ላይ የተገለፀው ፍሬ ነገር መሰረት በማድረግ ተከሳሹ ከሚሰጠው መልስ ጋር በማገናዘብ መመርመርን ይጠይቃል ፡፡ በዚህም መሰረት

- በአቤቱታ ጽሑፎች እና በችሎት ክርክሮች ተከሳሹ (ወይም የተከሳሽ ክስ ካላ ከሳሹ )የገለፃቸው ፍሬ ነገሮች ተለይተው መታወቅ አለባቸው ፡፡
- በዚህም መሰረት በግልጽ አምኖአል ለማለት ተከሳሹ (ወይም የተከሳሽ ከሳሽ ክስ ካላ የከሳሹ )በከሳሹ (ወይም በተከሳሽ ከሳሹ )አቤቱታ የተገለፀውን
- በግልጽ መቀበሉ መረጋገጥ አለበት ፡፡
- በዝምታ ታምኖአል ለማለትም በክስ ወይም በተከሳሽ ከሳሽ ክስ አቤቱታ ላይ የተገለፁት ፍሬ ነገሮች በማመን ወይም በማስተባበል መልስ ያልሰጠባቸው መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል ፡፡
- እንዲሁም ከችሎት ውጪ የታመነ ፍሬ ነገር ከሆነ የታመነው ፍሬ ነገር ከተከሳሹና መከላከያ ማስረጃዎች አንፃር መመዘን አለበት፡፡
- በመጨረሻም ታምኖአል ወይም አልታመነም በሚል ለመወሰን የታመነ ነው ፡፡ በሚል የተሰጠው ቃል አስረጂነት በተያዘው የፍ/ሔር ጉዳይ የአስጅት መማዘኛ
- (ደረጃ )አንፃር መታየት አለበት ::
-

–

# አመሰግናለሁ ።

